


የቴዲ አፍሮ "ህያው የክብር ሽልማቶች!"



"ፖለቲከኞች በብሄርተኝነት ቫይረስ ሕዝብን እየበከሉ ነው"
ዶ/ር ንጋቱ አስፋው



"የጠፋው ልጅ"
ለምን ሲሳይ፤ ዓለም አቀፉ ኢትዮጵያዊ ባለቅኔ



"ኢትዮጵያ በአንድነትና በሰላም ብትኖር ደስታዬ ነው"
ሳምራዊት ደረጀ

የመጨረሻው ንጉሰ ነገስት አጼ ኃይለ ስላሴ

የኢትዮጵያ ዩኒቨርስቲዎች የክብር ዶክትሬት


መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን!

# ግዮን

በየሳምንቱ ቅዳሜ

ግዮን ቅጽ 2 ቁጥር 66 ሐምሌ 2011 ዓ.ም

ዋጋ 14.99


# የኢጄቶ ጨካኝ ልብ!

## የዘር ጥላቻ፣ ሞት፣ ንብረት ውድመት፣ ዘረፋ፣ ኮማንድ ፖስት፣ የባለስልጣናት እግድ - በደቡብ ኢትዮጵያ

## የክልልነት ጥያቄዎችና የደኢህዴን ውጥረት



"አገር ሰላም ሳትሆን ስለ ነጭ
ሳር ማሰብ አይቻልም!"
የፓራዳይዝ ሎጅ ባለቤት አቶ ኢያሱ ወሰን
2
የኢጄቶ ጨካኝ ልብ!

የክልል ጥያቄ፣ የዘር ጥላቻ፣
ሞት፣ ንብረት ውድመት፣
ዘረፋ፣ ኮማንድ ፖስት በደቡብ
ኢትዮጵያ
በዝግጅት ክፍሉ

3
"ደቡብ"
(ከፋ፣ሸካ፣ጎፋ፣ጋሞ፣ሲዳማ፣
ቤንች፣ሃዲያ፣ጉራጌ፣ወላይታ
፣ጋሞ...)
የክልልነት ጥያቄዎችና
የደኢህዴን ውጥረት

መላክ ቢ.
5

የፋኖ፣ ቄሮ፣ ኢጄቶ፣ ዘርማና
መሰል ቡድኖች ባለቤት ማነው?
8


14

"ፖለቲከኞች በብሄርተኝነት ቫይረስ
ሕዝብን እየበከሉ ነው"
ዶ/ር ንጋቱ አስፋው


23

የቴዲ አፍሮ "ህያው
የክብር ሽልማቶች!"

የፋኖ ጅራፍ ራሱን ገርፎ ራሱ ሲጮህ
ጌታቸው መላኩ
9

የአዲስ አበባ "አዳዲስ አበቦች!"
10

የኢትዮጵያ ዩኒቨርስቲዎች የክብር ዶክትሬት
አለማየሁ ባዘዘው
11

ለዛ
12

ብሔርተኝነት "ቅርስ" እንጂ ማንነት
ወይም ዜግነት አይደደለም!
መታሰቢያ መልአከ ሕይወት

18

"የጠፋው ልጅ"
ለምን ሲሳይ፤ ዓለም አቀፉ ኢትዮጵያዊ
ባለቅኔ
ብሩክ መኮንን
19

ወጣቶች ከልዩነት ጎራ ወጥተው
መቀራረብና ትስስር መፍጠር
አለባቸው
ከእሸቱ ደስታ
21

የመጨረሻው ንጉሰ ነገስት አጼ
ኃይለ ስላሴ
ብሩክ መኮንን
22

ቀጣይ ዕትም
ቅዳሜ
ሐምሌ 27
ይጠብቁን!



ቁጥር 65 ዕትም

የስፖርት ችግሮቻችንን መቅረፍ!
24
በአዲስ አበባ የሌኒን ሀውልት
ውዝግብ !
27

"ኢትዮጵያና ዓለም
በአንድነት በሰላምና
በፍቅር ብትኖር ደስታዬ
ነው!!"
የሚስ ኢትዮጵያ በአሜሪካ
አሸናፊ፣ ሳምራዊት ደረጀ


25

# “አገር ሰላም ሳትሆን ስለ ነጭ ሳር ማሰብ አይቻልም!”

## የፓራዳይዝ ሎጅ ባለቤት አቶ ኢያሱ ወሰን

ከ“ክልል እንሁን” ጥያቄ ጋር ተያይዞ በደቡብ ኢትዮጵያ የተከሰተውን ግጭትና የደረሰውን ጉዳት በሚመለከት አስተያየት የሰጡት የአርባ ምንጩ ፓራዳይዝ ሎጅ ባለቤት አቶ ኢያሱ ወሰን የአርባ ምንጭ አባቶችና የከተማው ወጣቶች በሌሎች የደቡብ ክልል ከተሞች የተከሰተውን አይነት ጥፋት በከተማቸው እንዳይደርስ ለማድረግ በምክክርና በውይይት ላይ የተመሰረተ ሰፊ ስራ እየሰሩ መሆናቸውን ገለፁ፡፡

በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መስተዳደር ስር የሚገኙ ዞኖች ክልል የመሆን ሕገ መንግስታዊ መብታቸው እንዲከበር በአደባባይ ሰልፍ ጭምር ደጋግመው ሲገልፁ የቆዩ ሲሆን በተለይም በሲዳማ ዞን ይህንኑ ጥያቄ በገዛ ፈቃድ በሀይል ለማስፈፀም የተደረገው እንቅስቃሴ ወደ ግጭት ተለውጦ ለበርካቶች ሞትና ንበረት ውድመት መንስኤ ሆኗል፡፡

“ክልል እንሁን” የሚል ጥያቄ ካላቸው ዞኖች መካከል አንዱ የሆነው የጋሞ ተወላጅ የሆኑት አቶ ኢያሱ ከሰሞኑ በክልሉ የተከሰተውን አለመረጋጋት አስመልክተው በሰጡት አስተያየት “የሚሞተው የደሃ ልጅ ነው፡፡ ፖለቲከኞቹን ወይም ልጆቻቸውን የለኮሱት እሳት አይነካቸውም፡፡ መንገድ እያዘጉ የሀገር ኢኮኖሚ ድጋፍ የሆነው ቱሪስት እንዳይመጣ ማድረግ፣ እንደ አረጋሽ ሎጅ ያሉትን ማቃጠል ሀገርና ህዝብን ለተጨማሪ ጉዳት ከማዳረግ ውጪ ለማንም ጥቅም ስለማይሰጥ በተለይ ፖለቲከኞች ቆም ብለው ማሰብ ይኖርባቸዋል፡፡ ከሀይልና ረብሻ ይልቅ ወደ ንግግር መምጣት አለባቸው፡፡ እነርሱ በለኮሱት እሳት የደሃ ልጅ እየሞተ፣ የሀገሪቱ ንብረት እየወደመ ነው፡፡ አዛውንቱ፣ ወጣቱ፣ ተማሪው፣ ሴቱ፣ ወንዱ፣ መምህሩ፣ ፖለቲከኛው፣ የሀይማኖት አባቱ፣ ሀኪሙ ሁሉም በጋራ ሆነው ስለአገር መቆርቆርና ማሰብ ካልቻሉ የአገራችን ሁኔታ ከባድ ነው›› ሲሉ ተናግረዋል፡፡




ባለፈው ረቡዕ ሐምሌ 17 ቀን 2011 ዓ.ም በአርባ ምንጭ ከተማ ስለሚገኘው ፓራዳይዝ ሎጅ የማስፋፊያ ፕሮጀክት፣ በቱርሚ ስለተሰራው የፓራዳይዝ ቅርንጫፍ ሆቴልና ሪዞርት እንዲሁም በጂንካ ከተማ በአንድ መቶ ሚሊዮን ብር በጀት ሊሰራ ስለታቀደው የፓራዳይዝ ሎጅ አዲስ ፕሮጀክት ለጋዜጠኞች መግለጫ የሰጡት አቶ ኢያሱ በክልሉ የሚታየው የፀጥታ መደፍረስ ለያዟቸው እቅዶችና እያከናወኑ ላሉት የቢዝነስ እንቅስቃሴ ምን ያክል ጫና እንደፈጠረ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ “የእኛ ተቋማት ባሉበት የጋሞ እና አካባቢው ዞኖች ናቶ የሚባሉት ወጣቶችና የአገር ሽማግሌዎች ከክልሉ አስተዳደር ጋር በመናበብ ሰላምን ለማረጋገጥ እየሰሩ በመሆኑ በዚህ በኩል ብዙም ስጋት የለብንም፡፡ ይሁንና በየትኛውም የአገራችን ክፍል የሚፈጠር ችግር ሁሉ ያሳስበናል፡፡ በየትኛዋም ቦታ ያለ ወገናችን ጉዳት ሲደርስበት በእጅጉ ያሳዝነናል፡፡ አገር ሠላም ካልሆነች ነጋዴዎች ስራችን ይጎዳል፡፡ አገራችን ሠላም ሣትሆን ስለነጭ ሣር ማሰብ አይቻልም፡፡ ሠላም የሁሉም ነገር መሰረት በመሆኑ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ስለሠላም መነጋገርና ተቀራርቦ መስራት ይኖርበታል” ብለዋል፡፡

በአርባ ምንጭ ከተማ እጅግ ውብና ማራኪ የተፈጥሮ በረከቶችን ማየት በሚቻልበት የከተማው ከፍታ ቦታ ተገንብቶ ከፍተኛ ቁጥር ላላቸው የውጭ ሀገራት ዜጎችና የኢትዮጵያ ተወላጆች አገልግሎት ሲሰጥ የቆየው ፓራዳይዝ ሎጅ በቱርሚ ከተማም ቅርንጫፍ ከፍቶ አገልግሎት በመስጠቱ አገራችን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ገቢ ልታገኝ መቻሏን አያይዘው የገለፁት አቶ ኢያሱ ድርጅታቸው እስካሁን ለ340 ቋሚ ሰራተኞችና ከ500 ለማያንሱ ጊዜያዊ ሠራተኞች የሥራ ዕድል መፍጠሩን አመልክተዋል፡፡ በአርባ ምንጭ ፓራዳይዝ ሎጅ ማስፋፊያ ፕሮጀክት (ፓራዳይዝ ሞቴል) የአገር መሪዎችን ማሳረፍ የሚችሉ ፕሬዚዳንሻል ሩሞች እና የስፓ አገልግሎት መካተቱን ገልፀው በጂንካ ሊከፈት ዕቅድ የተያዘለት የፓራዳይዝ ቅርንጫፍ በቅርቡ ዕውን እንደሚሆን ያላቸውን እምነት ተናግረዋል፡፡

ማኅበራዊ ሀላፊነትን በመወጣት በኩል በአካባቢያቸው ምን እንዳደረጉ ከጋዜጠኞች ጥያቄ የቀረበላቸው አቶ ኢያሱ ወሰን ባለፉት ጊዜያት ግምታቸው ሰባት መቶ ሺህ ብር የሚገመቱ ላፕቶፕ ኮምፒዩተሮችን ገዝተው ለአካባቢው ት/ቤቶችና ተማሪዎች እንደሰጡ፣ ጫኖ በሚባለው አካባቢ ት/ቤት ሰርተው እንዳስረከቡ፣ ለጌዲዮ ተፈናቃዮች በፓራዳይዝ ሎጅ የነበሩ በርካታ መገልገያ ቁሳቁሶችን በጋሞ ሴቶች በኩል እንደላኩና ለመቄዶንያ የአረጋውያን አዕምሮ ህሙማን ማዕከል በየጊዜው ድጋፍ እንደሚያደርጉ ገልፀዋል፡፡

በሸራተን አዲስ ሆቴል የድርጅታቸውን እንቅስቃሴና በክልላቸው ያለውን ወቅታዊ ሁኔታ በዝርዝር ያስረዱት ባህብቱ “የፓራዳይዝ ሎጆች መከፈት አገራችን አጥብቃ የምትፈልገውን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እያስገኘ መሆኑ በግልፅ የሚታወቅ ቢሆንም በመንግስት ስር ያለው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ግን ለማስፋፊያ ፕሮጀክቶቻችን ማስፈፀሚያ የሚሆን ብድር ሊሰጠን አልፈቀደም” በማለትም ቅሬታቸውን ተናግረዋል፡፡

## ኢትዮ ቴሌኮም በኢንተርኔት መቆራረጥ 204 ሚሊዮን ብር ማጣቱን ገለጸ!!

ኢትዮ ቴሌኮም በኢንተርኔት መቆራረጥ ምክንያት ብቻ 204 ሚሊዮን ብር ማጣቱን ገለጸ፡፡ ኢትዮ ቴሌኮም የ2011 በጀት ዓመት እቅድ አፈጻጸሙን አስመልክቶ ለመገናኛ ብዙሃን መግለጫ ሰጥቷል፡፡ የድርጅቱ ዋና ስራ አስፈጻሚ ወይዘሮ ፍሬህይወት በዚህ ጊዜ እንዳሉት በኢንተርኔት መቆራረጥ ምክንያት ብቻ 204 ሚሊዮን ብር አጥተናል ብለዋል፡፡

ከዚህ በፊት በኢንተርኔት መዘጋት ምክንያት ኢትዮጵያ በቀን 4 ነጥብ 5 ሚሊዮን ዶላር ታጣለች ተብሎ የወጣው ዘገባ ስህተት መሆኑን ስራ አስፈጻሚዋ ተናግረዋል፡፡

ኢትዮ ቴሌኮም በ2011 በጀት ዓመት 36 ነጥብ 3 ቢሊዮን ብር ገቢ ማግኘቱን ገልጿል፡፡ የተገኘው ገቢ የእቅዱን 80 በመቶ ያሳካ ሲሆን ገቢው ከአምናው ጋር ሲነጻጸር በ7 በመቶ ብልጫ ማሳየቱን ወይዘሮ ፍሬህይወት ተናግረዋል፡፡

ድርጅቱ የደንበኞቹን ቁጥር 43 ሚሊዮን ያደረሰ ሲሆን አገራዊ የቴሌኮም ስርጭቱ 44 ነጥብ 5 በመቶ መድረሱም በመግለጫው ወቅት ተገልጿል፡፡

በተጠናቀቀው በጀት ዓመት በአገሪቱ የተወሰኑ አካባቢዎች የጸጥታ ሁኔታ አስጊ በመሆኑ የቴሌኮም አገልግሎቶች የግድ ማቋረጥ አስፈልጓል ይሄ ደግሞ በገቢው ላይ ተጽዕኖ ፈጥሮብናል ሲሉ ስራ አስፈጻሚዋ ተናግረዋል፡፡

## ኢትዮጵያዊው የአፍሮቢት ስልተምት አቀንቃኝ ለብላክ ፓንተር ፊልም ተመረጠ

ዋካንዳ ኢንተርናሽናል ኮላቦሬሽን የሙዚቃ ቪዲዮ እና ቶማስ ኃይሉ(ቶሚ ፕላስ) ሐምሌ17 ቀን 2011 በካሌብ ሆቴል  ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥተዋል፡፡  በዓለም አቀፍ ደረጃ እጅግ ተወዳጅነት ባገኘው ብላክ ፓንተር ፊልም አስተዋዋቂ ድርጅት ዋካንዳ አድቨርታይዚንግ አማካኝነት ዓለምአቀፍ ደረጃውን ጠብቆ ለሚሰራው የሙዚቃ ቪዲዮ፤ ኢትዮጵያዊው ቶማስ ኃይሉ መመረጥና መፈራረም ለኢትዮጵያ ታላቅ ዜና ሆኗል፡፡

ቶማስ ኃይሉ በሙዚቃ ስሙ (ቶሚ ፕላስ) የ27 ወጣት የአፍሮቢት ስልተምት አቀንቃኝ፣ የባህላዊ ውዝዋዜ ተወዛዋዥ፣ የዘመናዊ ዳንስ ባለሙያ እና አሰልጣኝ፣ ከ40 በላይ በሆኑ የሙዚቃ ቪዲዮዎችም በተወዛዋዥነትና በኬሮግራፈርነት ሰርቷል፡፡ በሙዚቃ  የመጀመሪያ ስራው ትወጂናን በ2010 ዓ.ም፤ለሙዚቃ አፍቃሪያን አድርሷል፡፡ ከ1 ሚሊዮን በላይ የማህበራዊ ሚዲያ ተመልካቾች በሀገራችን፤ እንዲሁም ከ18 በላይ የምስራቅ አፍሪቃ የቴሌቪዥን ቻናሎች ላይ በመታየትነ በሬድዮ በመደመጥ ተወዳጅነት አትርፏል፡፡  ቶሚን ለብላክ ፓንተር ኢንተርቴይመንት የሙዚቃ ስራ ያሳጨው አዲሱ የሙዚቃ ቪዲዮ ኢንተርናሽናል ደረጃውን የጠበቀ ጥራትና ቴክኒክ ያለው መሆኑ፣በፓን አፍሪካኒዝም በ2 የአፍሪካ ሀገራት ግኑኙነት ላይ የራሱን አሻራ ማስቀመጡ ከሌሎች መስፈርቶች ጋር ተዳምሮ መሆኑን  ከመግለጫው ተጠቁሟል፡፡ “ዋካንዳ ኢንተርናሽናል ኮላቦሬሽን” የሚል ስያሜ በተሰጠው የሙዚቃ ስራ ላይ  ሌሎች ሁለት የአፍሪካ አቀንቃኞችም በጋራ ይሰራሉ፡፡ የሙዚቃ ሪከርዲንግ፣ ሚክሲንግ እና ማስተሪንግ በአሜሪካ ወይም በኬንያ ተሰርቶ፣ ቪዲዮው ሙሉ በሙሉ በምስራቅ አፍሪካ ሀገራት ይሰራጫል ተብሏል፡፡ ባሳለፍነው ወር የናይጄሪያዊው ፓቶራንኪንግ ማኔጅመንት አዲስ አበባ ተገኝተው፤ ከቶሚ ጥምረት ፈጥረው እንደሚሰሩ መናገራቸው ይታወሳል፡፡

# በብሔራዊ ሐዘን ምክንያት የተራዘመው የአስቴር አወቀ “ጨዋ” አልበም ወጣ!




ኢትዮጵያዊቷ “የሶል ሙዚቃ ንግሥት” ድምፃዊት አስቴር አወቀ ሰኔ 15 ቀን 2011 ዓ.ም በአማራ ክልልና በአዲስ አበባ ከተከሰተው የባለስልጣናት ግድያ ጋር ተያይዞ በሀገራችን ብሔራዊ ሐዘን በመስፈኑ ምክንያት ላልተወሰነ ጊዜ አራዝማው የነበረው “ጨዋ” የተሰኘ አዲስ አልበሟን በዚህ ሣምንት ለገበያ ውሏል፡፡

የደምፀ መረዋዋ ተወዳጅ ሙዚቀኛ አስቴር አወቀ “ጨዋ” አልበም ለአድማጭ እንዲደርስ ታስቦ የነበረው ከ20 ቀናት በፊት ሆኖ በወቅቱም አልበሟን የማስተዋወቅ ሰፊ ዘመቻ ተጀምሮ የነበረ ቢሆንም በሀገሪቱ ድንገት በተከሰተው ብሔራዊ ሐዘን ምክንያት ከታሰበለት ቀን ሊራዘም ችሏል፡፡

በሙዚቃ ዓለም በቆየችባቸው ረጅም ዓመታት ያካበተችው ዕውቀት፣ ልምድ፣ ጥልቅ የስሜት መረዳት እና የስብዕና ልህቀት በሚገባ ተንፀባርቆበታል የተባለው አዲሱ “ጨዋ” የሙዚቃ አልበም በብሔራዊ ሐዘኑ ምክንያት እንደተራዘመ የገለፀችው አርቲስቷ በወቅቱ “ሰኔ 15 ቀን 2011 ምሽት በተፈጠረው አስደንጋጭ ሁኔታ ምክንያት ለስርጭት ተዘጋጅቶ የነበረው ጨዋ አልበም በአገራችን ባህልና ልማድ መሠረት ለተወሰነ ጊዜ እንዲራዘም መወሰናችንን ለመግለፅ እወዳለሁ” በማለት ገልፃ ለኢትዮጵያውያን መፅናናትን፣ ለአገራችንም ሰላምን ተመኝታ ነበር፡፡

ማክሰኞ ዕለት በይፋ መደመጥ የጀመረውን ይህን የአስቴር “ጨዋ” አዲስ አልበም ለገበያ ያቀረበው ኢዮሃ ኢንተርቴይመንት ሲሆን፣ ኢዮሃ በኤግዚብሽን ማዕከል የበዓል ንግድ ትርዒትና ባዛሮችን እንዲሁም ልዩ ልዩ የሙዚቃ ኮንሰርቶችን በማዘጋጀት በስፋት ይታወቃል፡፡

የጨዋ አልበም ስርጭት ለየት ባለ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን የገለፁልን የኢዮሃ የሥራ ሀላፊዎች የአልበሙን ሽያጭ ብቻ የሚያከናወኑ አዟሪዎችና በተለያዩ ቦታዎች ላይ እንደ ጊዜያዊ የሽያጭ ማዕከል የሚያገለግሉ ተሽከርካሪዎች ተሰማርተው ይገኛሉ ብለዋል፡፡ ይህም የአርቲስቷን 26ኛ አልበም ሽያጭ የትኛውም ሙዚቃ ወዳድና የአርቲስቷ አድናቂ በቀላሉ ለማግኘት እንዲያስችለው ይረዳል፡፡

## ጌጅ ኮሌጅ ለመጀመሪያ ጊዜ በማስተርስ ተማሪዎቹን አስቀመረቀ

ጌጅ ኮሌጅ ሐምሌ 18 ቀን 2011 ዓ.ም በተለያዩ የትምህርት ዘርፎች ያሰለጠናቸውን ተማሪዎች አስመርቋል፡፡ በቴክኒክና ሙያ ዘርፍ 4066፣ በቅድመ ምረቃ(የመጀመሪያ ዲግሪ) 2299፣ በድህረ ምረቃ (በሁለተኛ ዲግሪ) 79 ተማሪዎችን በአጠቃላይ በድምሩ 6454 ተማሪዎችን በሚሊኒየም አዳራሽ ያስመረቀ ሲሆን፣ ለመጀመሪያ ጊዜ በማስተርስ ፕሮግራም ተማሪዎቹን ማስመረቁንም በዕለቱ የኮሌጁ ባለቤትና ዋና ስራ አስኪያጅ አቶ ሞገስ ግርማ ገልፀዋል፡፡ ኮሌጁ ከተመሰረተ 16 ዓመታትን አስቆጥሯል፡፡ በተጨማሪም ኮሌጁ የራሱን ህንፃ አስገንብቶ እየሰራ መሆኑን፤ በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና በ8 ዘርፎች በአካውንቲንግ፣ በሂዩማን ሪሶርስ ማኔጅመንት፣ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ ሴክረተሪ ኤንድ ኦፌስ ማኔጅመንት፣ በኤሌክትሮኒክስ፣ በማርኬቲንግ፣ በሌጋል ሰርቪስና፣ በፐርቼዚንግ የቅድመ ምረቃ የመጀመሪያ ዲግሪ ፤በ4 ዘርፎች ቅድመ ምረቃ በርቀት፤ በ3 ዘርፎች ድኅረ ምረቃ፤ 2ኛ ዲግሪ በ2 ዘርፎች አሰልጥኖ ማስመረቁን በምርቃት ስነ ስርዓቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡



# የኢጄቶ ጨካኝ ልብ!

## የክልል ጥያቄ፣ የዘር ጥላቻ፣ ሞት፣ ንብረት ውድመት፣ ዘረፋ፣ ኮማንድ ፖስት በደቡብ ኢትዮጵያ

**በዝግጅት ክፍሉ**

ብዙ አመታትን ተሻግሮ ዛሬ ላይ የደረሰው የሲዳማ ብሔር የክልልነት ጥያቄ በሰከነና ህግን በተከተለ አግባብ የታሰበውን ግብ ይመታል ተብሎ ሲጠበቅ ደም መፋሰስን ወዳስከተለ ግጭትና ሁከት አምርቷል፡፡ አሁን ሁሉም የሲዳማ ዞን ወረዳና የገጠር ቀበሌዎች እጅግ አስፈሪ መልክን ተላብሰው አደገኛ ቀጠና ለመሆን በቅተዋል፡፡

ሰሞኑን በብዙ ሲነገርና በሰፊው ሲተነተን እንደቆየው የሲዳማ ብሔር “ክልል እንሁን” ጥያቄ ህገ መንግስታዊ መሰረት ያለውና ለአመታት የህዝብ ጥያቄ ሆኖ የኖረ ነው፡፡ የዞኑ ህዝብ ይህን ፍላጎቱን በተለያየ መንገድ ሲገልፅና በአደባባይ ሰልፍ ጭምር ጥያቄውን ሲያስተጋባ ነው የቆየው፡፡ ጥያቄው ከታዋቂ የብሔሩ ተወላጆች አንስቶ በፓርቲ እስከተደራጁ በብሔሩ ስም የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶች ድረስ በህጋዊና ሠላማዊ መንገድ ሲቀርብ የኖረ ከመሆኑም ባሻገር ሰፊው የሲዳማ ህዝብም አደባባይ ወጥቶ የመንግሥትንና የክልሉን አስተዳደር ይሁንታ የጠየቀበት ነው፡፡ የጥያቄውን ለአመታት መልስ ማጣት ተረድቶ ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት የፈቀደ አካል አለመኖሩ ግን የነበረውን ሰላማዊና ህጋዊ መልክ እንዲቀይር ገፍቶታል፡፡ አሁን እየሆነ ወደሚገኘው አሳዛኝና አስደንጋጭ እውነታም አድርሶታል፡፡



የሲዳማ ወጣቶች የተደራጁበት ኢጄቶ የሚባለው የህዝባዊ ንቅናቄ ቡድን ለዘመናት መልስ አጥቶ ሲንከባለል የኖረውን ጥያቄ በአዲስ ጉልበትና የእኔነት ስሜት መልስ እንዲያገኝ ጠንካራ እንቅስቃሴ ከጀመረ ወራት ተቆጥረዋል፡፡ ሀገሪቱ በስርዓት ለውጥ ውስጥ የመክረሚ ሁኔታ የጥያቄውን መልስ በአፋጣኝ ለማበጀት ምቹ ሁኔታን አለመፍጠሩ ተደጋግሞ ቢነገርም የሁኔታዎችን አካሄድና የህዝቡን እልህ ውስጥ መሆን መረዳት የነበረበት የክልሉ መንግሥትም ምንም ዓይነት አማራጭ መፍትሔ አለማበጀታቸውና የማረጋጋት ስራ አለመስራታቸው አሁን ለተገባበት ውጥንቅጥ በመንስኤነት ይጠቀሳል፡፡

የሲዳማ ወጣቶቹ ሀይል (ኢጄቶ) ለዘመናት ሲንከባለል ለቆየው የብሔሩ የክልልነት ጥያቄ የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት አፋጣኝ መፍትሔ እንዲሰጡ በመሻት የህዝቡን እንቅስቃሴ በበላይነት መምራት ከጀመረ በኂላ ከአጠቃላይ ሁኔታዎች አንፃር ነገሮች ወደየት እያመሩ መሆናቸውን በቀላሉ መረዳት ይቻል ነበር፡፡ ከወራቶች በፊት ኢጄቶና ቄሮ በሀዋሳ ሲዳማ ባህል አዳራሽ ባደረጉት የጋራ ስብሰባ የቄሮ መሪው ጃዋር መሀመድ “ሲዳማ ፍላጎቱን በሰላማዊ ብቻ ሳይሆን በጉልበቱም ማስከበር አለበት” ብሎ አዳራሽ ሙሉ ህዝብ ሲያስጨበጭብ የረጨው መርዝ ውሎ አድሮ ምን እንደሚያስከትል እየታወቀ ዝም መባሉ ይኸው ዋጋ አስከፍሏል፡፡ በተለይም በሐዋሳ ከተማ በሳምንት ልዩነት ወንዶችና ሴቶች ለየብቻ ያደረጓቸው ሰላማዊ ሰልፎች ቀጥሎ ምን ሊፈጠር እንደሚችል በበቂ ፍንጭ የሰጡ ነበሩ፡፡ ነገሩን በእኔነት ስሜት ለማየት የፈቀደና ምላሽ መስጠት ህዝብን ማክበር መሆኑን የተቀበለ የአገር አስተዳር አለመኖሩ ግን ይኸው ደም መፋሰስ እንዲሰፍን፣ አገር ሰላም አጥታ እንድትታመስ ዕድል ፈጥሯል፡፡ ኢጄቶ በ11/11/11 የሲዳማ ነፃነት ቀንን በራሳችን ፈቃድ እናውጃለን ብሎ▶

ፍላጎቱን ከሠላማዊና ህጋዊ ጥያቄ ወደ ጉልበት ሲወስድ ቀነ ገደቡ እስኪደርሱ ማንም ምንም ለማድረግ ሲሞክር አለመስተዋሉም በራሱ አስተዛዛቢ ነው፡፡ ሀገር በእነማን እየተመራ መሆኑን እንድንረዳም ዓይነተኛ ማሳያ መሆን የሚችል ነው፡፡ ይሁንና ኢጄቶም በመጨረሻው ሰዓት ራሱን ወደ ጥፋተኝነት መረብ ወርውሮ እጆቹን የወንጀል ባህር ውስጥ ነክሯል፡ ፡ ያን የመሠለ፤ ያውም ህገመንግስታዊ ድጋፍ ያለውን የሕዝቦችን ሠላማዊ የመብት ጥያቄ በስተመጨረሻ አበለሻሽቶታል፡፡ መሆን የማይገባው ሁሉ እንዲሆን በር በመክፈቱ ራሱን ለወንጀል ተጠያቂነት ዳ ርጓል፡፡ በገናና ስሙ እና በነበረው ክብር ላይም ቀዝቃዛ ውሃ ቸልሶበታል፡፡

አሁን መላው የደቡብ ክልል በኮማንድ ፖስት ስር ሆኖ ሁሉም ዞኖች በመሣሪያ አፈሙዝ የሚጠበቁ ሆነዋል፡፡ የክልሉ መንግሥት ንብረት የሆነው ደቡብ ቴሌቪዥን በ“ሰበር ዜናው” እንዳስታወቀው የክልሉ መንግሥት በጠየቀው መሰረት ሁሉም የደቡብ ክልል ዞኖች እና ከተሞች በፌደራል የመከላከያ ሰራዊት በሚመራ ጊዜያዊ ዕዝ (ኮማንድ ፖስት) ቁጥጥር ስር እ ንዲሆኑ ተወስኖ ይህም ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

የክልሉ መንግሥት ባወጣው መግለጫ እንዳለው የክልሉ የፀጥታ መዋቅር የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥ የሚችልበት አቅሙ ደካማ መሆኑና ተቋማቱ በየራሳቸው የክልል አካባቢያዊ አጀንዳዎች የተተበተቡ በመሆናቸው ወታደራዊ ዕዙ የክልሉን ሰላም፣ ፀጥታ፣ ደህንነትና የሕግ የበላይነትን ለማስከበር ስልጣን ተረክቧል፡፡

**...የኢጄቶ መሪው በላንድ ክሩዘር መኪና ለማምለጥ መሞከሩና ወላጅ አባቱ የስብከተወንጌል አገልግሎት በሚሰጡበት የፕሮቴስታንት ቤተ እምነት ተደብቆ መያዙን የደረሰን መረጃ ያመለክታል...**

## በሲዳማ ዞን ከተሞች ምን ሆነ?

ኢጄቶ “የሲዳማ ህዝብ የክልልነት ጥያቄ በራሱ በህዝቡ የሚወሰንበት ቀን በ11/11/11 ነው” ብሎ ባስቀመጠው ቀነ ገደብ መሰረት ይህ ዕለት የሆነው ነገር ሁሉ መነሻ ነው፡፡ በዕለቱ ማለዳ ላይ የሐዋሳ ወጣቶችና የሀገር ሽማግሌዎች በባህላዊው የጨምበላላ በዓል ማክበሪያ ቦታ (ጉዱማሌ) ተገናኝተው ክልል መሆናቸውን በይፋ ለማወጅ ሲጠራሩ ቀድሞ ወደ ከተማዋ የገባው የፌደራልና የመከላከያ ወታደራዊ ሀይል ቦታውን በመቆጣጠር በዚህ ስፍራ መሰባሰብ እንደማይቻል ክልከላ አድርገዋል፡፡ ይህንኑ ተከትሎም የከተማዋ ወጣቶች በዚህ ሀይል ላይ ተቃውሞ ወደማሰማት ተሻግረው አሞራ ገደል በተባለው አካባቢም የመከላከያ አባላት ላይ ጥቃት ሰንዝረዋል፡፡ የፀጥታ ሀይሉ የአፀፋ እርምጃ መውሰድ በመጀመሩም ነገሮች በፍጥነት መልካቸውን ቀይረዋል፡፡

በተለይ የሲዳማ ተወላጆች በብዛት በሚኖሩባቸው አቶቴ፣ ዲያስፖራ፣ አዲሱ ገበያ፣ ዶሮ እርባታ እና ወልደ አማኑኤል አደባባይ ተብለው በሚታወቁ አካባቢዎች የተሰባሰቡ የሲዳማ ተወላጆች ተቃዋሞ ካስነሱና የፀጥታ ሀይሉም እርምጃ በመውሰድ ሰልፈኛውን በትኖ ሰላም የማስፈን ተልዕኮውን መወጣት ከጀመረ በኋላ ቀውሱ፣ ነውጡ፣ ረብሻውና የጥፋት ዘመቻው ወደ ሌሎች የዞኑ ከተሞች ተዛምቷል፡፡

በአብዛኛዎቹ የዞኑ ከተሞች ረብሻና ዘርን መሰረት ያደረገ ጥቃት መሰንዘር የተጀመረው በተመሳሳይ ሰዓት ከማለዳው 4፡00 አካባቢ ነው፡፡ ሀዋሳ ላይ በፀጥታ ሀይሎች በጥይት ተመትተው የሞቱና የቆሰሉ ሰዎች መኖራቸው እንደተሰማ ነው ሁከቱ ወደሌሎቹ አካባቢዎች የተዛመተው፡፡ እንደ አንዳንዶች ግምት ከሆነ ሐዋሳ ላይ ይከሰታል የተባለው ጥፋት በተጋነነ መልኩ የተገመተ በመሆኑ መንግሥት የበዛ ሀይሉን ወደዚህ ከተማ ማድረጉ በሌሎች የዞኑ አካባቢዎች የደረሰውን ጉዳት ቀድሞ መከላከል እንዳይቻል ክፍተት ፈጥሯል፡፡ የሐዋሳ ተቃዋሚ ሀይሎች የከተማዋን በወታደር መወጠር እንደተረዱም ጉዳዩን ወደሌሎቹ ከተሞች አሻግረውታል፡፡ በመሆኑም ወደ ይርጋለም፣ ሞሮቲ፣ ጭኮ፣ ለኩ፣ ተፈሪ ኬላ፣ ወንዶ ገነት፣ አለታወንዶ እና ሀገረ ሰላም የተዛመተው ሁከት እስከ ገጠር ቀበሌዎች ዘልቆ ብዙሃንን ለሞትና ንብረት ውድመት ዳርጓል፡፡

ሁከቱን ያስነሱትና ለንፁሐን ሞትና ንብረት ውድመት መንስኤ የሆኑት የዞኑ ተወላጆች በሰፊው በተጠናና በተደራጀ መንገድ ጥፋቱን እንደፈፀሙ ከሁኔታዎች መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህ ውስጥ የከተማ አስተዳደርና የመንግሥት የሥራ ሀላፊዎች እጅ እንዳለበትም ያስታውቃል፡፡ ከሌሎች አካባቢዎች የመጡ ወጣቶች ከየከተማው ጥቂት ነዋሪዎች ጋር በመሆን ስም ዝርዝር ያለበት ወረቀት ይዘው በተፃፈው መረጃ መሰረት በሌሎች ብሔር ተወላጆች ህይወትና ንብረት ላይ ያሻቸውን ሲፈፅሙ መታየታቸው በርግጥም ከዚህ የተደራጀ ወንጀል ጀርባ እነማን እንዳሉበት ለመገመት አይከብድም፡፡

በአለታ ወንዶ የሌላ ብሔር በሆኑ ኢትዮጵያውያን ላይ በተከፈተ የጥቃት ዘመቻ ብዙ ጉዳት ደርሷል፡፡ በተለምዶ አረብ ሰፈርና መናኸሪያ በሚባሉት አከባቢዎች የጨርቃ ጨርቅና ሌሎች ቁሳቁስ መሸጫ ሱቆች እንዲሁም ከመናኸሪያው ጀርባ ያሉ መኖሪያ ቤቶች እንዲቃጠሉና ንብረታቸው እንዲወድም ተደርጓል፡፡ የከተማ አስተዳሩ ሁለት መኪኖችና የዱቄት ፋብሪካ ተቃጥለዋል፡ ፡ ሰዎች ተደብድበው ለሞትና አካል ጉድለት ተዳርገዋል፡፡ ጥቃቱን የሸሹ ብዙሃንም በገዛ አገራቸው ስደተኛ ሆነዋል፡፡

በይርጋለም ለብዙ የውጭ ሀገራት ቱሪስቶች መዳረሻ ሆኖ ለአገር ኢኮኖሚ ጠቃሚ የውጭ ምንዛሪ ያስገኝ የነበረው አረጋሽ ሎጅ ተቃጥሏል፡፡ የክልሉ ከንቲባ መኪኖች፣ የበጎ አድራጎ ድርጅት ንብረቶች እና ክልል እንዳይሰጠን አድርገዋል የሚል ጭፍን ምክንያት ባቀረቡባቸው የሌላ ብሔር ተወላጆች ንብረት ላይ የበዛ ጉዳት አድርሰው በሰዎቹም ላይ አካላዊ ጥቃት ፈፅመዋል፡፡

አሁን ዘግይተው እየወጡ ካሉ መረጃዎች ለመረዳ እንደሚቻለው ከሆነ ደግሞ እጅግ የበዛው ጉዳት የደረሰው ከከተማ ይልቅ በገጠር ወረዳና ቀበሌዎች ነው፡፡ በዞኑ ገጠራማ አካባቢዎች የሚኖሩ የሌላ ብሔር ተወላጆች ቤታቸው ተቃጥሏል፡፡ የቤት እንስሶቻቸው ተዘርፈዋል፡፡ በተደራጁት ወጣቶች ከብቶቻቸው ታርደው ተበልተዋል፡፡

ቤተ ዕምነቶችና የሌላ ብሔር ተወላጆች የሲዳማ ጥያቄ መልስ እንዳያገኝ ገንዘብ አሰባስበው ሰጥተዋል የሚል እጅና እግር የሌለው ተባራሪ ወሬ መናፈሱ በሌላ ብሔር ተወላጆችና በቤተ እምነቶች ላይ ጥቃት እንዲከፈት ምክንያት መሆኑ እየተነገረ ሲሆን በተለይም በሀገረ ሰላም ከተማ የሚገኙ ሶስት ቤተ ክርስቲያናት ተቃጥለዋል፡፡ በሌሎች ሶስት አብያተ ክርስቲያናት ላይ ደግሞ የንዋያተ ቅድስት ዝርፊያ ተፈፅሟል፡፡ በቃጠሎ ሙሉ በሙሉ የወደሙት የዶያ ቅዱስ ሚካኤል ቤ/ክ፣ ጌታማ ገብረ ክርስቶስ እና ጭሮኒ ቅዱስ አማኑኤል ቤ/ክርስቲያን ሲሆኑ የተዘረፉት ደግሞ ሀገረ ሰላም ደብረ ገነት ቅድስት ኪዳነ ምህረት፣ ሎዳ ቅዱስ ገብርኤል እና ጭሬ አማኑኤል ቤ/ክ ናቸው፡፡

በሲዳማ ዞን ልዩ ልዩ አካባቢዎች በተደራጁ ወጣቶች የተከፈተው ረብሻና ንፁሃንን የማጥቃት ዘመቻ እስካሁን በትክክል ቁጥሩ ይህ ነው ተብሎ ባይገለፅም ከ50 በላይ የሚሆኑ ሰዎችን ለሞት፣ ከ120 በላይ የሚሆኑትንም ለከፍተኛ አካላዊ ጉዳት ሣይዳርግ እንዳልቀረ ይገመታል፡፡ ሐሙስ ዕለት የተከፈተው የጥቃት ዘመቻ እስከ ሰኞ የዘለቀባቸው አካባቢዎች መኖራቸው ሲጠቆም በገጠር ወረዳና ቀበሌዎች የደረሰውን የጉዳት መጠን ለማወቅ ምንም ዓይነት የመረጃ አማራጭ የሌለ መሆኑ አዳጋች አድርጎታል፡ ፡ ምናልባትም ከቀናት በኋላ ሲታወቅ የጉዳቱ መጠን ከሚባለው በዕጥፍ ሊጨምር እንደሚችል ይታሰባል፡፡

አሁን ሁሉም የሲዳማ ዞን አካባቢዎች በወታደራዊ ዕዝ (ኮማንድ ፖስት) ሥር እንዲሆኑ በመደረጉ በአብዛኛው አንፃራዊ ሰላም እየሰፈነ ቢሆንም አጥፊዎቹን በቁጥጥር ሥር የማድረግና በህግ የማስጠየቅ ተግባር ግን ብዙ ይቀረዋል፡፡ አብዛኞቹ ጥቃት አድራሾች ከአጎራባች ቀበሌዎች የመጡና በነዋሪዎች የማይታወቁ መሆናቸው ተጠያቂዎችን የማደን ሥራውን ከባድ እንደሚያደርገው ይጠበቃል፡፡

ይሁንና የኢጄቶ መሪውን ጨምሮ በመቶዋች የሚቆጠሩ የወንጀሉ ተሳታፊዎች በቁጥጥር ስር ውለዋል፡፡ የኢጄቶ መሪው በላንድ ክሩዘር መኪና ለማምለጥ መሞከሩና ወላጅ

ቀሪውን በገጽ 27 ይመልከቱ

# “ደቡብ”

## (ከፋ፣ሸካ፣ጎፋ፣ጋሞ፣ሲዳማ፣ቤንች፣ሃዲያ፣ጉራጌ፣ወላይታ፣ጋሞ...)

# የክልልነት ጥያቄዎችና የደኢህዴን ውጥረት

መላክ ቢ.

በቁጥር ከ 56 የሚልቁ ብሔር ብሔረሰቦች መኖሪያ የሆነው የደቡብ ክልል ከተመሰረተ ገና 24 ዓመቱ ነው። በዚህ ክልል ውስጥ ያሉት እና “ዞን” በተባለ የአስተዳደር መዋቅር ውስጥ ተጠቃልለው የሚገኙት ብሔሮች ዳግማዊ አጼ ምኒሊክ የዛሬዋን ኢትዮጵያ ቅርጽ ለማስያዝ ባካሄዷቸው ጦርነቶች ከመገበራቸው (ወደ ኢትዮጵያ ከመጠቃለላቸው) ቀደም ብሎ አብዛኞቹ “ራሳችንን የቻልን ፣ በንጉስ የምንተዳደር ሃገራት ነበርን” ሲሉ ቀደምት የሃገረ መንግስትነት ታሪካቸውን እየጠቀሱ ይናገራሉ። ሲዳማ፣ ወላይታ እና ካፋን የመሳሰሉ ብሔሮች ለዚህ አይነት ‘የቀድሞ ሃገርነት’ ትርክት ምሳሌዎች ናቸው።

ከአዲሲቷ ኢትዮጵያ ምስረታ በኋላ ከእነዚህ ብሔሮች ውስጥ በህዝብ ብዛትም ይሁን በቀደመ አስተዳደራዊ መዋቅር ታሪካቸው ላቅ ያሉት እየተመረጡ ሲደራጁ ፣ በስራቸው በቁጥር አናሳ የሆኑና በመልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ቅርብ የሆኑ ብሔሮችን እንዲያጠቃልሉ እየተደረገ በየዘመኑ መንግስቱ በተሰጣቸው መዋቅር ስም ውስጥ የኢትዮጵያ አካል እንደሆኑ ቀጥለዋል። በአጼ ሃይለስላሴ ዘመነ መንግስት በጠቅላይ ግዛት እና በአውራጃ ሲደራጁ በደርግ ዘመነ መንግስት ደግሞ በክፍለሃገር ተደልድለው መዋቅሩንም መጠሪያቸው አድርገው ኖረዋል።

> ***ደቡብ ክልል በመንግስት ተጠፍጥፎ የተሰራ አይደለም” ብለዋል... የክልሉ ምሁራን ያለመንግስት ተጽዕኖ ደቡብ ክልል እንዲመሰረት ተስማምተው የተመሰረተ መሆኑም [ተረጋግጧል]...አብዛኛው ህዝብ አሁን ያለው የክልል አደረጃጀት ይቀጥል ብሏል...***

1983 ዓ.ም የደርግ መንግስት ሲወድቅ እና ኢህአዴግ ስልጣን ሲይዝ ከ1966ቱ የተማሪዎች ንቅናቄ በተመዘዘው እና መሰረታዊ ትርክት በነበረው የስታሊኒዝም አስተምህሮ ‘ኢትዮጵያ የብሄር ብሄረሰቦች እስር ቤት ናት’ የሚለው የብሄር ትርክት መነሻ ሆኖ የሃገሪቱ አስተዳደር መዋቅር ከአሃዳዊ ወደ ፌዴራላዊ አወቃቀር የሚቀየርበት መንገድ ተጀመረ። ከ1984 እስከ 1987 ድረስ በሃገሪቱ ውስጥ እንደህገመንግስት ሆኖ ያገለገለው የሽግግር ወቅት ቻርተር በደርግ ዘመን የነበረውን አስተዳደራዊ መዋቅር በማፍረስ ኢትዮጵያን በ14 ክልሎች ከፈላት።በዚህ ወቅት በደቡባዊ ኢትዮጵያ የሚገኙት 56 ብሄር ብሄረሰቦች ከክልል 7 እስከ ክልል 11 ድረስ ባሉ ክልሎች ተካተቱ።

በ1987 ዓ.ም የኢፌዲሪ ህገመንግስት ከመጽደቁ ቀደም ብሎ በነበሩት ጊዜያት ራሱን በአራት ብሔራዊ ድርጅቶች ጥምረት ግንባር አድርጎ ያዋቀረው ኢህአዴግ ለየብሔራዊ ድርጅቶቹ የሚያስተዳድሩትን ክልል አስቀድሞ ደልድሎ ነበር። ለሕወሓት ትግራይን፣ ለብአዴን አማራን፣ ለኦህዴድ ኦሮሚያን ሲደለድል 56 ብሄር ብሄረሰቦችን በአንድ በመጨፍለቅ የደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ደኢህዴን) የተባለ የግንባሩ አባል ፓርቲ እንዲያስተዳድራቸው ወሰነ።

የብሔር ፌዴራሊዝምን በኢትዮጵያ ማስፈን መሰረታዊ ዓላማው አድርጎ የተነሳው ኢህአዴግ በሽግግር ወቅት ባወጣው አዋጅ ቁጥር 719/84 ኢትዮጲያን በአስራ አራት ክልሎች ከፍሎ አቋቋመ። ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በዚህ አዋጅ ተዋቅረዉ ከነበሩት አስራ አራት ክልሎች መካከል አምስቱ በደቡብ የሚገኙ ሲሆን፤ ከክልል 7 እስከ ክልል 11 የነበረውን አከላለል የያዙ ነበሩ። በዚህ አወቃቀር በደቡብ የነበሩ 56 ብሔረሰቦች በ5 ክልል ውስጥ ተጠቃለሉ። ኢህአዴግ ይህንን ክልል አንድ ለማድረግ የቀደመ ዕቅድ ነበረውና በ1985 ዓ.ም በሃዋሳ ከተማ በሚያደርጋቸው ስብሰባዎች የደቡብ ክልል አንድ እንዲሆን ለማድረግ ከአምስቱ የደቡብ ክልሎች አመራሮች ጋር ውይይት ያካሂድ ነበር። ያም ሆኖ ጥቂት የክልልቹ ባለስልጣናት ይህንን እቅድ በሙሉ ልብ ተቀብለውት ነበር ለማለት ያዳግታል።አብዛኞቹ በተጽዕኖ ስር ሆነውም ቢሆን ይህንን ዕቅድ አምርረው ተቃውመው እንደነበር ሰነዶች ያመላክታሉ። የኢፌዲሪ ህገመንግስት በረቂቅ ሂደት ላይ እያለ በተካሄዱ ውይይቶችም ኢህአዴግ አስቀድሞ የያዘው የአንድ ክልልነት አቅጣጫ በህገመንግስቱ ውስጥ መካተቱ ያላስደሰታቸው የየክልሉ ተወካዮች ሊመጣ ያለውን አወቃቀር አምርረው በመቃወም የየራሳቸውን የውሳኔ ሃሳብ በልዩነት ማስቀመጣቸውም ይነገራል።

ከክልል 7 እስከ ክልል 11 ድረስ ባሉ አምስት ክልሎች የተዋቀሩት የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች የያዙትን አስተዳደራዊ መዋቅር ይዘው የዘለቁት እስከ 1987 ዓም ማለትም የሽግግር ወቅት ቻርተሩ በኢፌዲሪ ህገመንግስት እስኪተካ ድረስ ብቻ ነበር። የኢፌዲሪ ህገመንግስት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት አባላት የሆኑት ክልሎች 9 መሆናቸውን ሲደነግግ የደቡብ ብሔሮች ከዚህ ቀደም ሲተዳደሩበት የነበረው 5 ክልል ተጨፍልቆ ወደአንድ ክልል እንዲጠቃለል እና ስሙም “የደቡብ ኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል” ተብሎ እንዲጠራ ተደረገ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የደቡብ ብሄሮች ዋነኛ አጀንዳ “ራሳችንን ችለን እንተዳደር፣ የአስተዳደር መዋቅሩ ይህንን ሁሉ ብሄር በአንድ ላይ ጨፍልቆ በአቅጣጫ ስም መጥራቱ ተገቢ አይደለም ወዘተ” የሚል ተቃውሞ ሆነ። ነገር ግን የኢህአዴግን መዋቅር የተቃወሙና አንድም “ቀድሞ የነበረን ክልልነት ይመለስልን” ያሉ የተጨፈለቁ ክልሎች ብሔሮች ፣ ሌላም “ራሳችንን ችለን ክልል እንሁን” የሚል ጥያቄ ያነሱ ከዚህ ቀደም ክልል ያልነበሩ ብሔሮች ተወካዮች ሁሉ በከባድ ተጽዕኖ ስር ከመውደቃቸው ባሻገር ጸረ ልማትና ጸረ አንድነት አቀንቃኝ ተብለው መፈረጅ እጣቸው ሆነ። ይህ ጥያቄ ውስጥ ውስጡን ሲብላላ እና በተገኘው መድረክ ሁሉ የተቃውሞ መቀስቀሻ ምክንያት ሆኖ ኖሮ በ2010 ደቡብ አንድ ክልል ሆኖ መተዳደር ከጀመረ ከ21 ዓመታት በኋላ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ለውጥ ሲመጣ የክልልነት ጥያቄ አዲስ ጥያቄ መስሎ ፈንድቶ ወጣ። ባለፈው አንድ አመትም በኢትዮጵያ የፖለቲካ ተቃውሞ እና ቅሬታ ምህዳር ላይ የደቡብ ክልል “ራሳችንን ችለን ክልል እንሁን” ባሉ 11 ብሔር ብሔረሰቦች ጥያቄ ተሞላ። በለውጡ ዘመን ጠንካራ የፖለቲካ ጥያቄ ከሆኑት መካከል ዋናውም የደቡብ ጉዳይ ሆነ። ►

## ጥያቄዎቹና ረብሻው

በአሁኑ ወቅት በደቡብ ክልል የሚገኙና የክልልነት ጥያቄ ያቀረቡ ብሄሮች ቁጥር 11 ደርሷል። ሲዳማ፣ ወላይታ፣ሃዲያ፣ካፋ፣ጉራጌ፣ጋሞ፣ከምባታ፣ሸካ፣ጋሞ፣ቤንች እና ጎፋ ዞኖች "ክልል እንሁን" ብለው ጠይቀው ይህንኑ የክልልነት ጥያቄ ተገቢነት የየዞኖቹ ምክር ቤቶች አጽድቀውና በሂደቱ መሰረት ወደክልሉ ምክር ቤት አቅርበው፣ በክልሉ ምክር ቤት በህገመንግስቱ በተደነገገው መሰረት ጥያቄው በቀረበ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ህዝበ ውሳኔ እንዲደራጅ የሚጠብቁ ናቸው። ነገር ግን የክልሉ ምክር ቤት ከየዞኖቹ የመጣለትን ጥያቄ ተቀብሎ ምንም አይነት ህዝበውሳኔ ሳያደራጅ እና ጉዳዩንም አጀንዳ አድርጎ ሳይወያይ በመቀመጡ ሳቢያ ሁሉም ሊባል በሚችል መልክ ዞኖቹ ውስጥ ተቃውሞ እና ቅሬታ ተቀስቅሷል። በዚህ መካከል ወደ 60 ዓመታት ይጠጋዋል የሚባለው የሲዳማ አርነት ንቅናቄ (ሲአን) ተብሎ በሚጠራው ፓርቲ የሚመራው የሲዳማ የራስን በራስ ማስተዳደር ትግል እየመረረ መጥቶ ነበር።

ኢህአዴግ ሲኣንን እና አባላቶቹን ሲያድን እና ሌሎች የክልል እንሁን ጥያቄ የሚያነሱ አካላትን በሰበብ በአስባቡ ሲያዋክብ ቢቆይም በራሱ ውስጥ በተካሄደ ትግል በተፈጠረው የፖለቲካ ክፍተት (ለውጥ) ተገንነት እነዚህ ጥያቄዎች ከቀድሞው በበለጠ እና በጠነከረ መልኩ ጎልተው ወጡ።

የረጅም ዘመን ራስን በራስ ማስተዳደር ጥያቄ ታሪክ ያለው ሲዳማ በኢህአዴግ ዘመን ያቀረበው የክልልነት ጥያቄ በዞኑ ጸድቆ ለክልሉ ምክር ቤት የቀረበበት ጊዜ (ሃምሌ 11 ቀን 2010) በህገመንግስቱ መሰረት አንድ አመት የሚሞላው ሃምሌ 11 ቀን 2011 በመሆኑ የክልሉ ወጣቶች ንቅናቄ የሆነው ኢጄቶ የተባለ ቡድን "ደኢህዴን ጥያቄያችንን ተቀብሎ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ህዝበውሳኔ ስላላደራጀልን በ11/11/2011 በራሳችን ጊዜ ክልልነታችንን እናውጃለን" በማለት ማስጠንቀቂያ ሰጠ። ከዚህ በቀደመው ጊዜ ይኸው የወጣቶች ቡድን የክልሉ መሪ ፓርቲ እና የኢህአዴግ እህት ድርጅት የሆነው ደኢህዴን በሃዋሳ ከተማ ላይ ስብሰባ በማድረግ ላይ እያለ "ፓርቲው አይወክለንም፣ ጥቅማችንን አሳልፎ ሸጧል፣ ጠላታችን እንጂ ለኛ የቆመ አይደለም" በሚል ተቃውሞ ስብሰባውን አዳራሽ ድረስ ገብቶ በትኖታል። የክልሉ መንግስት (መዘጋጃ) ውስጥ ሲውለበለብ የነበረውን የድርጅቱን ባንዲራም አውርዶ በምትኩ የሲዳማን አርማ ሰቅሏል። በዚህ ሳቢያ ደኢህዴን ያካሄደው ስብሰባ ከመቋረጡ በተጨማሪ ከደህንነት ስጋት ጋር በተገናኘ ፓርቲው ከዚያን ጊዜ ወዲህ በክልሉ ውስጥ ምንም አይነት ስብሰባ አላካሄደም።

ኤጀቶ ምንም እንኳን ኢመደበኛ ሃይል ወይም ቡድን ቢሆንም በኦሮሚያ እንዳለው ቄሮ፣ በአማራ እንዳለው ፋኖ እና በወላይታ እንዳለው ዬላጋ እንዲሁም በከፋ እንዳለው ጉርማሾ የወጣቶች ቡድን የህዝቡን ጥያቄ በማንሳት ከመንግስት ሃይሎች ጋር የሚፋጠጥ እና የሚፋለም ቡድን በመሆኑ የሲዳማ ህዝብም በቀና የሚመለከተውና የሚደግፈው አካል ነው። ይህ ቡድን "ክልልነታችንን በራሳችን እናውጃለን" በማለት የሰጠው የመጨረሻ ቀን ከመቃረቡ አስቀድሞ የደኢህዴን የስራ አስፈጻሚና ማዕከላዊ ምክር ቤት ስብሰባ አካሂዶ በዞኖች በቀረቡ የክልል እንሁን ጥያቄዎች ላይ የተድበሰበሰ እና ምንም የማይገልጽ መግለጫ ማውጣቱ ፣ ምርጫቦርድም በመጨረሻው ሰዓት በቀሩት አምስት ወራት ውስጥ የህዝበውሳኔ ለማደራጀት የሚያስፈልጉ ቅድመሁኔታዎችን ዘርዝሮ ለክልሉ ምክር ቤት መላኩና በዚህ ጉዳይ ላይ ደኢህዴን ምንም አይነት ቃል ባለመተንፈሱ የፈጠረው ተቃውሞ ቁጣ ተደምሮበት በዕለቱ ሃዋሳ ከተማ እና አካባቢዋ በከፍተኛ የጸጥታ ችግር ውስጥ ወደቁ። ብዙዎች ኢጄቶን በራስወዳድነት እና "የኔ" በሚል አስተሳሰብ ብቻ የተቃኘ ቡድን ነው በማለት ይከስሱታል። ለዚህም የሚያነሱት ምክንያት ከዚህ ቀደም ለውጡ እንደመጣ ሰሞን በሃዋሳ ከተማ በሚኖሩ የሌላ ብሔር ተወላጆች በተለይም የወላይታ ብሔሮች ለይ ጥቃት በመሰነዘር ከፍ ያለ ጉዳት ማድረሱን ነው። የሲዳማ ብሔር ተወላጆች ለዚህ ጥቃት ተጠያቂዎቹ ኢጄቶዎች ሳይሆኑ እነሱን መስሎና ተቀላቅሎ የገባ ጸረ ሰላም ሃይል እንደሆነ ይናገራሉ።በማህበራዊ ሚዲያ የተለቀቁ አንዳንድ ዘግናኝ ምስሎች ላይ እንደሚታየው የወላይታ ተወላጆች ላይ ከፍተኛ ጥቃት ደርሷል። በብሔራቸው ሳቢያ በቁማቸው ተደብድበው የተገደሉ፣ መሬት ለመሬት እየተጎተቱ የሞቱ እና ከነነፍሳቸው እያሉ እሳት የተለኮሰባቸው የወላይታ ወጣቶች ብዙ ናቸው። ይህ ጥቃት በብዙ ተወግዞ እና አጥፊዎቹ እንዲቀጡ ጥያቄ ቀርቦ ምላሹ ሲጠበቅ በድጋሚ በሁለተኛ ዙር በዚሁ ሃዋሳ በተነሳ ረብሻ አሁንም ይኼው የወጣቶች ቡድን ተጠያቂ ሆኖ የቀረበበት ጥቃት ተከናውኗል። በጊዜው በወጣቶቹ (አንዳንዶች ከበስተጀኋላቸው ሌላ ሃይል አለ ይላሉ) በክልሉ የሚኖሩ የጉራጌ እና አማራ ተወላጆች ላይ ጥቃት ደርሷል። አብያተ ክርስቲያናት ተቃጥለዋል። ንብረት ተዘርፏል። ግለሰቦች ቆስለዋል። የሃዋሳውን ጨምሮ በአጠቃላይ በሲዳማ ዞን በሚገኙ ወረዳዎች ውስጥ በነበረው ብጥብጥ 21 ሰዎች ህይወትም አልፏል ተብሏል። ይህንን ተከትሎ መላው ደቡብ ዞን ከነልዩ ወረዳዎች እና ከተሞቻቸው ጭምር የጸጥታው ጥበቃ በጊዜያዊ የጸጥታ እዝ ስር እንዲሆን ተደርጓል።

## "ደኢህዴን በእሳት ላይ"

በሲዳማ ይህን መሰል ረብሻ ቢቀሰቀስም በሌሎቹ ዞኖች የተካሄዱ ሰላማዊ ሰልፎች ግን የክልልነት ጥያቄን ከማቅረብ ባሻገር ደኢህዴንን ከማውገዝ እና አይወክለንም ከሚል ተቃውሞ የዘለለ አልነበረም። ክልሉ በኮማንድ ፖስቱ ስር እስኪሆን ድረስ በወላይታ፣ በካፋ፣ በሃዲያ፣ በጉራጌ፣ ወዘተ ዞኖች በተከታታይ ሲካሄዱ የቆዩት ተቃውሞ ሰልፎች ለምን ደኢህዴን ለይ አነጣጠሩ? የሚለውን ጥያቄ ከየዞኑ በተገኙ መረጃዎች እዚህ ላይ ቆም ብሎ መፈተሽ ተገቢ ይሆናል።

በደኢህዴን ላይ የተነሳውን ህዝባዊ ተቃውሞ የተመለከቱና ሃሳባቸውን በድረገጽ ላይ ያሰፈሩ አንድ አስተያየት ሰጪ ድርጅቱ ከባድ አደጋ ላይ እንዳለ ለማሳየት "SNNDP, on fire " "ደኢህዴን በእሳት ላይ" የሚል ርዕስ ተጠቅመዋል። ደኢህዴን እንደክልሉ መሪ ፓርቲነቱ በቀዳሚነት ሊታገል የሚገባው ለክልሉ ህዝቦች መብት ሆኖ ሳለ ነገር ግን የክልሉን ህዝቦች የሚጎዳ ውሳኔ በማሳለፍ ሂደት ውስጥ ግንባር ቀደም ተዋናይ ነው ይላሉ ተቃዋሚዎቹ። በኢህአዴግ ውስጥ ያለው ሽኩቻ ከፈጠረው አዲስ የፖለቲካ መከፈት እና የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ወደስልጣን መምጣት ጋር ተያይዞ ከፍ ያለ ተስፋ ያደረበት የክልሉ ህዝብ በየዞኖቹ ዋና ከተሞች ተከታታይ የድጋፍ ሰልፎች አድርጎ ደስታውንና ተስፋውን መግለጹ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው። ያም ሆኖ በዚያው የለውጥ ሞቅታ ሰሞን በሃዋሳ እና በወልቂጤ አካባቢ ተነስተው የነበሩ ብሔር ተኮር ጥቃቶች እና ማፈናቀሎች እንዲሁም ውጥረቶች የፈጠሯቸውን ጉዳቶች በማየት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወደስፍራው ሄደው ህዝቡን አነጋግረዋል። በአንዳንድ ስፍራም የአስታራቂነት ሚና ተጫውተዋል። ገስጸዋል።ተቆጥተዋል።ወቅሰዋል። ዞኖቹ የጠቅላይ ሚኒስትሩን ቃል ሰምተው በተለይም ጉራጌ ከቀበኔ ብሔር ጋር ሊፈጥር የነበረውና ጫፍ የደረሰውን ግጭት ማርገብ ችሏል።ሲዳማም በጊዜው በወጣቶቹ የተወሰዱ ጥቃቶችን አምርሮ አውግዟል። እንዲህ በለውጡ መንፈስ ተጋግሎ የነበረው የደቡብ ህዝብ በኢህአዴግ አባል ድርጅት ደኢህዴን ውስጥ ምንም አይነት የተቀየረ አሰራር እና አመራር አለመኖሩን አየሁ ይላል። "ከፖለቲካ ፍጆታ ውጪ ለህዝቡ ጥቅም መቆሙን በአንድም አጋጣሚ ያላሳየው ደኢህዴን በተደጋጋሚ ጊዜ የሚወስናቸው ውሳኔዎች ከህዝብ ጥቅም ይልቅ ከፓርቲው ህልውና እና ዘላቂ እድሜ ጋር ተያይዘው የተሳሉ መሆናቸው "ፓርቲው አይወክለኝም" ብሎ እንዲነሳ አድርጎታል" ይላሉ አስተያየት ሰጪዎች።

ለደቡብ ዞኖች በደኢህዴን ለይ ላነሱት ተቃውሞ ቀዳሚው ምክንያት ክልል ለመሆን ያነሱትን ጥያቄ በጥናት እና በመሳሰሉት ሰበቦች ምላሽ ሳይሰጥ ማዘግየቱ ነው። ይህ በመሆኑ ሲዳማ ወደቀውስ አምርቷል። ሌሎቹ ዞኖች ደግሞ ጥያቄያቸው አለመመለሱን በመግለጽ ተቃውሞ እንዲያሰሙ ምክንያት ሆኗቸዋል። "ፓርቲው የክልሉ መንግስት መሆኑን ተገን በማድረግ በህገመንግስቱ ለብሔሮች የተሰጠውን መብት በመጣስ "ጥናት ላስደርግ" በሚል ሰበብ አዘግይቶ የህዝቡ መብት እንዲደፈጠጥ እየሰራ ነው በማለትም ይከስሱታል።በዚህ ሳቢያም የፓርቲው ህልውና በክልሉ ውስጥ አደጋ ላይ እንዲወድቅ ምክንያት ሆነውበታል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ደኢህዴን ሁለት መግለጫዎቹ ህዝቡን አስቆጥተው በሰላማዊ ሰልፍ ድርጅቱ እንዲወገዝ ምክንያት ሆነዋል። ቀዳሚው ከ15 ቀናት በፊት የድርጅቱ ስራ አስፈጻሚ እና ማዕከላዊ ኮሚቴ ለሶስት ቀናት ብለው 11 ቀን የፈጀ ስብሰባ በማድረግ በመጨረሻ ላይ ዞኖች ያቀረቡትን የክልልነት ጥያቄ በተመለከተ ምንም የማይገልጽ መግለጫ ማውጣቱ ነው። በዚህ መሃል ምርጫ ቦርድ ለሲዳማ ህዝበውሳኔ ዝግጅት እንዲደረግ መመሪያ መስጠቱ ተጨምሮበት የተቀሩትን ዞኖችም ሆነ ሲዳማን ራሱን የሚያስቆጡ ችግሮች ተከሰቱ። "መግለጫውን

እናወግዛለን፣ የክልሉን ህዝቦች ይጎዳል፣ ድርጅቱ የራሱን ህልውና ለመጠበቅ ሲል በራስ ወዳድነት የሚሰራው ተግባር ይቁም፣ ድርጅቱ አይወክለንም" ወዘተ የሚሉ ድምጾችም ተሰምተዋል።የተለያዩ ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር የተስተዋለባቸው ሰላማዊ ሰልፎችም ተደርገዋል። ሁለተኛው የየዞኖቹን ብሄሮች ያስቆጣው ተግባር ደግሞ ደኢህዴን በክልልነት ጥያቄዎች ላይ አካሄድኩ ያለው ጥናት ነው።

ሃምሌ 17 ቀን 2011 ይፋ የተደረገው እና ቀደም ብሎም በዝርዝር ባይሆንም በጨረፍታ የተገለጸው ጥናት ጉዳይ ሲገለጽ በውጤቱ ላይ የዘረዘረው ነገር የህዝቡን ፍላጎት ከነባራዊው እውነት ጋር ያላገናዘበ እና ህገመንግስቱን የሚጻረር ነው የሚል ቁጣ ቀስቅሷል። የጥናቱ ውጤት የተገለጸበት ሃተታ ከሞላ ጎደል የሚከተለውን ይመስላል።

*"ደኢህዴን በደቡብ ክልል የሚነሱ የአደረጃጀት ጥያቄዎችን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ምላሽ ለመስጠት ያስጠናው ጥናት ሰባት ወራት ፈጅቷል ...የደቡብ ክልል የብዝሃነት ምልክት እና አብሮ የመኖር አርአያ ነው...ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄዎች እና የክልል ምስረታ ጥያቄ በክልሉ በስፋት ቀርቧል....በደኢህዴን ሃሳብ አመንጪነት 20 አባላት ያሉት የጥናት ቡድን ተቋቁሞ ከአንድ ዞን በስተቀር ከክልሉ ዞኖች ከተውጣጡ ከ17ሺህ በላይ ሰዎች መረጃ ተሰብስቧል..." የ1987 የደቡብ ህዝቦች በፌዴራል መንግስት ውሳኔ በዘፈቀደ ወይስ ህዝብ ተሳትፎበት" የሚለው ጥያቄ ቀርቦ ህዝቡ በምላሹ "ደቡብ ክልል በመንግስት ተጠፍጥፎ የተሰራ አይደለም" ብለዋል... የክልሉ ምሁራን ያለመንግስት ተጽዕኖ ደቡብ ክልል እንዲመሰረት ተስማምተው የተመሰረተ መሆኑም [ተረጋግጧል]...አብዛኛው ህዝብ አሁን ያለው የክልል አደረጃጀት ይቀጥል ብሏል...ክልሉ በሁለት ወይም ከዚያ በላይ ይዋቀር የሚለው አስተያየት ሁለተኛ አማራጭ ሆኗል...የክልል ምስረታ ጥያቄ ለጊዜው ይቆይ እና በእርጋታ ይታይ የሚለውም በጥናቱ ሶስተኛ አማራጭ ሆኗል"*

ይህ መግለጫ ብዙዎችን ያስቆጣው በሁለት ምክንያት መሆኑ ይነገራል። "አንደኛው በዞኖቹ እየተካሄደ ያለው የክልል እንሁን ጥያቄ በሰላማዊ ሰልፍ እየተደገፈ በግልጽ እየታየ ድርጅቱ ግን ያንን በመናቅ አካሄድኩ ባለው ጥናት መደምደሚያ "አብዛኛው ህዝብ አሁን ያለው የክልል አደረጃጀት ይቀጥል ብሏል" በማለት ነባራዊውን እውነት በመካዱ" የሚል እና ሁለተኛው ደግሞ ህዝቡ የደረሰበትን የኢኮኖሚ ጉዳት፣ የሃብት ክፍፍል አለመመጣጠን እንዲሁም የፖለቲካ ውክልና ማነስ ምክንያት በማድረግ ክልል ልሁን ብሎ ህገመንግስቱ በሚፈቅድለት መሰረት ጥያቄ እያቀረበ ባለበት በዚህ ጊዜ፣ ከጥያቄም አልፎ ማመልከቻዬ ዘገየ በማለት ቅሬታ አልፎ አልፎም የተቀውሞ ሰልፍ እያካሄደ ባለበት በዚህ ጊዜ የክልል ምስረታ ጥያቄ ለጊዜው ይቆይ እና በእርጋታ ይታይ የሚል ውሳኔ ማሳለፉ የክልሉ ብሔሮች ከዚህ ፓርቲ ጋር ሆድና ጀርባ እንዲሆኑ ምክንያት ሆኗል የሚሉ ብዙዎች ናቸው።

የጉራጌ ህዝባዊ ንቅናቄ ሊቀመንበር ኢንጂነር ሸዋለም እንደሚናገሩት "ደኢህዴን ከህዝብ ጥቅም ይልቅ የራሱን ጥቅም የሚያስቀድም፣ አባላቱም የራሳቸው ህልውና እንዳይከስም የህዝብን ጥቅም ወደጎን የሚገፉ በውስጡ አሃዳዊነት የሚጎላበት ከአዲሱ አስተሳሰብ ጋር የማይሄድ ድርጅት ነው " በቅርቡ በተካሄዱ የቴሌቪዥን ውይይቶች ላይ የሚቀርቡ የየዞኖቹ ተወካዮች እና የፓርቲ ሊቀመንበሮች ድርጅቱ ህዝባችንን አይወክልም፣ በደቡብ ክልልም መንቀሳቀስ አይገባውም " የሚሉ መረር ያሉ ተቃውሞዎች ሲያሰሙ እየተስተዋሉ ነው። ደኢህዴን እንዲህ ያሉ ተቃውሞዎች የሚቀርቡበት ከውጭ ባሉ አካላት ብቻ ሳይሆን ከራሱ አባላትም ጭምር መሆኑ ደግሞ የፓርቲውን ቅቡልነት እና መጻዒ እድል ጥያቄ ውስጥ የሚከትት ነው። በብዙዎች ዘንድ ደኢህዴን ደቡብ ክልል ባለበት እንዲቀጥል ፈልጓል ለሚለው መደምደሚያቸው መገለጫ አድርገው የሚያቀርቡት፤ ፓርቲው ክልሉ ከተበታተነ እና ዞኖች ክልል ከሆኑ ህልውናው የሚያከትም በመሆኑ ከዚህ መክሰም ለመዳን ሲል የሚያደርገው ጥረት ነው የሚል ነው። ደኢህዴን በሚያስተዳድራቸው ዞኖች እንዲህ ያለ ቅሬታ እየቀረበበት ሳለ ከህዝብ ፍላጎት ውጪ የሆነ መመሪያ እያወጣ መቀጠል ይችላል ወይ? የሚለው ጥያቄም ለብዙዎች ግራ የሆነውም ለዚህ ነው።በአሁኑ ወቅት ይህ ፓርቲ በሚያስተዳድረው ክልል ስብሰባ ማድረግ ሳይችል አዲስ አበባ ውስጥ እንዲሰበሰብ ያስገደደውም የተነሱበት ተቃውሞዎች እና የጸጥታ ስጋቶች ናቸው።

## ጥናቱ ለምን ተኮነነ?

የደቡብ ዞኖች ክልል ለመሆን ያቀረቡት ጥያቄ በጥናት ይፈታ ሲባል ብዙዎች ተቃውመዋል። ለዚህም የሚያቀርቡት ምክንያት ሁለት ነው። አንደኛው ህገመንግስቱ በአንቀጽ 47 ድንጋጌው ክልል ለመሆን ጥናት ይደረግ የሚል መመሪያ አለማካተቱ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ደቡብ ከ5 ክልልነት ወደአንድ ክልልነት ሲጨፈለቅ የህዝብ ምክክር አለመካሄዱና በዚህ ጉዳይ ላይ የተደረገ ጥናት አለመኖሩ ነው። በመሆኑም የህዝብ ጥያቄ በህገመንግስት እና በተቀመጠ ህግ እንጂ በጥናት አይፈታም የሚል አቋም እየተንጸባረቀ ይገኛል። ይህ በሆነበት ሁኔታ ደኢህዴን በራሱ አነሳሽነት እንዳካሄደ በግልጽ የሚነገርለትን ጥናት በመደምደሚያ ሃሳቡ "የክልልነት ጥያቄን ለጊዜው ይቆይ" ብሎ ሲወስን፤ ኢ ህገመንግስታዊ ሆኖ የብሔሮችን መብት ጨፍልቋል" የሚል ተቃውሞም ቀርቧል።

የኢፌዲሪ ህገመንግስቱ አንቀፅ 47 ንዑስ አንቀፅ 3 ስር ከሀ-ሠ በተዘረዘሩት ቅድመ ሁኔታዎች የክልል መሆን ጥያቄ የሚስተናገድበት አግባብ ተቀምጧል። ህገመንግስቱ " ማንኛውም ብሔር፣ ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ የራሱን ክልል የመመሥረት መብት አለው።" ይላል። ክልል ለመሆን ብቸኛ መስፈርትም ቋንቋና ማንነትን ማሟላት መሆኑን ይናገራል።

በዚህ አንቀጽ መሠረት ይህ መብት ተግባራዊ የሚሆነው የክልል መመሥረት ጥያቄው በብሔሩ፣ ብሔረሰቡ፣ ወይም ሕዝቡ ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ ድምፅ ተቀባይነት ማግኘቱ ሲረጋገጥና ጥያቄው በጽሑፍ ለክልል ምክር ቤት ሲቀርብ፣ ጥያቄው የቀረበለት ምክር ቤት ጥያቄውን በደረሰው በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለጠየቀው ብሔር፣ ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ሕዝበ ውሳኔ ሲያደራጅ፣ ክልል የመመሥረት ጥያቄው በብሔሩ፣ ብሔረሰቡ ወይም ሕዝቡ ሕዝበ ውሳኔ በአብላጫ ድምፅ ሲደገፍና የክልሉ ምክር ቤት ሥልጣኑን ለጠየቀው ብሔር፣ ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ሲያስረክብ እንደሆነና ይህ አዲሱ ክልል የፌዴራል መንግሥቱ አባል እንደሚሆን ይደነግጋል። በዚህ ውስጥ ጥናት ይደረግ የሚል አንቀጽ አለመኖሩ በደኢህዴን ተካሄደ ለተባለው ጥናት ህጋዊነት ጥያቄ ሆኖ የቀረበውም ለዚሁ ነው።

## "ለግማሽ ቀን ስብሰባ የሁለት ቀን ጉዞ"

ባለፈው ወር በቦንጋ ከተማ በተካሄደው የካፋ ዞን የክልልነት ጥያቄ ሰላማዊ ሰልፍ ላይ በካፋ ጉርማሾ ወጣቶች ተይዘው ከታዩት መፈክሮች አንዱ "ለግማሽ ቀን ስብሰባ የሁለት ቀን መንገድ" የሚል ውስጠ ወይራ መልዕክት አንዱ ነበር። ይህ መልዕክት የደቡብ ክልል የፖለቲካ እና ኢኮኖሚ ማዕከል የሆነችው ሃዋሳ ላይ የተቀመጠው የክልሉ መንግስት መሪ ፓርቲ ደኢህዴን የግማሽ ቀን ስብሰባ ሲጠራ ከካፋ ዞን የተለያዩ ወረዳዎች ወደሃዋሳ የሚጓዙ ባለስልጣናት ለዚህ የግማሽ ቀን ስብሰባ 2 ቀን ሙሉ መጓዛቸውን በማሳየት ዞኑ ምን ያህል ከፍትህ እና አስተዳደር አገልግሎቶች ተራርቆ መኖሩን ለማሳየት የተጠቀሙበት ነው። በአንዳንድ ቦታዎች እንደሚነገረው ፓርቲው የሚመራው የክልሉ አስተዳደር ሃዋሳ ላይ ዓመታዊ ወይም የሩብ አመቶች ግምገማ ስብሰባ ሲጠራ፤ ከዞኖች ነቅለው ወደሃዋሳ በሚጓዙ የአስተዳደር ሓላፊዎች ሳቢያ ዞኖቹ በሙሉ የፍትህ እና አስተዳደር አገልግሎት የሚቋረጥባቸው መሆኑንም ይናገራሉ።

ይህ ብቻ ሳይሆን ህዝቡ ፍትህ ሲፈልግ ፣ በዞኑ መፈጸም የማይችሉ አስተዳደራዊ ጉዳዮች ሲገጥመው ከዞኑ እየተነሳ ወደክልሉ መቀመጫ ከተማ ሃዋሳ የሚያደርገው ጉዞ "ፍትህን በ2000 ኪሎሜትር ርቀት ላይ እንደመፈለግ" እየተወሳ አወቃቀሩ ህዝቡን የማይጠቅም እንደሆነም ሲነገርበት ቆይቷል።

እንዲህ ያሉ የምጣኔ ሃብት ብክነት፣ የሃብት ክፍፍል መዛባት፣ የፖለቲካ ውክልና ማጣትና የመሳሰሉት ጥያቄዎች ራስን በራስ ለማስተዳደር ፍላጎት መነሻ መሆናቸው ከታየ፣ ያም በህዝብ ድጋፍ ከተረጋገጠ፣ ህገመንግስቱም ይህንን መብት በግልጽ ካስቀመጠ እና ክልል መመስረቱ በሃገር አንድነት ላይ የሚፈጥረው አደጋ ከሌላ ጉዳዩ ተካረሮ ዘላቂ የሰላም ማጣት ችግር ከመሆኑ በፊት መንግስት ውሳኔ ቢሰጠው ሊከሰት የሚችለውን የህዝብ ቅሬታ፣ ቁጣ እና ጥፋት ከወዲሁ ለመከላከል ይበጃል የሚሉ መካሪዎች የስጋት ድምጽም መሰማት ጀምሯል። ምናልባትም ይህ ክልል ለዓላማቸው "የበሰለ እንጀራ" የሆነላቸው አካላት በስንጥቁ ገብተው ችግሩን እንዳያሰፉትና ሃገሪቱንና ዜጎቿን ስጋት ላይ የሚጥል ነገር እንዳይጭሩ ከወዲሁ ለመከላከል ማሰብ ከተቻለ አሁን ህዝብን ያማከለ ውሳኔ ለማሳለፍ ጊዜው ባይረፍድ ሁሉም ያተርፋል።

# የፋኖ፣ ቄሮ፣ ኢጄቶ፣ ዘርማና መሰል ቡድኖች ባለቤት ማነው?

ከሀዋሳ ተነስቶ ይርጋለም፣ አለታወንዶ፣ ሀገረማርያምና የተለያዩ የሲዳማ ዞኖችን ያዳረሰው የአመጽ እንቅስቃሴ አሳዛኝ የሆኑ ክስተቶችን በስፋት እንድንመለከት አድርጎናል፡፡ የሲዳማን የክልልነት ጥያቄ መሰረት ያደረጉ ወጣቶች፤ የክልሉ ሕዝብ ያቀረበው ሕገ - መንግስታዊ ጥያቄ፣ በተጀመረው የህግ አግባብ መስመር እንዲጓዝ ማድረግ ሲጠብቅባቸው ነውረኛ ድርጊቶችን ለመፈፀም ያለ መታከት ሲባዝኑ ታይተዋል፡፡

በተጠቀሱት ከተሞችና የተለያዩ ጥቃቅን ስፍራዎች ውስጥ በጥቂት የሲዳማ ተወላጅ ወጣቶች ስም የተዋቀረው ኢጄቶ የተሰኘው ቡድን፤ ለጥያቄያቸው ምላሽ የነፈጋቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሆነ ይመስል፣ ከራሳቸው ብሔር ተወላጅ ውጪ የሆኑ ዜጎችን በድንጋይና በገጀራ ደብድበው አካል አጉድለዋል፣ የሰው ሕይወት አጥፍተዋል፡፡ አስቀድመው በሰሩት የሥም ዝርዝር እየተመሩም በርካታ መኖሪያ ቤቶችንና የንግድ ሱቆችን አውድመዋል፤ አቃጥለዋል፡፡

ለዘመናት በደስታ፣ በሀዘንና በመከራ ከሲዳማ ሕዝብ ጋር የኖሩ፣ ወልደው ከብደው ሃብት ማፍራት የቻሉ፣ የአያትነት ፀጋን በዚህ ለም ምድር የተጎናጸፉ፣ የኑሮና የሕይወት መስተጋብራቸው ከዞኑ ነዋሪ ጋር የተጋመደ፤ በርካታ ኢትዮጵያውያን "የእኛ አይደላችሁም" በሚል ክፉኛ ተደብድበዋል፤ ቤት ንብረታቸውንም ጥለው ለመውጣት ተገደዋል፡፡ የሲዳማ ዞንን እንደናጧት የኢጄቶ ዕድሜ እኩዮቻቸው በዛው ሥፍራ ተወልደው፣ ተምረውና ተመርቀው፣ ተሞሽረው ለወግ ለማዕረግ የበቁ ብዛት ያላቸው የተለያዩ ብሔሮችን የሚወክሉ ኢትዮጵያውያን በጥቂት የሲዳማ ወጣቶች ጨዋነት የጎደለው ተግባር መጠጊያ፣ መሸሸጊያ አጥተው፤ አቅፎ ባሳደጋቸው ማህበረሰብ ፊት አንገት እንዲደፉ ተደርገዋል፡፡

በጥቂት የሲዳማ የሲዳማው ወጣቶች ስብስብ ሰሞኑን የተፈፀመውን የብሔርተኛነት እንቅስቃሴ ተከትሎ በወላይታና በአንዳንድ አካባቢዎችም ለራሳቸው "መጠሪያ" ያበጁ የተለያዩ ቡድኖች ሕግን ከመጣስ ባሻገር፤ የሌላውን ሕብረተሰብ የመኖር ነፃነት በተጋፋ መልኩ በስህተት የተለመዱ ድርጊቶችን በማንአለብኝነት ፈፅመዋል፡፡ ባለፉት ሁለት እና ሶስት ዓመታት፣ በተለይም ከለውጡ ማግስት ጀምሮ በየቦታው "የጎበዝ አለቃ ነኝ" ባይ በዝቷል፡፡ እነዚህ ቡድኖች ከጊዜ ወደ ጊዜ መበራከታቸው ብቻ ሳይሆን የሚፈይዱትም አንድም የረባ ነገር አለመኖሩ ደግሞ ያሳዝናል፡፡

በአማራ ክልል "ፋኖ"፣ በኦሮሚያ "ቄሮ"፤ በክልልነት ጥያቄ ስም "ኢጄቶ"፣ የጉራጌው "ዘርማም" ሆነ የትኛውም ቡድን፤ ከሚያነሷቸው ጥያቄዎች ጀርባ የፈለጉትን ጥፋት ሲያደርሱ ዕርምጃቸው በፍጥነት ሊገታ ያልቻለው፤ ቡድኖቹ አንድም በየትኛውም ሕጋዊ መንገድ ዕውቅና ያገኙ፣ በተቋም ደረጃ የተመዘገቡ አለመሆናቸው ሲሆን፤ በየክልላቸው ያሉ ጥቂት የማይባሉ ከፍተኛ የመንግስት ሓላፊዎችም በተዘዋዋሪ መደግፋቸውና የወጣቶቹ እንቅስቃሴ እንዲኖር መሻታቸው በሁለተኛ ምክንያትነት ይጠቀሳል፡፡

በተለያዩ ጊዜያት "የእከሌ ቡድን መሪ ተያዘ" ከሚል መግለጫ ውጪ፤ ፋኖ ይሁን ቄሮ፣ ኢጄቶ ይሁን ዘርማን ማን እንደሚመራቸው፣ ባለቤታቸውስ ምን ዓይነት አካል እንደሆነ ሲገለጽ አልታየም ወይም በቂ ጥናትና ክትትል አልተደረገባቸውም፡፡ ማንም እየተነሳ ለቀናት መንገድ የሚዘጋበት፣ ፌደራል መንግስቱ በማያውቀውና ተጠቃሚ ሊሆን ባልቻለበት ህገ-ወጥ አሰራር፤ በተለያዩ ክልሎች ላይ ከአሽከርካሪዎች የመውጫና የመግቢያ ገንዘብ የሚከፈልባት፣ "በእኛ ክልል መስራት የምንችለው እኛ ብቻ ነን" የሚሉ የማፊያ ቡድኖችና ሕገ-ወጥ ድርጊቶች በአደባባይ የሚተገበሩበት ሃገር ሆናለች ኢትዮጵያ፡፡

ይህ ሂደት መቼና እንዴት ሊቆም የሚችል ጠቋሚ አንዳችም ፍንጭ የለም፡፡ መንግስትም የወጣቶቹ ስብስቦች በየቦታው ጥፋትና ዕልቂት ካደረሱ በኂላ ዕርምጃ መውሰዱ፣ አጥፊዎቹ የልብ ልብ እንዲሰማቸውና የሚሄዱበትን መንገድ ትክክለኛ አድርገው እንዲያስቡ አስገድዷቸዋል ማለት ይቻላል፡፡ ሰሞነኛው የኢጄቶ የለየለት ጥፋት፤ የዞን ጥያቄ ባቀረቡት ሌሎች አስር ዞኖች ውስጥ ነገ እንደ መርህ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችልበት ዕድል መኖሩን አስቦ፤ ከወዲሁ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ይመስለናል፡፡

ወጣት የነገ ሀገር ተረካቢ ከመሆኑ አኳያ የሚያነሳቸው ዘርፈ ብዙ ጥያቄዎች መኖራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ጥያቄዎቹ እስከመጨረሻው ድረስ የሚጓዙበት ሂደት፣ አንዱን ከሌላው እያናከሰ የሚኖር ክፉ ጠባሳን ትቶ ማለፍ እንደሌለበትም ማስተዋል ብልህነት ነው፡፡ መንግስት ከእነዚህ ቡድኖች የሥር አደረጃጀት ጀምሮ እስከ አመፅ ማነሳሳት ተሳታፊ የሆኑ የየከተማውና የየዞኑ ሓላፊዎችና የየብሔሩ ልሂቃንና የጥፋት ፖለቲከኞች ላይም የማያደግም ዕርምጃ በመውሰድ በተቀደደው ቦይ ለመፍሰስ የሚግተለተሉ ኃይሎችን የመግታት ሃላፊነት ብቻ ሳይሆን ግዴታም ጭምር እንዳበት ለማስታወስ እንወዳለን፡፡


**ግዮን መጽሔት**
**ኢትዮ ሐበሻ ኅትመትና ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር**
**በየሳምንቱ ለኅትመት የምትበቃ መጽሔት**

**ማኔጂንግ ዳይሬክተር**
ፍቃዱ ማ/ወርቅ

**ዋና አዘጋጅ**
ሮቤል ምትኩ
አድራሻ፡- የካ ክ/ከተማ
ወረዳ 2 የቤት ቁጥር 475

**ከፍተኛ አዘጋጅ**
ብሩክ መኮንን
አለማየሁ ባዘዘው

**አዘጋጅ**
ፍቅርተ ተሾመ
ሙሉጌታ አክሊሉ

**አምደኞች**
ወንድሙ ነጋሽ(ኢ/ር ከለንደን)
ተረፈ ወርቁ
ሁሴን ከድር

**ክርኤቲቭ ዲዛይን**
ፍፁም ንጉሴ

**ጸሐፊ**
ሠላም ግርማ

**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**
አራዳ ክ/ከ ወረዳ 09
የቤት ቁጥር 552/1
አምባቸው ህንፃ 2ተኛ
ፎቅ ቢሮ ቁ. 207
ፖስታ ቁ. 676 ኮድ 1029
ስልክ ፡ +251 911 22 76 61
+251 912 165606
+251 118 12 2333
ኢ-ሜይል፡
enqu2013@ gmail.com
Ghion2011meg@gmail.com
**Facebook**
Gihon-meg Fekadu
www. facebook.com/enqu2013



በዚህ መጽሔት ላይ የሚወጡ ጽሑፎች በሙሉ ማተሚያ ቤቱን አይመለከትም



**አታሚ**
ቴዎድሮስ ንብሩ ማተሚያ ቤት ፤ አራዳ ክፍለ ከተማ
ወረዳ 10 የቤ.ቁ. 066/ሀ
0911223335/ 0911420506

# የፋኖ ጅራፍ ራሱን ገርፎ ራሱ ሲጮህ



ጌታቸው መለኩ

ባለፈው የወሩ መጀመሪያ ጠቅላይ ሚንስትር ዐቢይ አሕመድ አክሱም ከተማ ብዙዎች ባልጠበቁት ሁኔታ ደርሰው፣ ከህዝቡ ጋር እንዲሁም ከክልሉ ምክትል ርዕሰ መስተዳደር ዶ/ር ደብረፅዮን ገብረሚካኤል ጋር ተወያይተው ነበር፡፡ ዶ/ር ደብረፅዮን አዲስ አበባ ሲመጡ የሚደመሩት መቀሌ ሲመለሱ የሚቀነሱት ነገር በጥያቄ ምልክት ውስጥ እያለ፤ ጠ/ሚኒስትሩ ያደረጉት የዚህ ጉብኝታቸው ዋና ዓላማ ተድበስብሶ ቢታለፍም እንደሚገመተውም ከጆርባ ሌላ ዓላማ ይኖረዋል ተብሎ ብዙዎች መላምት እንዲሰናዝሩ አስገድዷል፡፡

ምንም ይሁን ምን ሰውየው በሚዲያ የተዘገበውን ውይይታቸውን ከማህበረሰቡ ጋር አድርገው ተመልሰዋል፡፡ ነገር ግን እንድ በድራማና በሽልማት የተድበሰበሰ ጉብኝት እግረ መንገዳቸውን ሚያስመስል መልኩ አድርገው ነበር፡፡ በደሴ ከተማ በተካሄደ የጠ/ሚኒስትሩ ጉብኝት ዋና ጉዳይ እንዲሁ በተለመደው የድብቅነት አባዜ ከህብረተሰቡ ጋር በሰላምና በልማት ጉዳይ ዙሪያ ተወያዩ ከማለት በቀር የተገለጠ ነገር አልነበረም፡፡ ነገር ግን ጉዳዩን በቅርበት የሚከታተሉ ግለሰቦች የጠ/ሚ/ሩ ጉዞ በተለይ በትግራይ ህዝብ ዘንድ የተነሳው የአዲስ አበባ ደሴ መቀሌ መንገድ ለረጅ ጊዜ መዘጋት ጉዳይ ነው ተብሏል፡፡

ሰዎች በአጋጣሚ ከአዲስ አበባ ቦሌ ዓለም ዓቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ የሀገር ውስጥ መንገደኞች ማስተናገጃ ተርሚናል ላይ ቢገኙ፤ በተለይ የሚታዘቡት ነገር ወደ ትግራይ ከተሞች የሚጓዙ ሰዎች ቁጥር ባልተለመደ ሁኔታ መጨመሩን ነው፡፡ ይህ በእርግጥ የሀገራችንን ጉዳይ የሚያውቅ ማንኛውም ግለሰብ የሚረዳው ጉዳይ እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡ ከአዲስ አበባ በደሴ መቀሌና ወደ ሌሎችም የትግራይ ክልል ከተሞች የሚያልፈው የየብስ ተሽከርካሪ መንገድ ከተዘጋ ቀናት አልፈው ወራት መምጣታቸውን ማንም የሚውቀው ጉዳይ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ በሰፊው የፋኖ ተግባር ነው ተብሎ የሚነገር ክልከላ በትግራይ ተጓዥ መንገደኞች፣ በትግራይ ክልል ባሉ ነጋዴዎችና ሌሎች አካላት እንዲሁም በትግራይ ክልል ያለው አብዛኛው ህብረተሰብ ላይ እያሳደረ ያለው የንግድ እንቅስቃሴና የሸቀጦች ዋጋ ንረት ተፅእኖ ከፍተኛና የወደፊት ህዝብ ለህዝብ የሚኖረውን ግንኙነት የሚያሻክር ተግባር ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ከአዲስ አበባ ደሴ መቀሌ ያለውን መንገድ የመዘጋት ተግባር ፋኖውን ራሱን ገርፎ ራሱ እንዲጮህ እያደረገው ነው፡፡

የአገራችን ሀገር አቋራጭ የረጅም ርቀት ትርንስፖርት ባህርይ የተለያዩ ባለድርሻዎችን በታሪኩ መፍጠሩን ብዙዎቻችን እናውቃለን፡፡ በተለይ የተሽከርካሪው መጓጓዣ መንገዶች በሚያልፉባቸው ከተሞች ያሉ ነዋሪዎች የሚያገኟቸው አንዳንድ ጠቀሜታዎች እንደሉ ሁላችንም የምናውቀው ጉዳይ ነው፡፡ ለምሳሌ ከአዲስ አበባ ደሴ መቀሌ መንገድ ላይ የሚያልፉት ተሽከርካሪዎች በየከተማው የሚያገኟቸውን ምርትና አገልግሎቶች እየተጠቀሙ ጉዞአቸውን እንደሚመሩ የታወቀ ነው፡፡ በዚሁ መንገድ ተጓዦች ደብረሲና ላይ ቆሎ ገዝተው፣ያቺን እየተካፈሉ ከዚያቀን በፊት አይትውት ከማያውቁት ሰው ጋር እንኳ መስተጋብር የሚፈጥሩበት አጋጣሚ ትልቅ ነው፡፡ ሲቀጥል አጣዬ ከመድረሱ በፊታ ካሉ ሞቃታማ ከተሞች ሸንኮራ አገዳውን ሰው እየገዛ ለቤተሰብ ወይም እዚያው ለጉዞ ድካም ማስረሻ እየተጠቀመበት ይጓዛል፡፡ ሲቀጥል ዘላቂ መንገደኞች ያላቸው አንዱን ቀን ምሽት የሚያሳልፉባቸው ከተሞች ውስጥ ለአልጋውም ይሁን ለሌሎች አገልግሎቶች የሚያደርጉት ወጪ ለእነዚህ አካላት ገቢ ብቻ ሳይሆን ለአንዳንዶች ደግሞ የኑሮ ዋስትና የሆነ ገቢ የሚገኝባቸው መንገዶች ናቸው፡፡ ታዲያ ይህንን ያጣው የእነዚህ ከተሞችና ክልሎች ህዝብ፣ በተለይ ደሀው ማህበረስብ በዚህ መንገድ መዘጋት "ተጠቃሚው ማን ይሆን?" ብሎ መጠየቁ አይቀርም፡፡

ከአንድ ወዳጄ ጋር የሰራናት ትንሽ ሂሳብ እንደምታሳየው መንገዱ ከመዘጋቱ በፊት በቀን ከ50 የማያንስ ሀገር አቋረጭ አውቶብስ በመንገዱ ይተላለፋል፡፡ ይህንን ቁጥር በአማካይ የተጓዦች ቁጥር 60 ብናበዛው 3000 ሰው ማለት ነው፡፡ ይህን ያህል ሰው በቀን 100 ብር እንኳ በጉዞው ቢያውጣ (ልብ ማድረግ ያለብን አዳር ሳይጭምር ነው) 300.000ብር ማለት ነው፡፡ ይህ በኣመት ውስጥ ባሉት 365 ቀናት ሲባዛ 110 ሚሊዮን ብር አካባቢ ነው፡፡ እዚህ ላይ በአማካይ 100 ብር የአልጋ ዋጋ ብንጨምርበት ሂሳቡን እጥፍ ያደርገዋል፡፡

ወደ ሰሜን በነበረ አንድ ጉዞ አንድ የወልድያ ነዋሪ ወጣት ለባልደረባዬ ያጫወተው ጉዳይ ለዚህ "የፋኖ ጅራፍ ራሱን ገርፎ ራሱ ይጮሀል" ለሚለው መነሻ ሁነኛ ማሳያ ሆኖ አይቼዋለሁ፡፡ ይህ በወልዲያ ከተማ የሚኖር ወጣት ዋናው የገቢው ምንጩ በከተማዋ ወደ አዲስ አበባም ይሁን ወደ መቀሌ የሚሄዱ መኪኖች ላይ የሚሳፈሩ ደራሽ ተጓዦችን በማፈላለግ የድለላ ስራ መስራት ነው፡፡ ወጣቱና ጓደኞቹ በዚህ የድለላ ስራ ላይ ተሰማርተው አንድም ይሁን ሁለት ሰው በመሸኘት የእለት ጉርሳቸውን ይሸፍኑ ነበር፡፡ ነገር ግን በመንገዱ መዘጋት ምክንያት ይህንን ማግኘት አልቻሉም፡፡ በዚህም ሀዘን እንደሚሰማው የገለፀው ወጣት ጉዳዩን በግሉ መቃወም አለመቻሉ ዋጋ እያስከፈለው እንደሆነ ገልጧል፡፡

እንደዚህ አይነት የደቦ ፍርድ ቢሚካሄድበት ቦታና አጋጣሚ ሰዎች ሰብአዊ የሆነ የመደገፍና የመቃወም እንዲሁም የተለየ ሀሳብ የማራመድ መብታቸው ሲደፈጠጥ ማየት እጅግ ያሳዝናል፡፡በተለይ አሁን ለውጥ መጥቷል፡፡ ማንም ሰው የፈለገውን ነገር መናርና ያሻውን ሀሳብ በሰላማዊ መንገድ ማራመድ ይችላል እየተባለ እንደዚህ አይነት አፋኝ ህገወጥ ድርጊቶች ዋጋ የሚያስከፍሉት "ዋጋ እንዲከፍል የተፈለገውን አካል" ሳይሆን ደካማውንና አማራጭ የሌለውን የማህበረሰብ ክፍል ነው፡፡ ሰዎች በዚሀ መልኩ ሰብአዊ የዜግነት መብታቸውን መነጠቅ ከጀመሩ በሂደት በራሳቸው ላይ አምባገነኖችን የመሸከም ግዴታ ውስጥ ገብተው ሌላ ዙር ችግርና መከራ ውስጥ ሲገቡ ማየት በእውነት ያማል፡፡

"በትግራይ ክልል ውስጥ ተደብቀዋልና ለበርካታ የአማራ ወጣት መገደል፣ መሰደድና መጎሳቆል ምክንያት ናቸው የተባሉትን ግለሰቦች አገኛለሁ" ብሎ እንዲህ አይነት ራስን የሚጎዳ ተግባር ከሚያስብና ከሚቆረቆር ፋኖ አይጠበቅም፡፡ በእውነትስ የፋኖውን እንቅስቃሴ በእውቀትም በስሜትም እንመራለን የሚሉ ግላቦች ይህንን ችግር ተመልክተውት ይሆን፡፡ የትግራይ ህዝብም እነዚህ የወንጀል ተፈላጊ ግለሰቦች በክልሉ መኖራቸውን እያየ ተራ ወገንተኝነት ካልሆነ በስተቀር ምን የሚሉት ዝምታ ነው? ቢያንስ በፌደራል መንግስት ክስ ተመስርቶባቸው ያሉ ግለሰቦች ለህግ የበላይነት ሲባል ራሳቸውን እንዲከላከሉ መገፋፋት ለምን ተሳነው? ስንል ከፋኖው ባልተናነሰ ቢያንስ ወጣቱ የሕወሓት ደጋፊ የስሜተኝነት አባዜ ሰለባ እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡

ሕወሓት የትጥቅ ትግሉን ሲጀምር የአማራን ህዝብ እንደ ህዝብ (እዚህ ጋር ልብ ማለት የሚያሻው የአማራን ገዢ መድብ የምትለው ትርክት የመጣችው በኋላ ነው) በጠላትነት ፈርጆ መነሳቱን በማኒፌስቶው ሳይቀር አስፍሮ ሲያበቃ፤ ቢያንስ "ለትግል እስትራቴጂ ሲባል የተሰራ ስህተት ነው" የሚል ውሀ የማያነሳ ምክንያት እንኳ ሰጥቶ ይቅርታ መጠየቅና የዚህን ችግር ምዕራፍ ሳንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መዝጋት ለምን አልፈለገም? ወይስ እንደሚባለው የመገንጠል ሀሳብን እስከ መጨረሻው ለመግፋት? ምክንያቱ ዋናዎቹ መሪዎች ተጠያቂነትን ፈርተው፣ ያለፉት መሪዎች ደግሞ ተወቃሽ እንዳሆኑበት ሰግቶ ከሆነ ችግሩ ለትውልድ የሚተርፍ መሆኑን እንዴት ያጡታል? ብዬ ራሴን ስጠይቅ ሞኝ የሆንኩኝ ያህል ይሰማኛል፡፡

በመሆኑም ፋኖው ከአዲስ አበባ ደሴ መቀሌን መንገድ ሲዘጋና ሌሎች እንቅስቃሴዎችን ሲገታ በተፈጠሮው እንዲሁም በህግ ላይ ወንጀል እየሰራ መሆኑን ቢረዳ፤ ከዚያም አልፎ በዚህ ስሜታዊነት በሚንፀባረቅበት እርምጃ ራሱን ገርፎ ራሱ እየጮኸ እንደሆ ቢገባው መልካም ነው፡፡

ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አዘውትው እንደሚናገሩት መንግስት ወደ እርምጃ የማይገባው ጉልበት ስላጣ ሳይሆን በተቃራኒው አለቅጥ ጉልበት ስላለው በሚወስደው እርምጃ ጉዳቱ አሳዛኝ እንዳይሆን ነው የሚለው ሀሳባቸው ታጋሽነትና አርቆ አሳቢነት የሚታይበት ቢመስልም፣ መንግስታዊ ሀላፊነትን የመሸሽ ያህል እንዳሆይን ደግሞ መጠንቀቅ አለባቸው፡፡ ጠቅላይ ሚንስትሩ አዘውትረው እንደሚሉት መንግስት ታጋሽነትና ሆደሰፊነትን በተግባር ማሳየት አለባት ቢባልም መጠኑና ልኩ ግን በደንብ ካልታወቀ የዚህ ነገር ጉዳቱ እንዳይከፋ ያሰጋል፡፡

# የአዲስ አበባ "አዳዲስ አበቦች!"

አዲስ አበባ ከተማ በበርካታ ጥልፍልፍ፣ ውስብስብና ተደራራቢ ችግሮች ተጠፍንጋ አመታትን በችግር ስትዳክር የኖረች ከተማ ናት። የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለማቸው ማጠንጠኛና የዙፋናቸው ማዕኛ አድርገዋት የቆዩ የሀገሪቷ መንግሥታትም ከከተማዋ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች ይልቅ በወንበራቸው ዕድሜ መርዘም ላይ በማተኮራቸው ከተማዋ ዘመናትን ከነችግሮቿ እንድትገፋ፣ ችግሮቿም እየተባባሱ እንዲሄዱ ምክንያት ሆነዋል።

በዶ/ር ዐቢይ አሕመድ የሚመራው አዲሱ የለውጥ መንግሥት በትረ ሥልጣኑን ከያዘ በኋላ ባሉት ጥቂት ወራት ወዲህ በመዲናዋ እየተስተዋሉ ያሉ አዳዲስ ነገሮች ግን ከተማዋ በአንዴም ባይሆን በጊዜ ሂደት ከችግሮቿ የምትላቀቅበት ፀሐይ እየወጣላት መሆኗን የሚያመላክቱና ነዋሪዎቿም ተስፋን የሚሰንቁባት እንድትሆን እያነሳሱ እንደሆነ ማስተዋል ይቻላል።

ለውጡን ተከትሎ የከተማዋ ም/ከንቲባ እንዲሆኑ የተሾሙትና አሁን ከተማይቱን በዋናነት እያስተዳደሩ የሚገኙት ም/ከንቲባ ኢንጂነር ታከለ ዑማ፤ ምንም እንኳን "በህዝብ የተመረጡ ባለመሆናቸው ሹመታቸው ህጋዊ አይደለም። የአስተዳደር ካቢኔያቸውም ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም" እየተባለ ትችት፣ አስተያየትና ተቃውሞ እየተነሳባቸው ቢሆንም፣ ከትችትና ተቃውሞው በመለስ በሹመታቸው ምን ሰሩ? ምን ለውጥ አመጡ? ተብለን ብንጠየቅ የምንመልሰው አዎንታዊ መልስ እንደማናጣ ከልብ አምናለሁ።

ኢንጂነር ታከለ ዑማ የከተማዋን የቀደመ መልክ ለመለወጥና ነዋሪውን ህዝብ የተሻለ አገልግሎት እንዲያገኝ ለማድረግ ሰፊ እቅድ ነድፈው ሁሉንም በበላይነት እየመሩና እያስፈፀሙ መሆኑን ለማጋገጥ ተግባሮቻቸውን ከብዙ በጥቂቱ ማንሳት ተገቢ ይመስለኛል። "የፈለገውን ያክል አኩሪ ተግባር ቢሰሩ ሹመታቸው ህጋዊ እስካልሆነ ድረስ ተቀባይነት የለውም" ከሚሉ ወገኖች ጋር በምንም መልኩ እሰጣገባ ውስጥ መግባትና "ልክ ናችሁ፤ አይደላችሁም" የሚል አስተያየት መስጠት የማልፈልግ መሆኔን በዚህ አጋጣሚ መግለጽ የምፈልግ ሲሆን፣ የፅሁፌ (ሀሳቤ) ማጠንጠኛ "ምን ተሰራ? ምን እየተሰራ ነው? ምንስ ታቅዷል" በሚለው ጉዳይ ላይ ብቻ የሚያተኩር መሆኑንም ለመግለፅ እፈልጋለሁ። ይህንን ሣደርግ ግን "ከዚህ ቀደም በህዝብ የተመረጡ ምን ሠሩ?" በሚለው ሀሳብ ውስጥም ሆኜ እንደሆነ ሳልዋሽ መናገር እፈልጋለሁ።

ም/ከንቲባ ኢንጂነር ታከለ ዑማ እና ካቢኔያቸው አዲስ አበባን ውብ፣ ፅዱና ለነዋሪዎቿ ምቹ የመኖሪያ ከተማ ለማድረግ እጅግ ግዙፍ ከሚባሉ ፕሮጀክቶች ጀምሮ በየቤታችን ሊደርሱ የሚችሉ ልዩ ልዩ የለውጥ ተግባራትን ነድፈው በተግባር ላይ እያዋሉ መሆኑን ከተጨባጭ ተግባራቸው መመዘን ይቻላል። በቅርቡ "የሸገር እራት" ተብሎ በቤተ መንግስት ከተካሄደው የገቢ ማሰባሰቢያ እራት ግብዣ ፕሮግራም በፊት በነበሩት ጊዜያት ተደጋግሞ ሲነገር እንደቆየው የቆሻሻ ማከማቻና ማዘዋወሪያ ሆነው የቆዩትን የከተማዋ ወንዞች አዲስ ውበት በማላበስ ከሀገር ውስጥ አልፎ የውጭ ሀገር ቱሪስቶችን ወደ ከተማዋ መሣብ የሚችል ግዙፍ ፕሮጀክት ተጠንቶ ወደ ስራ ተገብቷል። የአዲስ አበባ ወንዞችን ውብና ማራኪ የመናፈሻና የመዝናኛ ስፍራዎች ለማድረግ ስራው በይፋ ተጀምሯል። ይኖራቸዋል ተብሎ የታሰበውን የወንዞቹን የወደፊት መልክ ያየን ዜጎችም በዚህ ተደስተን አልቆ የምናይበትንም ቀን መናፈቅ ጀምረናል።

የከተማዋ ችግሮች ውስብስብ፣ ጥልፍልፍና ተደራራቢ እንደመሆናቸው ሁሉንም በአጭር ጊዜ መቅረፍ አይቻልም። በፍጥነት፣ በትጋትና፣ በእኔነት ስሜት ከተሰራባቸው ግን ሁሉም የማይወገዱ ችግሮች አይደሉም። ማኅበራዊ ችግሮች ላይ ተደጋጋሚና ያልተቋረጡ ጥረቶች ከተደረጉ የተሻለ ውጤት ለማምጣት ብዙ አስቸጋሪ አይደለም፡ ፡ ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ላይ የልብ ቅንነት ካለ ችግሩ ከኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን አቅም በታች እንጂ ከአቅም በላይ ተደርጎ አይታሰብም። ፖለቲካዊ ችግሮቹም የአንድነት፣ የመቻቻልና አብሮ የመኖር ባህላችንን መመለስ ከቻልን ተረት ሆኖ የሚቀር እንጂ ባለበት የሚዘልቅ አይሆንም፡ ፡ ምክትል ከንቲባ ኢንጂነር ታከለ ኡማ እና ካቢኒያቸው የከተማዋን ሁለንተናዊ የቆዩ ችግሮች ለመቅረፍ ረፍት አልባ ጥረት እያደረጉ ስለመሆኑ ከተግባራዊ እንቅስቃሴያቸውና እስካሁን ከታዩ ውጤቶች አንፃር መገምገም ይቻላል። ከተማዋን ውብ፣ ፅዱና ሣላማዊ የመኖሪያ ከተማ እንድትሆን ለማድረግ ከተጀመረው ሰፊ ስራ በተጓዳኝ የነዋሪውን ኢኮኖሚያዊ ጫናዎች ለመቅረፍ እየተሰሩ ያሉ አዎንታዊ ተግባራትን በመገምገም መጪው ጊዜ ምን ዓይነት ተስፋዎችን እንደሰነቀ ማሰብ የሚቻልም ይመስለኛል። በተለይም በዕለት ጉርስ እጦት ለከፋ ችግርና ስቃይ ተዳርጎ የሚገኘውን ዝቅተኛ የኑሮ ሁኔታ ውስጥ ያለውን ሰፊ ህብረተሰብ ተደራሽ ያደረጉ ተግባራዊ ጥረቶችን ማንሳትና ሂደታቸውን መገምገም የአስተዳደሩ ጥረትና ትግል እስከየት እንደሚጓዝና ለውጥ ለማምጣት እንዴት ያለ አቅም እንዳለው በቂ ግንዛቤ ይሰጠናል።

አጥብቀው ሲጨብጡት ከአንድ ጉርሻ የማያልፍ መጠን ያለውን ዳቦ እስከ 5 ብር በሚደርስ የመሸጫ ዋጋ ለህብረተሰብ ስታቀርብ በነበረች "የግፈኞች መፈንጫ ከተማ" ባለ መቶ ግራም ዳቦን በ75 ሣንቲም ማቅረብ እንዲቻል ተብሎ የተጀመረውና ስራው እየተቀላጠፈ የሚገኘው አዲስ ፕሮጀክት በአዲሱ ከተማ አስተዳደር ታቅዶ የተዘጋጀ እንጂ "ህዝባዊ ውክልና ነበረው በሚባለው የቀድሞው ካቢኔ" የታሰበ አይደለም። ለውጡ በየቤታችን እንዲደርስ የታለመለት ፕሮግራም እንጂ ለመሪዎች ፕሮፓጋንዳ ፍጆታ እንዲውል የታለመለትም ሆኖ አይታይም። የአዲስ አበባ የመንግሥት ት/ቤት ተማሪዎችን የት/ቤት ዩኒፎርም (የደንብ ልብስ) እና የትምህርት ቁሳቁስ ለመሸፈን የተጀመረው ስራ ብዙ ድካምና ልፋትን የሚጠይቅ ከመሆኑ በተጨማሪ ለህብረተሰባችን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት የሚኖረው የላቀ ፋይዳ በገንዘብ ብቻ የሚተመን አይደለም። በተለይም የተማሪ ወላጆችን "እፎይ!" በማስባልና ጭንቀትን በመቀነስ በኩል ያለው ሥነልቦናዊ ጠቀሜታ በቀላል ዋጋ አይተመንም። ሁሉንም የመንግሥት ት/ቤቶች የማደስና በአዲሱ ዓመት አዲስና ንፁህ መልክ እንዲላበሱ የማድረግ፣ አልፎም ምቹ የትምህርት መስጫ ማዕከሎች እንዲሆኑ የማስቻሉ ዘመቻም ከዘመን መለወጥ ጋር ተያይዞ የሚታሰብ የአንድ ሰሞን ጉዳይ ብቻ ተደርጎ ሊወሰድ አይችልም። ይልቁንም በተማሪዎች አዕምሮ ውስጥ የሚፈጥረው የመለወጥ፣ የትምህርት ተነሳሽነትና የመነቃቃት ሥነ ልቦናዊ ጠቃሚ ፋይዳው በምንም የማይተካና ታላቅ ዋጋ ያለው ነው።

በቀደሙት ዘመናት በኢትዮጵያ የተማሪዎች ታሪክ ውስጥ አንፀባራቂና እጅግ ግዙፍ ሀገራዊ ጠቀሜታ ያስገኙ የነበሩ የብቁ ትውልድ ማፍሪያ የትምህርት ማዕከላት ተረት ሆነው ደብዛቸው ጠፍቶ በሚገኝበት በዚህ ጊዜ ዘርፈ ብዙ ችግር ውስጥ ያሉ ታዳጊዎችን ተቀብለው በአዳሪ የትምህርት ፕሮግራሞች ለማስልጠን የሚያስችሉ ት/ቤቶችን ወደ ማቋቋም የተሻገረውና ከቀጣዩ ዓመት ጀምሮ ፕሮግራሙን በተግባር ላይ ለማዋል እየሰራ ያለው የከተማይቱ አስተዳደር ለነዋሪዎቹ ሁለንተናዊ ጥቅም አሳቢና ወገናዊ ተቆርቋሪነት የሚሰማው ስለመሆኑ ለመገምገም ይህን ተግባሩን በምሣሌነት አለማንሳት አይቻልም። ፕሮግራሙ ከፍተኛ የገንዘብ አቅምን፣ ተከታታይነት ያለው ልዩ ትኩረትን የሚፈልግ መሆኑን እያወቀ ወደ ስራ መግባትን የመረጠው የከተማዋ አስተዳደር ይህ ተግባር "በከተማዋ ሁለንተናዊ ለውጥ አመጣለሁ" ብሎ የገባውን ቃል የሚያስመሰክርለት ነው። የከተማዋ ስራ አጥ ወጣቶችን ወደ አምራችነት አስገብቶ እራሳቸውን እንዲችሉ ለማድረግ ከሰሞኑ የተጀመረውን ስራ አለማድነቅም ከባድ ነው።

የፅሁፌ መነሻ የአስተዳደሩን ተግባራዊ እንቅስቃሴዎችና ተጨባጭ ውጤቶች በግርድፉ መዳሰስና ከዚህ አንፃር ምስጋና ቢጤ ማቅረብ ባይሆን ኖሮ ባላነሳኋቸውና በሌሎች ለጊዜው ባልተጠቀሱ ተግባራት ላይ ጥልቅ ትንተኔና ፍተሻ ማድረግ እችል ነበር። ቢሆንም ግን የጠቀስኳቸውን ብቻ በማየትና በመገምገም ምን ተሰራ? ምን እየተሰራ ነው? ምን ለመስራት ታቅዷል? ለሚለው በቂ ምላሽ ማግኘት ይቻላል፡ ፡ እዚህ ጋር በድጋሚ ለመግለፅ የምወደው የአስተዳደሩ ም/ከንቲባና ካቢኔያቸው በህዝብ የተመረጠ ባለመሆኑ ህጋዊ አይደለም ለተግባራቱም ዕውቅና አንሰጥም በሚሉ ወገኖች ላይ "ምንም ዓይነት የተቃዋሚና የድጋፍ ሀሳብ" የለኝም። የተመረጡትስ ምን ሰርተው አልፈዋል? ብዬ ለመጠየቅ ግን ድፍረት አላጣም። ከተሰራው ስራ አንፃር በመነሳት ብቻ አስተዳደሩን "አመሰግናለሁ" ለማለትም ጊዜ አላጠፋም።


# የኢትዮጵያ ዩኒቨርስቲዎች የክብር ዶክትሬት

**አለማየሁ ባዘዘው**

የክብር ዶክትሬት ዲግሪ መስጠት ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በተለይም ለዩኒቨርስቲዎች ከተቀባዩ በላይ ክብርን የሚያስገኝ እንደሆነ ምሁራን ያምናሉ፡፡ የክብር ዶክትሬት ዲግሪው ከሚበረከትለት የሀገር ባለውለታ የበለጠ ሰጪው ዩኒቨርስቲ የራሱን ተቋማዊ ክብርና ዝና ከፍ የሚያደርግበትን ዕድል እንደሚሰጠውም በግልፅ ሲናገሩ ይደመጣሉ፡፡ ይሁንና ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በተለያዩ የኢትዮጵያ ዩኒቨርስቲዎች የታየው የክብር ዶክትሬት ዲግሪ አሰጣጥ ሁኔታ ከምርጫው ጀምሮ ችግር የሚታይበት እንደሆነ አስተያየት ሲሰጥበት ቆይቷል፡፡ በተለይም በክልል ከተሞች የሚገኙ የመንግሥት ዩኒቨርስቲዎች ዘርን መሠረት ያደረገ የሚመስል ምርጫ ሲያደርጉ መስተዋላቸውና አልፎ አልፎም ይህ ታላቅ ትርጉም ያለው የክብር ስያሜ (ሽልማት) ከሰሩት ስራ አንፃር ለሚበዛባቸው ሰዎች ሲሰጥ መታየቱ ብዙዎች ለሽልማቱ የነበራቸውን የገዘፈ አመለካከት ጥያቄ ውስጥ እንደከተተው መታዘብ ይቻላል፡፡

ቀደም ባለው ጊዜ የክብር ዶክትሬት ዲግሪ የመስጠትን ታላቅና የተከበረ ሥርዓት በሀገራችን መስጠት የጀመረው የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ እንደሆነና ሌሎቹ የሀገራችን ዩኒቨርስቲዎችም ይህን ሥነ ሥርዓት ማከናወን የቀጠሉት የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲን ተሞክሮ መነሻ በማድረግ ስለመሆኑ በግልፅ የሚታወቅ ሲሆን፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲም ቢሆን ከሽልማቱ ጋር ተያይዞ ብዙ ትችቶች ሲቀርቡበት ቆይቷል፡፡ ለሀገርና ለህዝብ የላቀ ፋይዳ ያላቸውን ተግባራት በተሰማሩበት የሙያ መስክ ላከናወኑ ከልዩ ልዩ የሙያ ዘርፍ ለተመረጡ ሰዎች ይህን የክብር ሽልማት ማበርከት በራሱ ችግር አለው ተብሎ የሚታሰብ ባይሆንም ብዙዎቹ ተሸላሚዎች የተሸለሙበት የዕድሜ ገድብ (የእርጅና ዘመን) እና አልፎም የሽልማቱን ክንውንና ያለውን ታላቅ ትርጉም ከእርጅና የተነሣ በማያገናዝቡበት ጊዜ የመሆኑ እውነታ ግን ዩኒቨርስቲውን በስፋት ሲያስተቸው መቆየቱ ይታወሣል፡፡

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በሰሩት የላቀ ተግባር “ክብር ይገባቸዋል” ብሎ የክብር ዶክትሬት ዲግሪ መስጠት በጀመረባቸው ዓመታት የዚህ ክብር ተቋዳሽ እንዲሆኑ ካደረጋቸው ባለውለታዎች መካከል አብዛኛዎቹ የዚህን ሽልማት ምንነት ተረድተው፣ በስራቸው ያገኙት መሆኑ ገብቷቸውና አገራቸው አገልግሎቻቸውን አስባ የምታከብራቸው እንጂ ውለታ በል አለመሆኗን ያስመሰከረችበት እንደሆነ አምነው ደስታውን በቅጡ ያጣጣሙ ነበሩ ማለት የሚቻል አይመስለኝም፡፡ ብዙዎች በእርጅና ብዛት መቆም አቅቷቸው በተሽከርካሪ (ዊልቸር) ላይ ሆነው ከመታየታቸው ባሻገር ስለተሰጣቸው ክብርና ስለቀረበላቸው የባለውለታነት ዕውቅና እና ምስጋና ብዙም








የገባቸው ሆነው አለመገኘታቸው በዩኒቨርስቲው ላይ የሰላ ትችት እንዲቀርብ ምክንያት ሆኖ ቆይቷል፡፡ በኢትዮጵያ ሙዚቃ ታሪክ ውስጥ የሴቶች ፈር ቀዳጅ የነበሩት ክብርት ዶክተር እማማ ንጋቷ ከልካይ፣ ሥነ ፅሁፍን መልካም ምግባር ያለው ሀገሩን የሚወድ አምራች ዜጋ ለማፍራት የተጠቀሙበት ባለውለታችን ክቡር ዶክተር ደራሲ ከበደ ሚካኤል፣ የፍቅር እስከ መቃብር “ፈጣሪው” ክቡር ዶክተር ሀዲስ አለማየሁና ሌሎችም ባውለታዎች ሽልማቱን ያገኙት እጅግ ዘግይቶ ከመሆኑም በላይ በዚህ የክብር ስያሜ እየተጠሩ በህይወት የቆዩበት ጊዜም በጣም አጭር ነበር፡፡

በዚህ ሁኔታ ላይ ብዙሃን ትችትና አስተያየትን በክፋት መሰንዘራቸው የፈጠረው መልካም አጋጣሚ መኖሩ አጠያያቂ አይደለም፡፡ ባለውለታዎችን ማክበርና ማመስገን የሚገባው “በጉብዝናቸው ጊዜ፣ በደህና ሁኔታ ላይ እያሉ መሆን አለበት” የሚለው የዜጎች ተደጋጋሚ አስተያየት አሁን በግልፅ እያየን ላለነው “መልካም የሰሩትን በጊዜ የማክበር” ሁኔታ የራሱ አስተዋፅኦ እንዳለውም አያጠራጥርም፡፡ በክልል ዩኒቨርስቲዎች የታየው ዘርን መሰረት ያደረገ አክብሮት ግን ሌላ ራስ ምታት ከመሆን አልዳነም፡፡

በኦሮሚያ ዩኒቨርስቲ የሚገኝ የመንግሥት ዩኒቨርስቲ የኦሮሞ ተወላጅ የሆነን ሰው መርጦ መሸለሙ፣ የአማራው የአማራ ተወላጅን፣ የትግራዩ ከትግራይ የተወለደውን እየመረጡ የክብር ዶክትሬት ዲግሪ የመስጠትን ስልት መከተላቸው ዛሬም በክብር ዶክትሬት ዲግሪ ክብር እና በዩኒቨርስቲዎቹ የዕውቀትና ምርምር ማዕከልነት ላይ ጥያቄ ከማስነሳት አልጸዳም፡፡ ቢሆንም ግን ካለመስጠት መስጠት፣ ካለማክበር ይልቅ ባለውለታን ማክበር በምንም የማይተካ ዋጋ ስላለው የክብር ዶክትሬት ዲግሪ ከነችግሮቹም ቢሆን መሰጠቱ መቀጠል እንዳለበት ሙሉ እምነት አለኝ፡፡

## ዘንድሮ እነማን ሸለሙ?

የኢትዮጵያ ዩኒቨርስቲዎች በዘንድሮ ዓመት በዩኒቨርስቲዎቻቸው ትምህርታቸውን ሲከታተሉ የነበሩ ተማሪዎቻቸውን ባስመረቁ ባቸው ሥነ ሥርዓቶች ለሀገርና ለህዝብ የላቀ ጥቅም የሰጡ ተግባራትን ከውነዋል ላሏቸው ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጅ ለሆኑ የውጭ ሀገራት ዜጎች የክብር ዶክትሬት ዲግሪ ሽልማትን ሰጥተዋል፡፡ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የባህር ዳር ዩኒቨርስቲ፣ የድሬድዋ ዩኒቨርስቲና የወላይታ ዩኒቨርስቲ የክብር ዶክትሬት ዲግሪ ለመስጠት ያስቀመጧቸውን መስፈርቶች በሚገባ አሟልተው ተገኝተዋል ላሏቸው ከልዩ ልዩ የሙያ መስኮች ለተመረጡ ምሁራንና ባለሙያዎች ሽልማቱን አበርክተዋል፡፡

## አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የክብር ዶክትሬት ዲግሪ ሽልማትን በመስጠት በሀገራችን ቀዳሚ (ጀማሪ) የሆነው የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ዑለማዎች ዳዕዋና ፈትዋ ም/ቤት ሰብሳቢ ለሆኑት ተቀዳሚ ሙፍቲ ሀጅ ዑመር ኢድሪስ እና ለኢትዮጵያ አየር መንገድ ዋና ስራ አስፈፃሚ ተወልደ ገብረ ማሪያም የክብር ዶክትሬት ዲግሪ ሽልማትን ጠ/ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ በክብር እንግድነት በተገኙበት ደማቅ ሥነ ሥርዓት አበርክቷል፡፡

**ሐጅ ዑመር ኢድሪስ፡-** በወሎ ክፍለ ሀገር ወረኢሉ ወረዳ የተወለዱት ተቀዳሚ ሙፍቲ ሐጅ ዑመር ኢድሪስ ገና በ8 ዓመታቸው ነው ▶

ቁርዓንን መማር የጀመሩት፡፡ የአርሶ አደር ልጅ በመሆናቸው በልጅነታቸው በእርሻ ስራ ከመሰማራት አልፈው በንግድ ስራ ውስጥ በመግባትም ለረጅም አመት ሠርተዋል፡፡ በትምህርት በኩል የሀይማኖት ትምህርትን እስከ ከፍተኛ ደረጃ ድረስ የተማሩ ሲሆን የሃይማኖት ትምህርት በማስተማርም የላቀ ክብርና ተቀባይነትን ለማግኘት ችለዋል፡፡ ከ50 በላይ የሃይማኖት መፅሐፍትን በመፃፍ ህዝበ ሙስሊሙን የጠንካራ ሀይማኖት ባለቤት እንዲሆንና ስለሀይማኖቱ በጥልቀት እንዲያውቅ አስችለዋል፡፡ ቅዱስ ቁርዓንን በመተርጎም የሃይማኖቱ ተከታዮች ስለእምነታቸው በደንብ እንዲያውቁ ከመርዳታቸውም በተጨማሪ ስለ አገር አንድነትና መቻቻል አበክረው አስተምረዋል፡፡

በሙስሊም ሃይማኖት ተከታዮችና በሀይማኖቱ ተቋማዊ መሪዎች አለመግባባት ተፈጥሮ በነበረ ጊዜ ሁሉም አንድ እንጂ የተለያዩ አለመሆናቸውን አጠንክረው በማስተማር በመካከላቸው ሠላምና መረጋጋት እንዲሰፍን ሌት ተቀን ሣይደክሙ የለፉ ሲሆን፣ ሀገራችን ወደ አላስፈላጊ ትርምስ እንዳትገባ እረፍት አልባ ጥረት በማድረግ ችግሮቹ በእርቅ እንዲፈቱ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክተዋል፡ ፡ በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ዑለማ ጉባኤና የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ተቋማዊ ለውጥ የጋራ ኮሚቴ ሊቀመንበር ሆነው አገራዊና ሀይማኖታዊ ሀላፊነታቸውን በላቀ ብቃት እየተወጡ የሚገኙት ቀዳሚ ሙፍቲ ሐጅ ዑመር ኢድሪስ ዕውቀታቸውን ሳይቆጥቡና ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ለሀገር ሠላምና መረጋጋት ላበረከቱት አስተዋፅኦ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የክብር ዶክትሬት ዲግሪ ተበርክቶላቸዋል፡፡

**አቶ ተወልደ ገ/ማሪያም፡-** የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሆነው በመስራት ላይ የሚገኙት አቶ ተወልደ አየር መንገዱ በአጭር ጊዜ ውስጥ መላውን ዓለም መድረስ በቻለበት አቅሙ ላይ እንዲደርስና ከአፍሪካ ቀዳሚው አትራፊና ሀያል ተቋም እንዲሆን ማስቻላቸው በአደባባይ ተመስክሮላቸዋል፡፡

ከዛሬ 30 ዓመት በፊት ዕቃ የመጫንና ማራገፍ (cargo) ሥራን የሚሰራው የካርጎ ትራፊክ ሀንድሊንግ ዲፓርትመንት አባል በመሆን አየር መንገዱን የተቀላቀሉት አቶ ተወልደ በስራ ላይ ባሳዩአቸው ውጤታማ የስራ ክንውኖች በየጊዜው ዕድገት እያገኙ እስከ ዋና ሥራ አስፈፃሚነት የደረሱ ናቸው፡ ፡ አሁን ላሉበት የዋና ስራ መሪነት ስልጣን ከመብቃታቸው በፊትም በማርኬቲንግ እና ሴልስ እንዲሁም በሌሎች የተቋሙ የስራ ክፍሎች ውስጥ የረጅም ዓመት ግልጋሎት ሰጥተዋል፡፡

በልዩ ልዩ የሀገሪቱ ዋና ዋና የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ድርጅቶች ውስጥ የቦርድ አባል በመሆን የሰሩት አቶ ተወልደ ገ/ማሪያም የፓን አፍሪካ አቪየሽን ኢንሼቲቭ ሊቀ መንበር፣ በተመድ ዋና ፀሐፊ ሥር የሚገኘው የአየር ትራንስፖርት ደህንነት ቡድን ከፍተኛ አማካሪ በመሆንና በሌሎችም ለአገርና ለዓለም የላቀ ፋይዳ ባላቸው የስራ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ቀጥተኛ ተሳታፊ ሆነው ከማገልገላቸው በተጨማሪ አየር መንገዱ ከፍተኛ ዝና ካላቸው አለም አቀፍ ተቋማት ከ20 በላይ ሽልማቶችን እንዲያገኝ በማስቻል ተቋሙ እጅግ ታላቅና ዝነኛ ሆኖ በዓለም ሁሉ እንዲታወቅ አስችለዋል፡፡

ቀደም ሲል በኢኮኖሚክስ የትምህርት ዘርፍ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ያገኙት አቶ ተወልደ ከዩናይትድ ኪንግደም ኦፕን ዩኒቨርስቲም በቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን የማስተርስ ዲግሪያቸውን ተቀብለዋል፡፡ ሶስት አስርት አመታትን በዘለቀው ጥረታቸውና ልፋታቸው አየር መንገዳችን በአለም ሁሉ ፊት በታላቅ ክብርና ግርማ የሚቆም እንዲሆን በማስቻላቸውና አየር መንገዱ ከኢትዮጵያ መልኮች እንደ አንዱ ሆኖ እንዲታሰብ በማብቃታቸው ዘንድሮ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የክብር ዶክትሬት ዲግሪ ተበርክቶላቸዋል፡፡

## ባህር ዳር ዩኒቨርስቲ

የባህርዳር ዩኒቨርስቲ የዘንድሮ ዓመት ተመራቂዎቹን በደማቅ ሥነ ሥርዓት ባስመረቀበት ወቅት ለሶስት የሀገር ባለውለታዎች የክብር ዶክትሬት ዲግሪ ሽልማት አበርክቷል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ዶ/ር ሰገነት ቀለሙ ኢትዮጵያዊ ሲሆኑ፣ ሁለቱ ማለትም ፕ/ር ሀንክ ማትሰንና ሚ/ር ማርክ ጌልፈንድ የውጭ ሀገራት ዜጎች ናቸው፡፡

**ዶ/ር ሰገነት ቀለሙ፡-** በጎረቤት ኬኒያ የሚገኘው የናይሮቢ አለም አቀፍ ግብረ አካል እና ሥነ ምህዳር ማዕከል የመጀመሪያዋ ሴት ዋና ስራ አስፈፃሚ ሆነው የሚሰሩት ዶ/ር ሰገነት የዕፀዋት ዝርያን ከምድር በሚያጠፉ በሽታዎች ላይ ሳይንሳዊ ምርምር በማድረግ ቀዳሚ ሴት ተመራማሪ ለመሆን የበቁ ናቸው፡፡ በሰሜን አሜሪካና በላቲን አሜሪካ በዚህ ዙሪያ በርካታ ምርምሮችን ያደረጉ ሲሆን፣ የምርምር ስራውን ከ25 ዓመት በላይ ሲያከናውኑ መቆየታቸው ይነገራል፡፡ ለእኚህ ከሀገር አልፎ ለመላው ዓለም የላቀ ፋይዳ ባለው የምርምር ስራ ውስጥ ለቆዩት ኢትዮጵያዊት የባህር ዳር ዩኒቨርስቲ የክብር ዶክትሬት ዲግሪ ክብርን አጎናፅፏቸዋል፡፡

**ፕሮፌሰር ሃንክ ማትሰን፡-** እኚህ ታላቅ ሰው በዜግነት ስዊድናዊ ሲሆኑ በኢትዮጵያ ምድር በተለይም በባህርዳር ዩኒቨርስቲ ውስጥ የመሬት አስተዳደርን በሚመለከት በርካታ የጥናት ውጤቶችን አበርክተዋል፡፡ በምስራቅ አፍሪካ የሚታየውን የመሬት ችግርና ከዚሁ ጋር ተያይዞ በየጊዜው የሚከሰተውን ግጭት በሚመለከት ሰፊ ጥናት ያደረጉ ሲሆን ጥናታቸው ለቀጠናው ሠላምና የሕዝቦች መረጋጋት ትልቅ ፋይዳ እንዳለው ተነግሯል፡ ፡ ለእኚህ በጎ ለመስራት ሠው መሆን ብቻ በቂ መሆኑን በተግባር ላሳዩ ተመራማሪ የባህርዳር ዩኒቨርስቲ ዘንድሮ የክብር ዶክትሬት ዲግሪ ሰጥቷቸዋል፡፡

**ሚ/ር ማርክ ጌልፋንድ፡-** እኚህ አሜሪካዊ የበጎ ምግባር ባለቤት በኢትዮጵያና በሌሎች ታዳጊ ሀገራት የሳይንስ፣ የቴክኖሎጂ፣ የምህንድስና እና የሒሳብ ትምህርቶች ለሀገር ዕድገት የላቀ ፋይዳ ያላቸው በመሆኑ የተለየ ትኩረት እንዲሰጣቸው ድጋፍ ሲያደርጉ የቆዩ ሲሆን፣ በተለይም በባህርዳር፣ በጎንደር፣ በአዲስ አበበና በሌሎች 12 ዩኒቨርስቲዎችና አካባቢዎች የስቲም ማዕከላት እንዲከፈቱ ብርቱ ጥረትና ድጋፍ በማድረግ የተሳካ ተግባር ፈፅመዋል፡ ፡ በእነዚህ ሀገራዊ ጠቀሜታ ባላቸው ታላላቅ የቅን መንፈስ ተግባሮቻቸውም የባህርዳር ዩኒቨርስቲ የከበረውን የክብር ዶክትሬት ዲግሪ ሸልሟቸዋል፡፡

## ድሬድዋ ዩኒቨርስቲ

በዘንድሮው ዓመት በተለያዩ የትምህርት ዘርፎች ያሰለጠናቸውን 2817 ተማሪዎች ሰኔ 29 ቀን 2011 ዓ.ም ያስመረቀው ድሬዳዋ ዩኒቨርስቲ ተግባራቸው ለሀገርና ለህዝብ የላቀ ፋይዳ አበርክቷል ላላቸው ለአርቲስት አሰገደች አስፋው እና ለድምፃዊ አሊ ቢራ የክብር ዶክትሬት ሰጥቷል፡፡

**አሰገደች አስፋው፡-** ሴቶች በየትኛውም የሙያ መስክ አደባባይ እንዳይወጡ ከፍተኛ ማኅበራዊ ተፅዕኖ ይደረግበት በነበረባት የቀደመችው ኢትዮጵያ ውስጥ ይህን ማኅበራዊ ጫና ተቋቁመው ራሳቸውን ለትልቅ ክብር ካበቁ የስነ ጥበብ ሰዎች መካከል አንዷና ከቀዳሚዎቹ ጋር ስማቸው የሚጠቀስላቸው ወ/ሮ አሰገደች አስፋው በብዙሃን ዘንድ "ዓይን የተፈጠረው ሁሉን ለማየት ነው" በተሰኘ የሙዚቃ ስራቸው ይታወቃሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ እጅግ በርካታ ተወዳጅ የሙዚቃ ተወዳጅ የሙዚቃ ስራዎች ያሏቸው አርቲስት አሰገደች በመድረክ ቴአትር ትወና፣ ውዝዋዜና መሰል የኪነት ዘርፎች ተሳታፊ በመሆን ሁለገብ አርቲስት ሲሆኑ የድሬዳዋ ዩኒቨርስቲ ለሰሩት ስራ እውቅና ለመስጠት የክብር ዶክትሬት ሸልሟቸዋል፡፡

**አሊ ቢራ፡-** በኦሮሚኛ ቋንቋ እየዘፈኑ የቋንቋው ተናጋሪ ባልሆኑት መላው ኢትዮጵያውያን ዘንድ ተደማጭና ተወዳጅ ለመሆን ከቻለው ድምፃዊ አሊ ቢራን የማያውቅ አለ ተብሎ አይገመትም፡፡ አሊ ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ በሁሉም የኢትዮጵያ አቅጣጫ ከፍተኛ ተቀባይነትን እና እጅግ የላቀ ተወዳጅነትን ለማግኘት የቻለ ዝነኛ ድምፃዊ ነው፡፡ በሙዚቃ ውስጥ በኖረባቸው ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ በሚሆኑ ጊዜያትም ለቁጥር የሚያታክቱ የሙዚቃ ስራዎችን አበርክቷል፡፡ ተወልዶ ባደገባት ድሬድዋ ከተማ የሚገኘው የድሬዳዋ ዩኒቨርስቲም ዘንድሮ ከሁሉ የላቀውን የክብር ዶክትሬት ዲግሪ ሽልማት አጎናፅፎታል፡፡

## ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ

ከመዲናችን አዲስ አበባ በ3 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው ወላይታ ሶዶ ከተማ የተንጣለለ ሰፊና ንፁህ ጊቢ ይዞ ሰላማዊ የትምህርትና የምርምር ማዕከልነቱን በተግባር ያረጋገጠው ወላይታ ዩኒቨርስቲ እስካሁን በኢትዮጵያ ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ ተደጋግሞ የታየው የተማሪዎች ዘርን መሠረት ያደረገ ግጭት ለአንዴም እንኳን ያልተከሰተበት በመሆን የዩኒቨርሰቲው አስተዳደር ስሙ በበጎ እየተነሳ ይገኛል፡፡ ይህ ዩኒቨርስቲ ሐምሌ 6 ቀን 2011 ዓ.ም ባከናወነው የተማሪዎች ምረቃ ደማቅ ሥነ ሥርዓት በወላይታና አካባቢው በግብርና እና አፈር ጥበቃ ላይ የላቀ አስተዋፅኦ ላበረከቱት አራት ግለሰቦች የክብር ዶክትሬት ዲግሪ ሸልሟል፡፡

## አንደበት



"አየር መንገዱ ከመንግስት ገንዘብ ሳይጠይቅ በደንብ እየሰራ እያለ ለምንድን ነው ለመሸጥ የሚቸኮለው፡፡ መሸጥስ ከታሰበ መንግስት ከአየር መንገዱ የሚያገኛቸው ጥቅሞች ይቀራሉ ወይስ ይቀጥላሉ የሚለው ሁሉ ቢታይ ይሻላል፤ ባንቸኩልም መልካም ነው፡፡ እንዲያውም አየር መንገዱ ከዚህም በላይ ብዙ ነገር ማድረግ የሚችል ነውና መተው ነው የሚሻለው፡፡ አየር መንገዱ በ2025 ያወጣውን እቅድ ከአራት ዓመት በፊት አስቀድሞ ይጨርሳል፡፡ ከታሰበው በላይ እየሄደ ነው፡፡"

አቶ ግርማ ዋቄ አዲስ አድማስ
/የቀድሞው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ሥራ አስፈፃሚ/
አዲስ ዘመን ሐምሌ 13 ቀን 2011 ዓ.ም



"በዚህ የመንጋ አስተሳሰብ፤ እኔ በትግርኛ ቋንቋ ሚዲያ እንዳልቀርብ ተደርጓል፡፡ በትግርኛ ቋንቋ እኔ ስላለኝ አቋምና ሀሳብ፣ ለትግራይ ህዝብ ማቅረብ ነገር ግን አልቻልኩም እኔንና ጄነራል ጻድቃን ‹‹ የትግራይ ጠላቶች ናቸው›› የሚል ዘመቻ እስከ ወረዳ ድረስ ከፍተውብን ነበር፡፡ ከሀለት ዓመት በፊት ይሄ የመንጋ አስተሳሰብ ነው፡፡ ጡረታ ከወጣሁ 20 ዓመት ሊሆነኝ ነው፡፡ በእነዚህ ጊዜያት ውስጥ አንድም ቀን በትግርኛ ቋንቋ፣ በትግራይ ሚዲያ ቀርቤ የመናገር እድሉን አላገኘሁም፡፡"

ሜጀር ጀነራል አበበ ተ/ሃይማኖት
/የቀድሞ የአየር ሃይል አዛዥ ሜጀር ጄነራል/
አዲስ አድማስ ጋዜጣ ሐም 13 ቀን 2011 ዓ.ም



"ከምሽቱ 1፡58 ሰዓት ላይ ስደውልለት አነሳልኝ፡፡ ‹‹ አሳምነው ምንድነው የምሰማው? ›› ብዬ ጮህኩበት፡፡ ‹‹ አይ ኢንጂነር ተመታታን፤ ›› አለኝ፡፡ ምን? ተመታታን? ምንድነው የምታወራው? ንገረኝ እንጂ ስለው፣ ‹‹ እያረጋጋሁ ነውና እደውልልሃለሁ፤ ›› ብሎ ስልኩን ዘጋ እየነገርኩህ ያለሁት፡፡ እስከ ምሽቱ 4፡15 ሰዓት ድረስ ስደውል ስልኩ ተይዟል ይላል፡፡ መጨረሻ ላይ አምባቸው መሞቱን አረጋገጥኩ፡፡"

አቶ አምሳል ጌትነት ከበደ /ኢንጅነር፣ የቀድሞ ፖለቲከኛ/
ሪፖርተር ጋዜጣ ሐምሌ 14 ቀን 2011 ዓ.ም



"ግን አንድ እውነት ልንገርህ ሀገር ቤት ያለው የስልጠና ሲስተም ብዙም አይመቸኝም፤ በተለይ ለእንደ እኔ አይነቱ ወጣ ያለ ባህሪ ላለው አሰልጣኝ ፍፁም ምቹ አይደለም፡፡ ሁሉም እንደሚያውቀው ገንዘብ ለመቀራመት ብዙዎች አሰፍስፈው ሲጠብቁ በቡድን ተደራጅተው ስስተም ዘርግተው ሲንቀሳቀሱ ታያለህ፤ አንተ የዚያ ሲስተም አካል ካልሆንክ በስተቀር ያንን አጥር አልፈህ በሙያህ ለመስራት ነገሮች ሁሉ ፈተናዎች ናቸው፡፡ ይሄ ነገር እኔም በሙያዬ ሀገሬ እንዳላገለግል ገፋፍቶኛል፤ የስልጠና አቅም እውቀትህ ሳይሆን ገንዘብ አፍ አውጥቶ የሚያወራበት ቦታ በመሆኑ ነገሮችን ለእኔ ትንሽ ከባድ አደርጎብኛል፡፡"

አሰልጣኝ አባይነህ ማሞ
ሀትሪክ ጋዜጣ ሐምሌ 17 ቀን 2011 ዓ.ም


# እንኳን ደስ አለሽ !

# Congratulation!

እሁድ ሐምሌ 21 ቀን 2011 ዓ.ም ከሊድ ስታር ዩኒቨርስቲ በቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን የማስተርስ ዲግሪሽን በክብር የምትቀበይው

**ወ/ሪት ጽዮን ኃ/ማርያም**


እንኳን ለዚህ አበቃሽ! ቀሪ ዘመንሽ የተባረከ ይሁን!

ቤተሰቦችሽ




## አባባል

### ስለ ሼክስፒር



- ሼክስፒር ስትራትፎርድ አፖን አቨን በተባለ ስፍራ በ1564 ዓ/ም ተወልዶ በዚህችው መንደር የሞተ ባለቅኔ ነው፡፡
- የዊሊያም ሼክስፒር ጓደኛና ፀሐፊ የነበረው ቤን ጆንሰን ሼክስፒር መጠነኛ ላቲንና በጣም ትንሽ ግሪክኛ ይችል እንደነበር ገልፆል፡፡ ይህም ዊሊያም በትምህርቱ ብዙ እንዳልገፋ ያመላክታል፡፡
- የየቲያትሮች ፀሀፊ ግን የግሪክንና የሮማን ክላሲክ ፅሁፎች እንዲሁም የፈረንሳይን፣ የጣሊያንና የስፔንን ስነ - ፅሁፍ ቋንቋ ጠንቅቆ የሚያውቅ ሰው ነበር፡፡
- የሼክስፒር ንብረቶች በሙሉ 3 ገፅ በፈጀው የኑዛዜ ቃሉ ውስጥ በጥንቃቄ የተዘረዘሩ ሲሆን፣ ስለ መፅሃፍቶቹና ስለ እጅ ፅሁፉ ግልቦጮቹ ግን የተጠቀሰ ነገር የለም፡፡
- ሼክስፒር የሚለው ስም እውነተኛውን ደራሲ ወይንም እውነተኞቹን ደራሲያን ለመደበቅ ያገለገለ የብዕር ስም ሳይሆን እንዳልቀረ አንዳንዶች ይናገራሉ፡፡ በዚህ ስም ተጠቅመው ይሆናል የሚባሉ ሰዎች ከ60 ይበልጣሉ፡፡

## ለፈገግታ

አባት እንግሊዘኛ እንደማይችል ልጆቹ እንዲያውቁበት አይፈልግም፡፡ ልጆች ደግሞ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ትምህርት የቤት ሥራ እንዲያሰራቸው ይፈልጋሉ፡፡ ልጆቹ በጥያቄ እንዳያፋጥጡት እስኪተኙ ድረስ አምሽቶ መምጣት ጀመረ፤ ሲጠጣ አምሽቶ በስካር መንፈስ ስልክ ይደውልና ሚስቱ ስታነሳ፡-

‹‹ የት ነህ? አትመጣም እንዴ? ስትለው....

‹‹ሸሸሸ ...... ቀስ በይ፤ ፈረንጆቹ ተኝተዋል?››

ዶ/ር ንጋቱ አስፋው ተወልደው ያደጉት በአዲስ አበባ ከተማ ዳግማዊ ምንሊክ ሆስፒታል አካባቢ ነው፡፡ በ1966 ዓ.ም ነበር አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ የመግባት ዕድል ያገኙት፡ ፡ ከወቅቱ አስቸጋሪ ፖለቲካ የሚሸሸጉበት የተደላደለ ቤተሰብ ስላልነበራቸው የዩንቨርስቲ ትምህርታቸውን በማቋረጥ ላስታ አውራጃ የብርሃነ ክርስቶስ ት/ቤት አንደኛ ደረጃ መምህርና ርዕሰ መምህር በመሆን ተመድበውም ሠርተዋል፡፡

በ1969 ዓ.ም ያቋረጡትን ትምህርት ለመቀጠል ባህርዳር ዩንቨርስቲ በማቅናት የአራት ዓመት የዲግሪ ፕሮግራማቸውን በማጠናቀቅ በፖለቲካል ሳይንስ ተመርቀዋል፡፡ በጅማ መምህራን ማሰልጠኛ ለአራት ዓመታት በተለያዩ ዲፓርትመንቶች ሓላፊ ከመሆን ባሻገር የሳይኮሎጂ መምህርም በመሆን ሠርተዋል፡፡

ደርግ ስልጣን ከመያዙና ምሁራን ላይ ከነበረው ጠንከር ያለ የፖለቲካ ልዩነትና ግልፅ የሆነ የፖለቲካ አቋም የተነሳ ችግሮች በመፈጠራቸው ሳይወዱ በግድ የኢሠፓ አባል በመሆን ለአጭር ጊዜ መስራታቸውን የሚናገሩት ዶ/ር ንጋት ፖለቲካውን ዕርግፍ አድርገው ባገኙት የስኮርላሺፕ ዕድል ለመጠቀም በ1980 መጨረሻ ከሃገር ወጡ፡፡ በአሁኑ ሰዓት በተለያዩ የግል ዩንቨርስቲዎች ውስጥ በመምህርነት የሚያገለግሉትና ረ/ፕሮፌሰር የሆኑት፤ ንጋት አስናቀን በፌደራሊዝም ጉዳዮች፣ እንዲሁም በኢትዮጵያ ወቅታዊ ፖለቲካ ዙሪያ የግዮን ጋዜጠኞች ሮቤል ምትኩና ፍቃዱ ማ/ወርቅ እንዲህ አነጋግረዋቸዋል፡፡



# “ፖለቲከኞች በብሄርተኝነት ቫይረስ ሕዝብን እየበከሉ ነው”

## ዶ/ር ንጋቱ አስፋው

**ግዮን፡- ለትምህርት ውጭ ከሄዱ በኋላ ከደርግ ጋር ውዝግብ ውሥጥ የገቡበት ሁኔታ እንደተ ፈጠረ ሰምተናል፡፡ ምክንያቱ ምን ነበር?**

ዶ/ር ንጋት፡- ለትምህርት የተጓዝኩት ምስራቅ አውሮፓ ቡልጋሪያ ነበር፡፡ እዛ በተማሪው ንቅናቂ ውስጥ የተማሪው ከፍተኛ አመራር ነኝ፡፡ በስርዓቱ ላይም ትልቅ ቅዋሜ ነበረን፤ ደርግ በተለይም በእነዛ ታላላቅ ጄነራሎች ላይ የወሰደውን ዕርምጃ ተከትሎ ድጋፍ እንድንሰጠውና የአቋም መግለጫ አውጥተን በፍጥነት እንድንልክለት ሲጠይቅ፤ እኛ ያንን አልተቀበልንም፡፡ ለአገሪቱ ዓይን የሆኑት ጄነራሎች በፋሺስታዊ ተግባር የተገደሉ በመሆናቸው፡፡ እናንተን ደግፈን ፈፅሞ መግለጫ አንሰጥም አልን፡፡

በወቅቱ ትምህርቴን ጨርሼ ነበር፤ እንደ አመራርቴ ውሳኔውን ባለመቀበሌ ከቡልጋሪያ እኔን በደህንነቶች አሳፍነው ወደ ሞስኮ ለመውሰድ ፣ ከሞስኮ በእኛ አየር መንገድ ወደ አዲስ አበባ ለማምጣት ትዕዛዝ መተላለፉን ሰማሁ፡፡ በስኩል ኦፍ ማኔጅመንት ውስጥ ብቸኛ ኢትዮጵያዊ እኔ ነበርኩ፤ ስለዚህ ሕይወቴን እንዲታደጉኝ በመንገር ጉዞዬ በለንደን እንዲሆን ጠይቂ ተቀባይነት አገኘሁ፡፡

**ግዮን፡- የለንደን ቆይታዎ ምን ይመስል ነበር?**

ዶ/ር ንጋቱ፡- ፖስት ግራጁዬትን በመቀጠል በስኩል ኦፍ ሜኔጅመንት ታምስቫለኒ ዩንቨርስቲ ኦፍ ለንደን ማስተርሴን እዛ ጨረስኹ፡፡ ወዲኊ በኃገሪቱ ለውጥ መጣና ሕወሓት ስልጣኑን ሲጨብጥ፣ የድርጅቱ ከፍተኛ አመራሮች ቀርበውኝ አብሬያቸው እንድሰራና ወደ ሃገር ቤት እንድገባ በተደጋጋሚ ይጠይቁኝ ጀመር፡፡

እኔም ሃገሬን እንደማልጠላ፣ ወደ ኢትዮጵያ በመመለስ በራሴ መንገድ እንደምሰራ የእነሱን ፖለቲካ ግን ፈፅሞ እንደማልቀጥል ነገርኳቸው፡፡ ታምራት ላይኔና መለስ ዜናዊ የተማሩ ኢትዮጵያውያንን ለአምባሳደርነት ይፈልጉ ስለነበር በርካታ ሰዎች በዛ መልክ ተመዝግበው ነበር፤ እኔ ግን በተለይም ወያኔ ከኤርትራ ጋር በነበረው አቋም የተነሳ፣ ዓለምን እየዞርኩ “ኤርትራ ከኢትዮጵያ ተገንጥላለች” እያልኩ አንድ የሆኑ ሕዝቦችን ሁለት አድርጌ አላቀርብም በሚል፤ ጥያቂያቸውን ሳልቀበል ቀረሁ፡፡ ከተወሰነ ጊዜ በኋላም ወደ ኢትዮጵያ መጣሁ፡፡

**ግዮን፡- እዚህ ሲመጡ ምን ገጠምዎት?**

ዶ/ር ንጋቱ፡- አስቀድሜ ለኑሮዬ ራሴን አዘጋጅቼ፣ ይህቺን ያለሁባትን ቤት ባለቤቴ ሰርታልኝ፣ በማልቸገርበት ሁኔታ ተዘጋጅቼ ነበር ወደ ኢትዮጵያ የመጣሁት፡፡ እዚህ ከመጣሁ ከአንድ ዓመት በኋላ ባለቤቴ አረፈች፡፡ ይሄ የሆነው በ1990 ዓ.ም አካባቢ ነው፡፡ ሁለት ልጆች አፍርተን ነበር፤ አንድ ወንድና አንድ ሴት፡፡ ወንዱ ፓይለት ነበር፣ የዛሬ አምስት ዓመት ገርጂ አካባቢ በራሱ መኪና የመገልበጥ አደጋ ገጥሞት ነው ሕይወቱ ያለፈው፡፡ ►

እዚህ እንደመጣሁ መከራ ነው በግል ሕይወቴ የተደራረበብኝ፤ ባለቤቴ በሞተች በስድስት ወር አለታ ወንዶ የሚኖር ወንድሜ አረፈ፡፡ እሱ ደግሞ ሁለት ልጆቹን እንዳሳድግ የተናዘዘው ለእኔ ነበር፡፡ ከለንደን መጥቼ ኑሮዬን እዚህ ሳደርግ አስራ አራት ሰው ከእኔ ጋር ይኖር ነበር፡፡ እነዚህን ሰዎች ለማብላትም ሆነ ለማስተማር ግድ መስራት ነበረብኝ፡፡ ግን ስራው በቀላሉ ሊገኝ አልቻለም፡፡ ጎሳዬ ሲጠየቅ፣ የውጭ ቆይታዬ ሲጣራ፤ ብቻ ሰበብ እየተፈለገ ብዙ ደከምኩ፡፡ ጓደኞቼ ወደ አገር ቤት ለመመለስ ስዘጋጅ "ተው ይቅርብህ" ያሉኝ የገባኝ ያኔ ነበር፡፡ ለጊዜው ብፈተንበትም በሂደት ስራዎችን በማግኘቴ ገቢ ያንን ቤተሰብ ማስተዳደር ጀመርኩ፡፡

**ግዮን፡- መጀመሪያ የት መ/ቤት ነበር የተቀ ጠሩት?**

ዶ/ር ንጋቱ፡- አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ በመም ህርነት የተቀጠርኩት በ1990 ዓ.ም አካባቢ ይመስለኛል፡፡ ግን ብዙ ትላልቅ ምሁራንን ያፈሩ ዩንቨርስቲ፣ ኢትዮጵያዊነት ያስከረው ትውልድን ያፈራ ዩንቨርስቲ በጎሳ ተከፋፍሎ፤ ከተማሪ እስከ መምህር በብሔር አደረጃጀት ሲዋቀር መመልከቱ አመመኝ፡፡ ይቅርብኝ ብዬ ጥዬው ወጣሁ፤ አንድ ዓመት እንኳን አልሞላኝም፡፡

በቀጣይ አንድ ካምፓኒ ውስጥ በማናጀርነት ተቀጥሬ ለመስራት ሞከርኩ፤ እሱም አልመጠነኝም ጥዬው ወጣሁ፡፡ ጃክሮስ የሚባል ድርጅት ባለቤቱ የትግራይ ተወላጅ ስለነበረች በእሷ በኩል ስራው ተገኘልኝና እዛ ገባሁ፡፡ እኔ የአስተዳደርና ፋይናንስ መምሪያ ሓላፊ ሆኜ እኔን የሚያዘኝ ተራ የጫካ ታጋይ ሆነ፡፡ ይሄም አልተመቸኝም ተውኹት፡፡

በኋላ ዩኒቲ ዩንቨርስቲ ኮሌጅን ዶ/ር ፍስሃ እሸቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲከፍት አብረን ከጀመርነው ጥቂት ስታፎች መሀል አንዱ እኔ ነበርኩ፡፡ ፖለቲካው ምንም ይሁን ምን የተማረ ኃይል አስፈላጊ በመሆኑ፤ የዩንቨርስቲ ካሪኩለም መምሪያዎችን ሌት ተቀን እያዘጋጀን ነው ዩኒቲን በሁለት እግሩ ያቆምነው፡፡ በፒ.ኤች.ዲ ደረጃ ያለን መምህራን ገና ሲጀመር አስራ ስድስት ነበርን፤ በማስተርስ የሚያስተምሩት ወደ አርባ ይጠጋሉ፡፡ የዲፕሎማ ተማሪዎች በፒ.ኤች.ዲ መምህራን ነበር የሚማሩት፡፡ ይህ ዩንቨርስቲ ከታች ተነስቶ አሁን ያለበት ደረጃ እንዲደርስ በጣው የለፋሁ በመሆኔ በጣም ያኮራኛል፡፡ ዩኒቲ አስር ዓመት ያህል ሠርቻለሁ፡፡

ከዛ ጊዜ በኋላ በተለያዩ የግል ዩንቨርስቲዎች ፖስት ግራጁየት በማስተርስ ደረጃ አስተምራለሁ፤ ኤግዛመር እሆናለሁ፤ አድቫይዘርም እሆናለሁ፡፡ በዚህ ደረጃ ነው እየሰራሁ ያለሁት፡፡

**ግዮን፡- ከመምህርነቱ ውጭ አገር ውስጥ በፖለቲካ ፓርቲ ደረጃ ያደረጉት ተሳትፎስ ምን ይመስላል?**

ዶ/ር ንጋት፡- ኢሠፓ ውስጥ ለአንድ ዓመት ስሞክረው ሶሻሊዝም በእነዛ ሰዎች ይሄን ከመሰለ እውነትም በኢትዮጵያ ውስጥ ያለነው አብደናል ከሚል መደምደሚያ ላይ ነው የደረስኹት፡፡ በኢትዮጵያ ደግሞ ሶሻሊዝም ብሎ የተለከፈው የ1960 ትውልድ እውነትም አብዷል ሰክሯል፡፡ ኢትዮጵያን እስካሁን ለጥፋት የዳረገው የ1960ዎቹ ትውልድ መሆኑ ይገባኛል፡፡እንደመጣሁ ኑሮዬ ራሱ አስቸጋሪ ነበር፤ ስለፖለቲካ ለማሰብ ጊዜውም አልነበረኝም፡፡

ምርጫ 97ን ተከትሎ መንግስት የወሰዳቸው አሳዛኝና አስከፊ ዕርምጃዎች ስርዓቱ በፍፁም ዲሞክራሲያዊ ሊሆን እንደማይችል ስለገባኝ ዶ/ር ነጋሶ፣ ብርቱካን ሚዴቅሳ፣ አንዷለም አራጌና ግርማ ሰይፉን ጨምሮ በርካታ በሳል ፖለቲከኞች የነበሩበትና የፈረሰው አንድነት ለፍትህና ለዴሞክራሲ ፓርቲን ተቀላቀልኩ፡፡ ይሄ ፓርቲ እንዴ እንደፈረሰ ታውቃላችሁ፡፡

በኋላ መ.ኢ.አ.ድ ገብቼ ሞከርኩት፤ እዛም ያለውን ነገር የምታውቁት ነው፡፡ እርስ በርስ ተሰነጣጥቀው ሲጨቃጨቁ ነበር፤ አሁን እንደውም ፈርሷል ማለት ትችላለህ፡፡ የት እንዳሉም አላውቅም፡፡ ከዛ ወዲህ ያለኝን ዕውቀት እያከፈሉ መኖሩ ይሻለኛል ብዬ ተውኩት፡፡ መምህርነቱ የበለጠ ተመችቶኛል፡፡

**ግዮን፡- በደርግ ስርዓት ክ/ሀገር የነበረው መዋቅር አሁን ክልል የሚል ስያሜ ተሰጥቶት አከላሎቹም አወዛጋቢ ሆነዋል፡፡ ካሉት ወቅታዊ ችግሮች አኳያ ፌደራሊዝሙ በምን መንገድ መጓዝ አለበት ይላሉ?**

ዶ/ር ንጋቱ፡- በቀዳማዊ ኃይለስላሴ ጊዜ ጠቅላይ ግዛት ነበር የሚባለው፡፡ ያኔ አስራ አራት ጠቅላይ ግዛት ነበር፣ አስተዳደር ክልል ማለት ነው፡፡ ሸዋ ጠቅላይ ግዛት ወይም ሸዋ ክ/ሀገር የሚባለው የማህበረሰቡ ሰዎች የሚኖሩበት አካባቢ ነው፡፡ የጎንደር ጠቅላይ ግዛት የሚባለው ደግሞ ጎንደሮች የሚያስተዳድሩበት ማለት ነው፡፡ የጎጃም ጠቅላይ ግዛት፣ የትግራይ ጠቅላይ ግዛት፣ የኤርትራ፣ የሲዳሞ ጠቅላይ ግዛት እየተባለ ይሄዳል፡፡

ደርግ ሲመጣ የቀዳማዊ ኃይለ ስላሴን ሕገ መንግስት አጠፋውና የራሱን የኢህዲሪ መርህ አወጣ፡፡ ኢህድሪ ሲወጣ ሕዝብ የሚተዳደርበት ሕገ-መንግስት በመሆኑ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በየመንደሩ ይወያይበት ነበር፡፡ እኔ ራሴ ውጪ እያለሁ የሚያወያዩ ግለሰቦች ከኢትዮጵያ ተልከው መጥተው በባዕድ አገር የምንኖር ኢትዮጵያውያንን አነጋግረዋል፡፡ ግብዓትም ተሰብስቧል፡፡ የደርግ አደረጃጀት ሰፊ ጥናት ተደርጎ፣ በአጠቃላይ 25 ጠቅላይ ግዛት እንዲኖር ነው የተደረገው፡፡ ጎንደር ሁለት ቦታ ሰሜንና ደቡብ ጎንደር፣ ጎጃም ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም በሚል ተለየ፡፡ ሸዋ አራት ቦታ ነው የተከፈለው ፡፡

ራስ ገዝ የሚባል ደግሞ አለ፤ ለምሳሌ ኤርትራ ራስ ገዝ ነበር፣ ትግራይ ምዕራባዊ ትግራይና ምስራቃዊ ትግራይ ራስ ገዝ ነበር፣ ድሬድዋም ራስ ገዝ ነበር፡፡ ይሄ አሃዳዊ ቢሆንም በጂኦግራፊ፣ ተመሳሳይ የኢኮኖሚ ትስስር ያለው፤ ሳይኮሎጂካል ቅኝቱና ባህሉ አብሮ ያለና ከመሰል ተጓዳኝ እውነቶች ጋርተያይዞ የተሰራ ነው፡፡ ደርግ ብሔርን፣ ጎሳን፣ ቋንቋን መሠረት ያደረገ አከላልና አስተዳደርን አልተጠቀመም፤ የአሁኑ ደግሞ ከእነዚህ ሁሉ የተለየ ነው፡፡

**ግዮን፡- እስኪ ልዩነቱን በዝርዝር ያስቀምጡት?**

ዶ/ር ንጋት፡- የአሁኑ በሕገ - መንግስት የተቀመጠ ነው ቢባልም የትኛውም ዜጋ እንደ ኢትዮጵያዊነቱ ሕገ መንግስቱ ላይ ሀሳብ አልሰጠም፡፡ በረቂቅ ደረጃ ሕዝብ በነፃነት መወያየት ነበረበት፤ ይሄ አልተደረገም፡፡ ኢህአዴግ በሕገ - መንግስቱም ሆነ በሰንደቅ ዓላማው ላይ ሕዝብን በትክክል አላወያየም፡፡ እነሱ በርሃ ሆነው የቀየሱትንና ህልማችን ነው ያሉትን የዘር ፖለቲካ ነው ተግባራዊ ያደረጉት፡፡

በዛ የፖለቲካ ፕሮግራም ውስጥ ፀረ ንዑስ ከበርቴ፣ ፀረ ኢምፔሪያሊስት፣ ፀረ ፊውዳሊዝም፣ ፀረ አማራ ብሔር የሚሉ ነጥቦች ማኒፌስቶው ላይ በግልፅ አስቀምጧል፡፡ አማራው ትግራይን የጨቆነ፣ ወደኋላ ያስቀረ፣ ያደቀቀ ነው የሚሉ ዕምነቶች ተይዘው ይሄንን የማጥፋት ፕሮግራም በስርዓቱ ውስጥ አስቀድሞ ተዘርግቷል፡፡ ትግራይን ነፃ አድርገው እንዴት ወደ መሀል አገር እንደመጡ፣ እነማን አማራን እንዲያስተዳሩ፣ እነማን ኦሮሞንና ደቡብን እንዲያስተዳድሩ አድርገው መርጠውና ቀርጸው በቦታው እንዳስቀመጧቸው መመልከቱ በቂ ይመስለኛል፡፡

ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ ሕገ መንግስቱን ተንተርሰው የአከላለል ሲስተማቸውን በቋንቋና በዘር ላይ ስላደረጉ "የእኔ ክልል" የሚለው በሽታና ሰዎችን ለያይቶ የሚያፋጅ ችግር ውስጥ እስካሁን ድረስ ተዘፍቀን እንድንቧቸር አድርገውናል፡፡ ይህ የተሳሳተ ሕገ - መንግስት ዕውን ከሆነበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን ድረስ በሐረር፣ በወለጋ፣ በአርሲ ያለቀው አማራ በርካታ ነው፡፡ በባሌ የተሞከረውና በአሶሳ የሆነውን ሳንረሳ ማለቴ ነው፡፡

ከሕገ - መንግስቱ ባሻገር ፌደራል አወቃቀሩን ብናይ አሜሪካን፣ ናይጄሪያም በፌደራሊዝም ነው የሚመሩት፡፡ የእኛን ፌደራሊዝም ልዩ የሚያደርገው ጎሳና ቋንቋን መሰረት ያደረገ ፌደራሊዝም በመሆኑ ነው፡፡ "የትግራይ ክልል" ስትል ከትግራውያን ውጭ ሌላ ኢትዮጵያዊ የመኖር መብት የለውም ብለህ ደንግገሃል ማለት ነው፡፡ "የአማራ ክልል" ስትል ከአማራው ውጭ ማንም አይኖርበትም ብለህ እየዘጋህ ነው፡፡ ይሄ ትልቅ የአዕምሮ በሽታን የሚያስከትል ጽንፈኛ የሆነና በጣም ያከረረ ብሔርተኛነት ዛሬ በስፋት እንዲፈጠር በር ከፍቷል፡፡

**ግዮን፡- ይሄ ጽንፈኛነት ወይም የአክራሪ ብሔርተኝነት መቋጫ ይኖረው ይሆን?**

ዶ/ር ንጋት፡- ጽንፈኛነቱ የፈለገበት ድረስ ይሂድ፤ ግን መቋጫው ምንድን ነው የሚለው ነው አሳሳቢው፡፡ የሚያዝ የሚጨበጥ ዓይነት አይደለም፡፡ አሁን ላይ ባለው "አብዮታዊ ዴሞክራሲና ልማታዊ መንግስት" በሚለው ቃጭል ውስጥ፤ እነ መለስ ዜናዊ የፖለቲካውን መስመር ቀጥ አድርገው ይዘው አቆይተውታል፡፡ ሁሉንም በአንድ ጎሳ የበላይነት ይዘውት፤ እፍን በማድረግ ሕዝቡን መሄጃ አሳጥተውት ኖረዋል፡፡

▶አሁን የሚስተዋሉትን ችግሮች ለመፍታት ከቋንቋና ጎሳ አደረጃጀት በመውጣት፣ ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ ሰጥተኸው መንዝና ከደርግ የአስተዳደር አወቃቀር አብዛኛውን ነገር ወስደህ፣ አሁን ካሉት የሕግ ማዕቀፍ ውስጥ የተወሰኑትን መርጠህ በማዋሃድ አንዱ ሌላውን ከሚያገልበትና “የእኔ ክልል ነው” ከሚል ስሜት በማውጣት ከዚህ በፊት ወደ ነበረው የአንድነት ስሜት መመለስ ስንችል ነው እነዚህ ነገሮች የሚቀሩት። ያለውን ሕገ-መንግስት ከላይ አንስተህ እስከ መደምደሚው ብታነበው አንዱ ከአንዱ ጋር ይጋጫል፡ ፡ ሲሰራ የኖረው ከአንድነት ይልቅ በልዩነት ስለነበር፤ እንዲህ እርስ በርስ የተከፋፈለች ሀገር እንድትሆን የዛሬ 26 ዓመት ገደማ የጸደቀው በችግርና በሴራ ፖለቲካ የተጠላለፈ ሕገ - መንግስት ጉልህ አስተዋፅኦ አበርክቷል ባይ ነኝ።

ዩጎዝላቪያ፣ ክሮሺያ፣ ሞንቴኔግሮ፣ ቦስኒያ ሄርዞ ጎቪኒያ፣ ሰርባኒሳ፣ ሰርቢያን የመሰሉ አገሮች አሉ የራሳቸው ቋንቋ የትም ያላደረሳቸውና በዚህ ምክንት ለመፈራረስ የበቁ። ወደ 1.6 ሚሊዮን ሕዝብም በዚህ ሂደት ውስጥ ለዕልቂት ተዳርጓል። በርስ በርስ ጦርነቱ ማለት ነው፤ ተጠያቂ ያደረጉት ሰርቢያን ነው።

**ግዮን፡- ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ብሔርተኝነት ትልቅ ችግር እየፈጠረ ነው። አሁን ያለው የጎሳ ፖለቲካ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ አያመዝንም?**

ዶ/ር ንጋቱ፡- እኔ የአዲስ አበባ ልጅ ነኝ፣ አስተዳደጌም ሆነ የትምህርት ቤት ሕይወቴ ከብዙ የሀገሪቱ ክፍሎች ከመጡ ልጆች ጋር ነው። ጓደኝነታችን ዘርን መሰረት ያደረገ ሳይሆን መልካምነትንና ባህርይን የተመረኮዘ ነበር። እኔ በፊት ስለአማራነቴ ምንም የማውቀው ነገር አልነበረም፣ ቤተሰቦቻችንም ጠይቀን አናውቅም። እነሱ የኖሩትም ሆነ እኛን ያሳደጉን ክብሯንና ሉዓላዊነቷን ጠብቃ ስለኖረች ኢትዮጵያ ብቻ ነው። ከውጭ ከመጣሁ በኋላ ነው “እከሌ የወለጋ ልጅ ነው፣ እከሊት እኮ የጎንደር ልጅ ናት” የሚለው መጠሪያ “ኦሮሞ ነው፣ አማራ ነው፣ ትግሬ ነው” በሚል ተተክቶ ያገኘሁት።

ብሔርተኝነት በእኔ ዕምነት ትልቅ በሽታ ነው፤ የታመመ ሰው ነው በዛ መንገድ የሚጓዘው። ብሔርተኝነት ሙሉ ለሙሉ አገር ያጠፋል፡ ፡ አይቻልም እንጂ ብሔርተኝነትን በሕግ መከልከል ነው የሚያስፈልገው፤ ምንም አይጠቅምም። በአፍሪካ ኬንያ፣ ናይጄሪያና ኤርትራን የመሳሰሉ አንዳንድ አገሮች ውስጥ በሃይማኖትና በጎሳ መደራጀት ክልክል ነው። እኔ በዲሞክራሲዊ ስርዓት የሀሳብን የበላይነት መቀበልና ማስረዳት ያስፈልጋል፤ ሕዝብ በኋላ ምስክርነቱን ወይም ዳተኝነቱን ይስጥ የሚል አቋም ነው ያለኝ።

በፖለቲካል አስተሳሰብ እጅግ ኋላ ቀር በሆነ ሃገር፣ የትምህርትና የጤና ዘርፉ ወደ ኋላ የቀረን ሰዎች፣ የተለያየ ባህል ያለን ሰዎች፣ 85% የአገሪቱ ሕዝብ ገና ከግብርና ያልወጣ ሕዝብ ውስጥ፤ ይሄን የዘረኝነትና የብሔር ፖለቲካ መስበክ ማለት አንድ ሊድን የማይችል ቫይረስ ሕዝብ ውስጥ መርጨት ማለት ነው፡ ፡ ፖለቲከኞች በብሄርተኝነት ቫይረስ ሕዝብን እየበከሉ ነው። ነገር ግን ወቅቱን ጠብቆ የብሔር ፖለቲካ ጥያቄ ማንሳቱ ተገቢ ነው።

አሁን ለምሳሌ ሰሜን አየርላንድ፣ ዌልስ፣ ስኮትላንድ ከብሪታንያ ለመለየትና ነፃ ሀገር ለመሆን ጠይቀዋል። በስፔን ካታሎናውያን ጥያቄ አቅርበዋል። ከዩጎዝላቪያ መለየት አለብን የሚሉት ስድስት ሀገሮችም በጣም የዳበሩ ናቸው፣ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ወደፊ ተራምደዋል። ከራሺያ አስራ አምስት ሪፐብሊክስ ወጥተው ራሳቸውን እያስተዳደሩ ነው። ዩክሬን፣ አዘርባጃን፣ ጆርጂያ፣ ኡዝቤኪታን የሚባሉት በጣም ወደ ፊት ሄደዋል። እኛ ግን ምንም አማራጭ የሌለን ነን፤ ከምንም በላይ በብዙ መንገድ እርስ በርስ የተሳሰርን ነን። አፋሩ ጨው ቢዘጋ ወለጋው ከየት ነው የሚያመጣው? አዲስ አበባዎችስ ጨው ከየት ልናገኝ ነው? አፋሩ ደግሞ በዛው መጠን ከአማራው የሚወስደው አለ፤ አንዱ ያለ አንዱ በእኛ ሃገር መኖር አይችልም።

ወደ ፊት ምናልባት የማደግና የመዘመን ደረጃ ላይ ስንገኝ ልንደርስ የምንችልበትን ነገር ዛሬ ላይ እያነሱ በብሔርተኝነት እርስ በርስ እንድንጨራረስ እየተደረገ ነው። እንዳልኩት እነዚህ ጥያቄዎች ወደ ኋላ ዕድገትን ጠብቀው የሚመጡ ናቸው። አሁን ተዛዝለን ድህነትን ማሸነፍ፣ ተጋግዘን የምንበላውን ከመስራት ባሻገር የጋራ ሰላማችንን መጠበቅና ማቆየት ነው ያለብን።

አንዱ አንዱን ሳይጫን ሕይወትን የሚገፋባትን የአኗኗር ዘዴ መፍጠር፣ ፍትሃዊ የኢኮኖሚ ክፍፍል፤ ትክክለኛና እኩልነትን መሰረት ያደረገ ፍትህ፣ የተመጣጠነ የትምህርትና የጤና አገልግሎት መስጠትና ሲገባን በጣም ጽንፍ በያዘ ብሔርተኝነት ውስጥ እየናወዝን እንገኛለን። እዚህ ላይ አንድ የማልዋሸው ነገር፤ እኔ የአማራን ብሔርተኝነት አጥብቄ እደግፋለሁ።

**ግዮን፡- ለምን? ከላይ ከገለጹት የኢትዮጵያዊነት ጋር አይጋጭም?**

ዶ/ር ንጋት፡- አማራው በጣም ተጎድቷል፤ ማንም አሳቢ አልነበረውም። ወያኔ ለመግዛት ሲል ባዋቀረው ኢህዴን/ብአዴን አማካይነት ብዙ ግፍ ተፈፅሞበታል። እነ ታምራት ላይኔ “ከአማራ ክልል ውጪ ያለውን አማራ አናውቅም” እስከማለት ደርሰው ነበር እኮ። “ሸርጣም የሚልህን ህዝብ ዝም ብለህ ታያለህ?” ያሉም ናቸው። አሩሲ፣ ወለጋ፣ ቤኒሻንጉል፣ ጋምቤላ ውስጥ አማራ ተጨፍጭፏል፡ ፡ ሕዝብ ሃይማኖቱን ስለሚያከብር ፣ እንደታወጀው አዋጅ የአማራ ሕዝብ አላለቀም፡ ፡ በሃይማኖቱ ላይ አማራ እንደተዋረደው ሌሎቹ አላዋረዱትም።

አሁን የመጣው “አማራ ተጎድቷል፣ እንጠብቀው፣ እንደግፈው” የሚለውን አካሄድ እደግፋሁ። ይሄን መደገፍ ከኢትዮጵያዊነት ጋር አይጋጭም። ጽንፈኛም አያስብልም። ከዚህ ከወጣና እኔ ብቻ የበላይ ልሁን የሚል የአክራሪነትና የፈላጭ ቆራጭት ስሜት ያለበት ብሔርተኝነት ከተፈጠረ ነው አደጋ የሚሆነው።

ብሔርተኝነት ቫይረስ ነው የሚል እምነቴ እንዳለ ሆኖ፤ ሌላው እንደፈለገ እየተጓዘ፣ ከፍ ከፍ እያለና የራሱን ፖለቲካ ባሻው መንገድ እያራመደ አማራው ጋር ሲደርስ “ጽንፈኛ” የሚለው ስም ሊሰጠው አይቻልም፤ አይገባምም ነው የምለው። የአማራ ሕዝብ አኩሪ ታሪክ ረክሶ፣ የምንሊክ ስራዎች ረክሰውና ተዘንግተው፣ ያ አኩሪ ሰንደቅ ዓላማ ረክሶ፣ ሁሉም የየራሱን ፖለቲካ ሲያራግብ፣ ሃይማኖትን መሰረት ባደረገ መልኩ ቤተ ክርስቲያንና ካህናት ሲቃጠሉ ዝም ብሎ ከመመልከት፤ እንዲህ ዓይነቱን አንድ ብሔር ነጥሎ የማጥቃት ዘመቻ በተደራጀ መልኩ ለመከላከል፣ ሕጋዊ መስመርን መከተል አግባብነት አለው። ከዚህ መስመር ሳትወጣና ፈር ሳትለቅ መንዝ ብቻ ልክ ብቻ ዕውነታ ይኖርሃል።

**ግዮን፡- እነዚህ በእርስዎ የሚጠቀሱት ግፍና በደሎች፤ በሌላው ብሔር ላይም ላለፉት በርካታ ዓመታት ሲደርሱ የኖሩ ናቸው።**

ዶ/ር ንጋት፡- ትክክል። በደሉ ደርሷል፤ ኢትዮጵያዊ እስከሆንኩ ድረስ የሁሉም የብሔሮች በደልና ስቃይ ይመለከተኛል። ነገር ግን አማራን አግልለህ ወይም ገፍተህ የሚሰራ ፖለቲካ በዚች ሃገር መኖር የለበትም ፤ ግን ተሰርቷል እያልኩህ ነው፡፤ ▶

**...ብሔርተኝነት ቫይረስ ነው የሚል እምነቴ እንዳለ ሆኖ፤ ሌላው እንደፈለገ እየተጓዘ፣ ከፍ ከፍ እያለና የራሱን ፖለቲካ ባሻው መንገድ እያራመደ አማራው ጋር ሲደርስ “ጽንፈኛ” የሚለው ስም ሊሰጠው አይቻልም፤ አይገባምም ነው የምለው...**

**ግዮን፡- አሁን ከለውጡ በኋላ ባለው አንድ ዓመት ይሄ ነገር አለ ብለው ያምናሉ?**

ዶ/ር ንጋት፡- አለ፡፡ በከሚሴ፣ በማጀቴና በአጣዬ የተሰራው ስራ እኮ ፈፅሞ ትክክል አይደለም፡፡ በ21ኛ ክፍለ ዘመን ቤተ ዕምነትን ማቃጠል፣ አንድ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይን ዘቅዝቅህና አቃጥለህ መግደል ትክክል አይደለም፡፡ እነዚህን ነገሮች በኦጋዴን አይተናል፡፡ በወለጋ ውስጥ የሆነውን ተመልክተናል፡፡ በአሶሳ የደረሰው መፈናቀልስ ተገቢ ነበር? በእነዚህ ቦታዎች ሁሉ አማራውን ታርጌት ባደረገ መልኩ ግፍ ተፈፅሟል፡፡ በጌዲኦና ጉጂ የተሰራውን በሚሊየን የሚቆጠር ተፈናቃይ ብታይ የአማራ ተወላጅ ውስጡ አለ፡፡

በርግጥ የብሔር ፖለቲካ በዚህ አንድ ዓመት ውስጥ ስር ሰዷል፡፡ ይሄ ለውጥ በግፍ የተሰራን ስራ እንዳጋለጠ፣ የፖለቲካ ዕስረኞችን እንዳ ስፈታ ሁሉ ተያያዥ ችግሮችንም ወልዷል፡፡ ኢህአዴግ "ስህተት ሰርተናል" ብሎ በይፋ መመስከሩና ይቅርታ መጠየቁ በእጅጉ የሚደነቅ ቢሆንም፤ መሠረታዊ ለውጥ ግን በፓርቲውም ሆነ በሀገሪቷ ላይ እስካሁን ድረስ የለም፡፡ ጥገናዊ ለውጥ ብቻ ነው የተደረገው፤ እሱ ደግሞ ቀደሞ ስልጣን ላይ የነበረው ስርዓት በዘረጋቸው ጠንካራ ኔትዎርክ አማካይነት ለውጡን ለመቀልበስ የተለያዩ ቦታዎች ችግር እየፈጠረ ነው፡፤ ለእዚህ ደግሞ ዕድል የፈጠሩት ስልጣን ላይ ያሉት አካላት ናቸው፡፡

**ግዮን፡- እንዴት?**

ዶ/ር ንጋት፡- አንዳንድ ጊዜ የፈለገ የአስተሳሰብ ለውጥ ቢያስፈልግም መሪ ስትሆን ኮምጠጥ ብለህ የምትሄድበት ጉዳይም አለ፡፡ ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ 22 ባንክ ቤቶች እስኪዘረፉ መጠበቅ አልነበረባቸውም፡፡ ከጅምሩ ጠራርጎ መክተት ቢችል ስህተቱ ተደጋጋሚ አይሆንም፡፡ ያ ብር ተዘርፎ ወዴት ነው የሄደው? ዘራፊ የተባሉት ትክክለኛ ሰዎችስ እነማን ናቸው? እስካሁንስ ለፍርድ ቀርበዋል? ሁሉም ነገር ግልፅ መሆን አለበት፡፡

በቤኒሻንጉል፣ በጌድኦ፣ በመከላከያው ውስጥም ሆነ በየትኛዋም ቦታ ለተሰሩ ጥፋቶች አስቀድሞ መንግስት መለሳለስ በማሳየቱና ቆፍጠን ያለ ዕርምጃ ባለመውሰዱ፣ ክፍተቶችንም መድፈን ባለመቻሉ የመጡ ናቸው፡፡ ይሄ መለስለስ ወደ ውድቀት ነው የሚያመራው፡፡ ባለፉት አስራ ሁለት ወራትና ከዛ ባይ መንግስት የተጓዘበት መንገድ በጣም የላላ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ሀገሪቱ በየቦታዋ በችግሮች እንድትናወጥ አድርጓል፡፡

አሁን በየቦታው ራሳቸውን የተለያየ ስያሜ እየሰጡ ቄሮ፣ ፋኖ፣ ኢጄቶ፣ ዘርማ እያሉ ሁከት የሚፈጥሩት ወጣቶችን ከተሳሳተ ፖለቲካና ከአሳሳች ብሔርተኞችና ልሂቃኖች ለማራቅ መንግስት በቂ የስራ ዕድሎችን መፍጠር ይኖርበታል፡፡ ስራ አጡ ከመጠን በላይ በሆነበት ሃገር በየዓመቱ ከዩንቨርስቲዎች የሚመረቁ በመቶ ሺህዎች የሚቆጠሩ ወጣቶችን መመልከት እየተለመደ ነው፡፡ ሁሉም ቁጭ ብሎ በሚውልበት ሂደት ውስጥ አስቀድመን ከጠቀስናቸው ነጥቦች ጋር በተያያዘ ወደ ፊትም ችግር መፈጠሩ አይቀሬ ነው፡፡ ስለዚህ መንግስት በተቻለ መጠን በያሉበት ክልል እነዚን ወጣቶች እያደራጀ፣ በስራ ራሳቸውን የሚለወጡበትን ሁኔታ ቢያመቻች መልካም ነው፡፡

**ግዮን፡- ሰሞነኛውን የሲዳማ የክልልነት ጥያቄና እሱን ተከትሎ የተፈጠረውን ችግር እንዴት አዩት?**

ዶ/ር ንጋት፡- እንዲህ ዓይነቱን ጥያቄ ሲዳማ፣ ወላይታ፣ ጉራጌ፣ ጌዲዮ፣ ሀዲያና ከንባታ ዳውሮ ጨምሮ የተለያዩ ዞኖች አቅርበዋል፡፡ ይሄ ደግሞ ሕገ - መንግስቱ የሚፈቅድላቸው መብት ነው፡፡ ሌሎቹን ትተን ወደ ሲዳማ ስንመጣ፣ ሲዳማ ከቀበሌ ገበሬ ማህበር እስከ ዞኑ አስተዳደር ጠይቋል፤ ተቀብሎታል፡፡ ከዞኑ አልፎ የክልሉ መንግስት ም/ቤት ተቀብሎታል፡፡ ጉዳዩን ወደ ምርጫ ሄዷል፤ እዛ ደግሞ የሰው ኃይል አባላት አልተሟሉልኝም የሚል ምላሽ ተሰጥቷል፡፡ ይሄ ደግሞ ጥያቄውን ባቀረበው ወገን ላይ ቅሬታ ፈጥሯል፡፡

በሕገ - መንግስት የክልልነት ጥያቄ ሲነሳ በግልፅ የተቀመጡ አንቀፆች አሉ፤ የሚ መለስበት የራሱ የሆነ መንገድ አለ፡፡ በዛ መሰረት ሕጉ ክልልነትን ይፈቅዳል፡፡ ለምንድን ነው የሲዳማ ጥያቄ ዝግ የሚሆነው? ለሚለው ሕገ - መንግስቱ ሃገሪቷን በሚያጠፋ መንገድ የተቀረፀ በመሆኑ ነው፡፡

ሰሞኑን ጥያቄውን ለመተግበር የተሄደበት መንገድ ደግሞ ብጥብጥ አስነስቶ በርካታ ሰዎች ሕይወታቸውን አጥተዋል፡፡ የተወሰደው የአስቸኳይ አዋጅ የሰዎቹን ጥያቄ ለማገድ ሳይሆን፤ በዚህ መከላከል ውስጥ ሊመጣ የሚችለውን ጥፋት ለማርገብ ይመስለኛል፡፡ ትክክልም ነው፡፡ ሕገ - መንግስቱ "እኛ



የተገፋን ቀን ዕውን ይሆናል" በሚል ይህቺን ሃገር ለመበታተን ሆን ተብሎ የተዘጋጀ ሕገ መንግስት ነው፡፡ የአፈፃፀም ችግር፣ የሰው ኃይል እጥረት፣ ምናምን የሚለው ምላሽ ለሽፋን የተሰጠ ነው፡፡ ግን ምንም ተባለ ምን በሕገ - ወጥ መንገድ ውሳኔ ለማሳለፍ ታስቦ በተያያዥነት የተፈጠረው ችግር በጣም ያሳዝናል፡፡

ለዚህ መፍትሔ የሚሆነው ሕገ - መንግስቱን በጥልቀት ማየት መፈተሽና ማስተካከል ነው፡፡ "ሕገ መንግስቱ ከተነሳ ሀገር ትፈርሳለች" የሚል ኃይል አለ፡፡ "ሕገ መንግስቱም፤ ሰንደቅ ዓላማውም አይወክለንም" የሚል ሌላ ኃይል አለ፡፡ በሶስተኛ ደረጃ "ሕገ መንግስቱ ሊያፈርሰን ነው፣ ሊያጠፋን ነው" የሚል ኃይልም አለ፡፡ የት ጋር ነው ያለነው? ግራ ያጋባል፡፡ ይሄ ሕገ - መንግስቱ እንዳይነካበት የሚፈልገው፣ ከብሔርተኝነት በላይ ጽንፈኛ የሆነው አካል ነው፡፡ በእንዲህ ዓይነቱ አተካሮ ከመተላለቃችን በፊት ሕገ - መንግስቱ በትክክል መላው ሕብረተሰብም ሆነ ሙያተኞች በተሳተፉበት መንገድ መሻሻል ይኖርበታል፡፡ ይህቺ ሃገር አደጋ ላይ መውደቅ በሚገባት ሰዓት አደጋ ላይ ሳትወድቅ አልፋ፤ በዚህ ትውልድ እንድትዋረድ አልፈልግም፡፡

**ግዮን፡- በመጨረሻም የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ ዕድል እንስጥዎት?**

ዶ/ር ንጋት፡- በየብሔሩ ብዙ ኤሊቶች አሉ፤ ከሃገር አልፈው ለዓለም የሚበቁ በርካታ ኢትዮጵያውያን በሃገሪቷ አንድነትና ሰላም ላይ ከመቼውም ጊዜ በላይ ተግባብተውና ልዩነቶቻቸውን አርቀው መስራት ይኖርባቸዋል፡፡ ምሁራን ዝም ብለን መኮፈስ የለብንም፡፡ አማራ፣ ኦሮሞ፣ ትግሬ እያሉ ለመተቻቸት በየሚዲያው ለመወጣት መጣደፍ የለብንም፡፡

እነዚህ ምሁራን የሲዳማ ጉዳይ ላይም ሆነ የሃገሪቷ ሕገ - መንግስት ላይ የራሳቸውን አሻራ በቅንነት እንዲያኖሩ ዕድሉ ከተሰጣቸው ብዙ ነገር መቀየር ይችላሉ ብዬ አምናለሁ፡፡ ነገር ግን አሁን የጎሳ ፖለቲካ የሁሉም መደበቂያ እየሆነ ነው፡፡ ይሄ መቅረት አለበት፡፡ ዛሬ ከስልጣን ከተገፋው ሕወሓት መማር ያስፈልጋል፡፡


በመንግስት ደረጃም ጠ/ሚ/ር ዐቢይ በኢህአዴግ አባል ድርጅቶች መሀል ጥልቅ ውይይት አድርገው ግንባሩ ትክክለኛ ግንባር መምሰል አለበት፤ ምርጫው እውን እስኪሆን ድረስ፡፡ በግንባሩ ውስጥ ያሉ ቫይረሶች ወደ ሕዝብ ይወርዳሉና ይሄንን በፍጥነት ማስተካከል ይጠበቅባቸዋል፡፡

የእዚህ ለውጥ እምብርት የሆኑት የአማራና የኦሮሞ ኤሊቶች ትልቅ ሓላፊነት አለባቸው፡፡ ስልሳና ሰባ ፐርሰንት የያዘውን የሃገሪቱን ህዝብ አንድ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከዛ ውጭ እኔም ሆንኩ ቀሪው የኢትዮጵያ ህዝብ ማን ያስተዳድረን ማን፤ የምንፈልገው ጥሩ ፖሊሲና ጥሩ ሕዝባዊ አገልግሎት እንዲሁም ሠላምን ነው፡፡ ይህ እንዲሆን ሁላችንም የድርሻችንን መወጣት አለብን፡፤

**ግዮን፡- እናመሰግናለን፡፡**

ምልከታ

# ብሔርተኝነት "ቅርስ" እንጂ ማንነት ወይም ዜግነት አይደደለም!



መታሰቢያ መልአከ ሕይወት

በአማርኛ ቋንቋ ቅርስ ብለን የምንረዳው ቃል መጠበቅ ያለበት፤ ከትውልድ ወደ ትውልድ መሸጋገር ያለበትን የሚዳሰስንም፣ የማይዳሰሱ ነገሮች የሚያጠቃልል ሲሆን፤ በተባበሩት መንግስታትም በኩል ይህ ጉዳይ ከፍተኛ ድጋፍ የሚሰጠው ነው፡፡

በማንኛውም ማኅበረሰብ በዘመናት ጉዞ የተፈጠሩና መጠበቅ የሚገባቸው በርካታ ቅርሶች አሉ፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን በመላው ዓለም ከፍተኛ የባህል ወረራ እየተካሄደ በመሆኑ እነዚህ ቅርሶች ከትውልድ ወደ ትውልድ መሸጋገር አቅቷቸው በመጥፋት ላይ ናቸው፡፡ እነዚህን ቅርሶች ለመጠበቅ ከሚደረግ ጥረት ይልቅ የራስን ክልል ወይም አገር ለመመስረት የሚደረግ ከንቱ ትግል በስፋት እየተካሄደ ነው፡፡

የራስን ክልል ወይም ሃገር የመመሥረት ሂደት ለሕዝቦች መፈናቀል፣ ለጦርነት፣ ለድህነት ምንጭ ይሆናል እንጂ መቼም ሊሳካ አይችልም፤ ዓለም ዓቀፋዊ ድጋፍም የለውም፡፡ ምክንያቱም ትናንሽ አገሮች አቅም የሌላቸው የድሕነት፣ የሽብርተኛ፣ የሠላም እጦት ምንጭ ይሆናሉ እንጂ ለሕዝባቸው የሚጠቅም ሥራ መሥራት አይችሉም፡፡

በአፍሪካ ከሁለት ሺ ቋንቋዎች በላይ ያሉ በመሆናቸው መቼም የማይሳካ ቅዠት ከመሆን ውጭ፤ ለሌሎች እጅግ ወሳኝ ለሆኑ ተግባራት (ማለት ድህነትን፣ ኋላቀርነትን ለመዋጋት ለሚደረገው ትግል) ትልቅ እንቅፋትም ነው፡፡

ማንኛውም ማንነቱን የሚወድ ዜጋ በተወለደበትም ቦታ ወይም በሌላ ቦታ ማንነቱን በቅርስነት ለመጠበቅና ሳይጠፉ ከትውልድ ወደ ትውልድ መሸጋገር አቅቶት፣ ብዙ ወላጆች ክልላዊ ቋንቋቸውን እንኳ ለልጆቻቸው ማስተላለፍ ተስኗቸው፣ ሊሳካ የማይችለውን ክልላዊነትንና ሃገር በሃገር ውስጥ የመፍጠር ቅዠት ቢያቆሙ የተሻለ ነው የሚል ዕምነት አለኝ፡፡

ዜግነት የሚገኘው የአንድ ሃገር ነዋሪ በመሆን እንጂ የአንድ ቋንቋ ተናጋሪ በመሆን አይደለም፡፡ እያንዳንዱን ቋንቋ ተናጋሪ በዓለም ላይ የራሱ አገር እንዲኖረው ቢደረግ፣ በዓለም ላይ ከስድስት ሺ በላይ አገሮች ይኖራሉ ማለት ነው፡፡ ይህ ማለት ሁሉም አገሮች ምንም አቅም የሌላቸው፣ ድሃ ሃገሮች ይፈጠራሉ፡ ፡ ለዚህ ነው በአንድ ሃገር ውስጥ አንድ ፓስፖርት የሚኖረው፡፡ ፓስፖርት ደግሞ ዜግነት መገለጫ፣ መታወቂያ ነው፡፡ በሰኔ ወር መጨረሻ ጠ/ሚ/ር ዐቢይ ፓርላማ ቀርበው የሥራ ሪፖርት ሲያቀርቡ የክልል ይገባኛል ጥያቄን አስመልክተው ሲናገሩ "ክልል ለመሆን ሕዝባዊ ሪፈረንደም የሚያካሄደው የምርጫ ቦርድ" እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

ይህ አባባል በመርሕ ደረጃ ትክክል ቢሆንም አንድ ትልቅ ጥያቄ ግን ያስነሳል፡፡ ጥያቄውም አሁን ያሉት ክልሎች በምርጫ ቦርድ በኩል በሪፈረንደም ነው ወይ የተመሰረቱት? ካልሆነስ ሕጋዊ ናቸው? የሚል፡፡

በ1983 ዓ.ም ሕወሓት ኢሕአዴግ ወደ ሥልጣን ሲመጣ ለራሱ በሚመቸው መልክ ክልሎችን አዋቅሮ፣ ሕጋዊ ለማድረግ ተንቀሳቀሰ እንጂ የሕዝቦችን ፍላጎት ምንም ቦታ አልሰጠውም፡ ፡ በተጨማሪም በአንድ ሃገር ውስጥ ዘጠኝ መንግስታትን (ያውም ምንም ዓለም አቀፍ እውቅና የሌላቸው) ፈጠረ እንጂ በሕዝቦች ፍላጎት የተመሰረተ፣ ለልማትና ለመልካም አስተዳደር የሚመች ፌዴራላዊ አወቃቀር አልፈጠረም፡፡ በመሆኑም እኛ ኢትዮጵያውያን ገና ብዙ ያልተሻገርነው ወንዝ አለ፡፡

የኢትዮጵያ ሕገ መንግስት ብሔርተኝነትን ወደ ክልል፣ ክልልን ደግሞ እስከ መገንጠል የፈቀደ ብቸኛ፣ በዓለም ላይ ያለ ሕገ መንግስት ያለን ሕዝቦች ነን፡፡ ይህ ትውልድ ይህንን ፈተና የመወጣት ከባድ ሓላፊነት አለበት፡፡

ባለፉት 28 ዓመታት በተግባር የሆነውን ብንገመግም ፤ ክልሎች መጀመሪያ መመሥረት ከዚያ ቀስ በቀስ የራሳቸውን መዋቅር መገንባት ከዚያ ደግሞ ወታደራዊ ኃይል ማደራጀት ሄዶ፤ አሁን ደግሞ ለማዕከላዊ መንግስት አልታዘዝም ባይነት ስሜት በስፋት እያደበሩ እንደመጡ ሁላችንም መመስከር እንችላለን፡፡

የክልል አመራሮች በአሁኑ ጊዜ ስለ መሬታቸው እንጂ ስለ ባሕላዊ ቅርሳቸው ብዙም ሲጨነቁ አይታዩም፡፡ እኔ ባለኝ መረጃ የራሱ የምርምር ተቋም አደራጅቶ የክልሉን ባህል፣ ጥንታዊ ታሪክ ወዘተ በተገቢው መልኩ እያጠና ያለ ክልል መኖሩን አላውቅም፡፡

ያ ክልላዊ ማንነት እንደ ቅርስ ተጠብቆ መቆየት ሲገባው በቂ ትኩረት ካላገኘ ሙሉ በሙሉ መጥፋቱ የማይቀር ነው ከዚህ በፊት ደጋግሜ ለመግለፅ እንደሞከርኹት ከብሔርተኝነት ይልቅ ሕብረ ብሔራዊነት፣ ማንኛውም ዜጋ በክልሉ ያለ ስጋት መኖር የሚያስችለው በመሆኑ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ለሕብረ ብሔራዊነት ተግቶ ቢሰራ የተሻለ ነው፡፡

ጠ/ሚ/ር ዐቢይ ወደ ስልጣን ከመጡ በርካታ ወራቶች የተቆጠሩ ሲሆን አንድም መሰረታዊ የሆነ ጉዳይ ላይ ሥራ አልተጀመረም፡ ፡ ሕገ መንግስት እንደሚታወቀው በአጭር ጊዜ ተጽፎ የሚፀድቅ ነገር አይደለም፡፡ ሰፊ ውይይት፣ ጥናትና ምርምር የሚጠይቅ ነው፡ ፡ ቢያንስ የሕገ መንግስት ኮሚሽን ተቋቁሞ፣ በተረጋጋ ሁኔታ ሥራ ቢጀመር በእጅጉ መልካም ይመሥለኛል፡፡

ሕገ መንግስቱ "እንዳለ ተቀዶ ይጣል" የሚለውን ሐሳብ እኔ በግሌ አልደግፈውም፡ ፡ ሕገ መንግስቱ ለምሣሌ ዓለም ዓቀፋዊውን የሰብዓዊ መብት ድንጋጌ እንደወረደ የተቀበለ ሕገ መንግስት ነው፡፡ መሻሻል ያለበት ችግር ያለባቸውን አንቀፆች ብቻ ነው መሆን ያለበት፡፡

በዋናነት ዜግነት ከኢትዮጵያዊነት ብቻ እንደሚመነጭ በግልጽ ቋንቋ መቀመጥ አለበት፡ ፡ በርዕሱ ላይ እንደተጠቀሰው ብሔርተኝነት እንደ ቅርስነት ተጠብቆ ሳይጠፉ ለትውልድ እንዲተላለፍ ማድረግ ብቻ ነው የሁላችንም የቤት ስራ መሆን ያለበት፡፡


ይህን ጉዳይ ሳንዴና ለመጨረሻ እልባት አበጅተን፣ ትኩረታችንን ሙሉ በሙሉ በኢኮኖሚ ዕድገት ላይ ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡ መንግስት ደጋግሞ እንደነገረን በክልል የሚገኙ የፌደራል ንብረቶችን ወደ ግል ለማዞር የሚደረግ መኩራ (ይህ ሕገ መንግስት እስካለ ድረስ) መቼም አይሳካም፡፡

ምክንያቱም ክልሎች ፍቃደኛ ላይሆኑ ይችላሉ፡ ፡ መረጃ ያላቸው ባለሀብቶችም በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር አውጥተው በክልሎች ውስጥ ኢንቨስት ያደርጋሉ የሚል ዕምነት የለኝም፡ ፡ ክልሎች በዋናነት የተጠያቂነት ሥሜት የሌላቸው በመሆኑ በባለሀብቶች ላይ ችግር መፍጠራቸው አይቀርም፡፡

በመጨረሻም ማንኛውም ብሔሩን የሚወድ ዜጋ ሊያውቀው የሚገባ ጉዳይ ብሔርተኝነት መቼም ወደ ሃገርነት መለወጥ የማይቻል መሆኑን ተገንዝቦ ወይም ከዚህ ቅዠት ወጥቶ የበለፀገች ኢትዮጵያን ለተተኪው ትውልድ ለማውረስ ተግቶ ቢሰራ መልካም ነው፡፡ የብሔር ፖለቲካ ፓርቲዎች በተቻለ ፍጥነት እንዲፈርሱ ተደርጎ፣ አመራሮቹ የብሔሩን አባላት በማይጨበጥ የብሔር ማንነት ቅዠት የኢትዮጵያን ሕዝቦች እያወናበዱ የራሳቸውን የሥልጣን እና የገንዘብ ጥማት ለማሳካት እንደሚሮጡም በተጨባጭ ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ የቀድሞው ጠ/ሚኒስትር አቶ መለስ "ክልሎች ቢፈልጉ በጀታቸውን ያቃጥሉት" የሚለው አባባል በይቅርታ ሳይዘጋ፤ እስከ አሁን ክልል ያልሆኑ ብሔሮች የክልል ጥያቄ ቢያነሱ ብዙም አይደንቀኝም፡፡ ምክንያቱም ክልል ከሆነ በጀት አለ፤ በጀት ካለ ደግሞ እንደ ልባቸው የሚያግዙት ሀብት አገኙ ማለት ነው፡፡

## *ማረሚያ*

*ባለፈው ዕትማችን "አራት ቢሊዮን ችግኝ ቅዥት ወይስ ሌላ?" በሚለው ርዕስ ውስጥ አንድ ሰው አራት ችግኝ መትከል የሚለው አርባ ችግኝ ተብሎ እንዲስተካከል፤ ለአንባቢያን ለተፈጠረው ስህተት ይቅርታ እንጠይቃለን፡፡*



# “የጠፋው ልጅ”

## ለምን ሲሳይ፤ ዓለም አቀፉ ኢትዮጵያዊ ባለቅኔ

**ብሩክ መኮንን**

ከዛሬ 52 ዓመት በፊት የምስራች ሲሳይ የተባለች ኢትዮጵያዊት ለትምህርት ወደ እንግሊዝ ሀገር ተጓዘች፡፡ ስትጓዝ ብቻዋን አልነበረም፣ በሆድዋ ፅንስ ይዛለች፡፡ የምስራች ሲሳይ በበርክሌይ ከተማ ትምህርቷን እየተማረች የመውለጃ ጊዜዋ ሲደርስ ወደ ላንክሻየር ቢሊንግ ሆስፒታል በማቅናት ሜይ 21 ቀን 1967 ወንድ ልጅ በሠላም ተገላገለች፡፡

የምስራች ልጇን በወለደችበት ሆስፒታል የከተማው የማኅበራዊ አገልግሎት ሰጭ ተቋም ባልደረባ አራሷንና ሕፃንዋን በቅርበት የመከታተልና የመንከባከብ ሥራ እየሰራ፣ ሕፃኑ በዊጋን የማኅበራዊ አገልግሎት ሰጭ ተቋም ስር ለተወሰነ ጊዜ መቆየት እንዳለበት ገልጾ እሷ ግን ልጅዋን ለተቋሙ በአደራ ሰጥታ ወደ ትምህርት ቤትዋ በመመለስ የጀመረችውን ትምህርት እንድትከታተል መወሰኑን በመግለፅ ሀሳቡን እንድትቀበል ያሳምናታል፡፡

በባዕድ ሀገር ያለዘመድ፣ የምታማክረው እንኳን በሌለበት ሁኔታ የምስራች ሲሳይ ልጇን ለተቋሙ በአደራ ሰጥታ፤ ሳትወድ በግዷ ወደ በርክኔል ተመለሰች፡፡ ለሳምንታት እንኳን ከወለደችው ልጇ ተለይታ መቆየት የቸገራት የምስራች፣ ሕጻኑን በአደራ የተረከባት ሚስተር ሞርማን ጎልድትሮፕ ጋር ስልክ በመደወል፣ ደብዳቤ በመጻፍ የአካልዋን ክፋይ እንዲሰጧት ብትሞክርም ሳይሳካላት ቀረ፡፡

በከተማው ምክር ቤት ስር ያለው የማኅበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋም የሥራ ኃላፊዎች ከሚስተር ኖርማን ጎልድትሮፕ ጋራ በመመሳጠር ያለ ወላጅ እናቱ ይሁንታ ኢትዮጵያዊውን ሕፃን ለአንድ እንግሊዛዊ ቤተሰብ በጉዲፈቻ ሰጡት፡፡

ይህ ሕፃን ነው ዛሬ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ታዋቂ ከሆኑ ባለቅኔዎችና ገጣሚያን ተርታ ስሙ የሚጠራው፡፡ የተሳካለት ደራሲ፣ የፊልምና የተውኔት አዘጋጅና አቅራቢ፣ እንዲሁም በማንቸስተር ዩንቨርስቲ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ቻንስለር በመሆን ስመ ገናና ለመሆን የበቃው ለምን ሲሳይን አጠቃላይ የሕይወት ታሪኩን በዚህ ዕትም “የግዮን ባህር ማዶ” አምድ ልናስቃኛችሁ ወደድን፡፡

እጅግ ወግ አጥባቂ ለሆነ እንግሊዛዊ ቤተሰብ፣ “ኖርማን” የሚል ስም ተሰጥቶት በጉዲፈቻ እንዲያድግ የተሰጠው ኢትዮጵያዊ ሕፃን አሳዳጊዎች ክርስትና ካስነሱት በኂላ መጠሪያ ስሙን “ማርክ”፣ የቤተሰቡን መጠሪያ ደግሞ “ግሪንውን” አስብለው ልጁን ተረክበው ማሳደግ ቀጠሉ፡፡

ሶስት ልጆች ያላቸው አሳዳጊዎቹ፣ ኢትዮጵያዊውን ሕፃን ዕድሜው አስራ ሁለት እስኪሆነው ካሳደጉት በኂላ፣ አዘውትሮ ኬክ በመብላቱና አመሻሽ ላይ ብቻውን ከመኖሪያ ቤታቸው በረንዳ ላይ ተቀምጦ መቆዘም በመጀመሩ፤ “ሰይጣን ተጣብቶታል” የሚል ሰንካላ ምክንያት በመስጠት በ12ኛ አመቱ ወደ ዊጋን የማኅበራዊ አገልግሎት ተቋም ወስደው ያስረክቡታል፡፡

አሳዳጊዎቹ አስራ ሁለት አመት ያሳደጉትን ልጅ ለተቋሙ ከመለሱ በኂላ አንድም ጊዜ ተመልሰው ደህንነቱን ለመጠየቅ እንኳን ሳይሞክሩ ደብዛቸውን አጠፉ፡፡

ለአምስት አመታት በአጠቃላይ በከተማይቱ በሚገኙና በአያያዛቸው ረገድ ከወሕኒ ቤት ባልተለዩ “የወላጅ አልባ ሕፃናት” ማሳደጊያዎች እየተዘዋወረ የኖረው ኢትዮጵያዊ ታዳጊ፣ አንድ ጠያቂና የቅርብ ሰው ሳይኖረው በሕፃናት ማሳደጊያ ተቋማቱ ሰራተኞች ከፍተኛ በደል እና የመብት ጥሠት እየተፈፀመበት፣ የቆሻሻ ማጠራቀሚያዎችን፣ መፀደጃ ቤቶችን እያፀዳ፣ በከፍተኛ ሁኔታ እየተንገላታ ዕድሜው አስራ ሰባት አመት እስኪሞላው ድረስ ቆየ፡፡

“በጊዜው ሠላምና እፎይታን ለማግኘት ከቤተ መጽሐፉ በምዋሳቸው መጽሐፍት ውስጥ መደበቅ ብቻ ነበር ያለኝ አማራጭ፡፡ በሕይወቴ ተስፋ እንዳልቆርጥ ያደረገኝ፣ የፅናቴ ምንጭ አስራ ሰባተኛ አመቴን እንዳገባደድኩ ከሕፃናት ማሳደጊያው ያለምንም ቤሳቤስቲን ሊያባርሩኝ ሲሉ፤ ማንነቴና ታሪኬን የተመዘገበበትን የግል ማኅደሬን አስረከቡኝ፡፡

በግል ማኅደሬ ውስጥ በሚገኘው የልደት ሰርተፍኬት ላይ እናቴ ያወጣችልኝ “ለምን ሲሳይ” ተብሎ የተመዘገበ ስሜን፣ የወላጅ እናቴ ስም የምስራች ሲሳይ መሆኑንና ኢትዮጵያዊ መሆኔንም የሚያረጋግጥ ማስረጃ አገኘሁ፡፡

በግል ማኅደሬ ውስጥ ከታጨቁ ማስረጃዎች መሀል እናቴ ገና ከሶስት ወሬ ጀምሮ እስከ አንድ አመቴ ድረስ ለሚስተር ኖርማን ጎልድትሮፕ ልጇን እንዲያገናኙዋትና ወስዳ በሀገሯ ከዘመድ አዝማድ፣ ቤተሰብ ጋራ ልታሳድገኝ እንደ ምትሻ፤ እንዲሁም “በቀለሙ ምክንያትና ልዩነት የመገለል ስሜት እንዲያድርበት ሆኖ ማደግ የለበትምና ልጄን ስጡኝ” የሚል በርካታ ደብዳቤዎችን አግኝቼ እያለቀስኩ አነበብኳቸው፡፡

ሁኔታው ለአመታት በቤተ ሙከራ ውስጥ ለመድኃኒት መሞከሪያና ለምርምር እንደሚረቡ አይጦች አድርጌ ይሰማኝ የነበረ የበታችነት፣ የመገፋት፣ የባይተዋር ስሜቴ ምን ያህል ለስነ ልቦና ጉዳት ዳርጎኝ እንደኖረና እንደጎዳኝ ባሰብኩ ቁጥር ውስጤ በሲቃ ይናጣል፡፡

እንደ በረሃ ዛፍ ብቻዬን አንዱ ሲያላትመኝ፣ አንዱ ከአጎነበስኩበት አንስቶ ሲያጎነኝ ያሳለፍኩት አበሳና ስቃይ ምን ያህል ልቤን እንደሰበረው በአስታወስኩኝ ቁጥር፤ ያቺ የግል ማኅደሬን ባየሁበት ቀን የተሰማኝ፣ የተስፋ ብቻዬን አይደለሁም የሚል ስሜት ለዛሬ እኔነቴ ጉልህ ባለ ድርሻ መሆኑ ይሰማኛል፡፡ ” ይላል ባለቅኔው ለምን ሲሳይ የኂላ ታሪኩን ሲተርክ፡፡

ለምን አስራ ስምንት ዓመት ሲሞላው ወደ ማንችስተር ከተማ በማቅናት በአተርቶን በተባለ ስፍራ ሕይወቱን እንደ አዲስ ሀ ብሎ ጀመረ፡፡ ለምን ሲሳይ 19ኛ አመቱን ከማክበሩ ከወራት ቀደም ብሎም ሥራ አጥ በመሆኑ መንግስት ለመተዳደሪያ ከሚከፍለው ወርሃዊ ድጎማ አጠራቅሞ የመጀመሪያውን የግጥም ስብስብ የያዘች ቅፅ አዘጋጅቶ በማሳተም፣ በጊዜው የስራ ማቆም አድማ አድርገው ለነበሩ ላንክሻየር የማዕድን ማውጫ ሠራተኞች መሸጥን ጀመረ፡፡

በዛው ዓመት በማንችስተር ኮሚኒቲ ሊትሬቸር ዴቨሎፕመንት ወርክ ባለሙያ በመሆን በማንችስተር ማኅበረሰብ አቀፍ አሳታሚዎች ሕብረት ውስጥ የመስራት ዕድልን አገኘ፡፡ በቀጣይ የነበሩት ተከታታይ ሶስት ዓመታት ▶

ያለ እረፍት ወላጅ እናቱን፣ ቤተሰቡን ለማግኘት ፍለጋ ያደረገባቸው ከባድ አመታት እንደነበሩ ለምን ሲሳይ ይናገራል።

ዕድሜው 21 ዓመት ሲሞላ፤ ለሶስት አመታት እናቱን ለማግኘት ያደረገው ፍለጋ ተሳክቶ፣ ወላጅ እናቱ ወ/ሮ የምስራች ሲሳይ በጋምቢያ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ውስጥ ተቀጥረው እየሰሩ እንዳሆነ ባገኘው መረጃ መሰረት፤ ወደስፍራው በመጓዝ ከወላጅ እናቱ ጋራ በአካል ተገናኘ።

ለምን ሲሳይ ከእናቱን የተገናኘበትን ቅፅበት ሲያስታውስ “የተሰማኝ ስሜት ጥልቅ ወደሆነ የውቅያኖስ ክፍል ዘልቆ እንደመግባት ያለ ልገልፀው የሚቸግረኝ ስሜት ነበር የተፈጠረብኝ። ማንም የሌለኝ፣ ባይተዋር፣ እንደ በረሃ ዛፍ ኑሮ ከአንዱ ጥግ ወደ አንዱ የሚያላትመኝ አድርጌ ሳስብ የነበረው እኔነቴ ፈፅሞ ተቀየረ።

ገና ከሕፃንቱ ጀምሮ ከባድ የሆነ ፈተና ውስጥ ወድቄ ነው ያደግሁት። ወላጆቼ ማን እንደሆኑ እንዳላውቅ ተደርጌያለሁ። ሌላው ይቅር ኢትዮጵያዊ መሆኔን እንኳን አላወቅሁም፡ ፡ ከወሕኒ ቤት ፍፁም በማይለዩት የሕፃናት ማሳደጊያ ቤቶች ከአንደኛው ወደ አንደኛው እየተዘዋወርኩ ስሰቃይ የነበረበት ምክንያት ምንድን ነው? ብዬ ራሴን ጠየቅሁ” በማለት ይገለጻል ።

24 ዓመት ሲሆነው በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ታዋቂ ከሆኑ ባለቅኔ ገጣሚዎች ተርታ ለመመደብ የቻለው ለምን ሲሳይ፤ በታዋቂው የብሪታኒያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ባሉት የተለያዩ ቲቪ ቻናሎች በራሱ ሕይወትና አስተዳደግ ላይ ያተኮሩ ሁለት ዶክመንተሪ ፊልሞች፤ እንዲሁም ተከታታይ ድራማዎችን ጽፎ ያቀረበ ሲሆን፣ እነዚህ ስራዎች በቢቢሲ ራዲዮ ቻናል 3 ላይ በተከታታይ የራዲዮ ፕሮግራም በመሆን ቀርበውለታል። በዚህም ሥራው በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ዘረኝነትና መድልዎ የሚያቃጭለው የኪነጥበብ ባለሙያዎች የሚሰጠውን “የእንግሊዝ የእኩልነት ኮሚሽን የመገናኛ ብዙሃን” ሽልማትን አሸንፏል።

በ2007 ለምን ሲሳይ ከሚኖርባት የለንደን ሳውዝ ባንክ ሴንተር የ2012 የለንደን ኦሎምፒክ የመክፈቻ ስነስርዓት ላይ ስራዎች እንዲያቀርብ በእንግሊዝዋ ንግስት ዳግማዊ ኤልዛቤት ተመረጠ። በብሪቲሽ ካውንስል የበላይ ጠባቂነት በብሪቲሽ ፊልም ኢንስቲዩትና በሮያል አካዳሚ ስር የሚካሄዱ የሕፃናት የደብዳቤ አፃፃፍ ውድድሮችን፣ ክለቦችን የማስተባበር ሥራን ለሁለት ዓመታት በሓላፊነት መርቷል።

በ2009 አመተ ምህረት የሀደርስፊልድ ዩንቨርስቲ ለለምን ሲሳይ የክብር ዶክትሬት ዲግሪ ሰጥቶታል። በዚያው አመት የብሪቲሽ ንግስት የተመረጡ የብሪቲሽ ኢምፓየር ምርጥ ባለሙያዎች አንዱ እንደሆነ፣ ለዚህም የሚገባውን ክብር እና ሽልማት በኪንግሃም ቤተ መንግስት በሺዎች የሚቆጠሩ ታዳሚዎች ባሉበት ሰጥተውታል።

የበርካታ መጽሐፍት ደራሲ፣ በራዲዮና በቴሌቪዥን በመቅረብ የተለያዩ ኪነ ጥበባዊ ሥራዎቹ የተላለፉለት፣ በኡርዱ፣ በፖላንድኛ፣ በሶማሊኛ በፐርሺኛ ቋንቋዎች ስራዎቹ የተተረጎመለት፣ ከፍተኛ ተደማጭነት ባላቸው የእንግሊዝ የኤፍ ኤም ራዲዮ ጣቢያዎች የተላለፉለት ትውልደ ኢትዮጵያዊው ለምን ሲሳይ በ2015 የዩንቨርስቲ ኦፍ ማንችስተር የቀድሞ ተማሪዎች፣ መምህራን፣ የአስተዳደር ሠራተኞች እንደዚሁም የዩንቨርስቲው አጠቃላይ የአስተዳደር ጉባኤ ባደረጉት ምርጫ፤ የማንችስተር ዩንቨርስቲ “የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ቻንስለር” ሆኖ ለሰባት ዓመታት እንዲያገለገል ተመረጠ።

በመላው ዓለም ከፍተኛ ተነባቢነትና ተቀባይነት ያገኙ ስምንት መጽሐፍት የታተመለት፣ ስድስት በለንደን እና በእንግሊዝ የቲያትር አፍቃሪዎች አድናቆት ያገኙ የመድረክ ቲያትሮች፣ አራት ረዣዥም የራዲዮ ድራማዎች በተለያዩ የቢቢሲ የሚያስተላልፋቸው የኤፍ. ኤም ራዲዮ ጣብያዎች በተለያዩ ቋንቋዎች ተተርጉመው የተላለፉለት ትውልደ ኢትዮጵያዊው ባለ ቅኔ፣ ጸሐፊ ተውኔትና ገጣሚ፣ ደራሲ ለምን ሲሳይ በ2017 አፕሪል ወር የፋውድሊንግ ሙዚየም የበላይ ጠባቂ ቦርድ አባል በመሆን ተመድቦ በመስራት ላይ ይገኛል።

በማንችስተር ዩንቨርስቲ ቻንስለር በመሆን ከተመረጠ ወዲህ በዩንቨርስቲው የሕግ ትምህርት ቤት ውስጥ የጥቁሮችን ተሳትፎ ለማሳደግ የሚያስችለውን ሰፊ ተግባር እያከናወነ ሲሆን፤ በዚህም ጥረቱ 1200 ትውልደ አፍሪካውያን ካሪቢያን ወጣቶች በድህረ ምረቃ በዲግሪ እንዲማሩ አድርጓል። ከዚህም በተጨማሪ በወንጀል መሰማራትና የተለያዩ ሕገወጥ ተግባራትን በተመለከተ ለምን ሲሳይ “እኔ ኩሩ ኢትዮጵያዊ፤ ኩሩ እንግሊዛዊ ነኝ” ይላል። ወደ አገሩ በመምጣትም በኢትዮጵያ ያሉ ታሪካዊ ቦታዎች፣ እንዲሁም የቱሪስት መስህቦችን ሁሉ እየተዘዋወረ ከመጎብኘቱ በተጨማሪ፤ “ታላቅ ዘመናት ያስቆጠረ ያልተነካ ታሪክና ባህል ያላት ኢትዮጵያ እንደቀድሞ ታሪኳ ገናና ታላቅ እንድትሆን የበኩላችንን መወጣት አለብን፤ ይህ የሁላችንም ተልዕኮ መሆን ይገባዋል” ሲልም ተናግሯል።

**...እጅግ ወግ አጥባቂ ለሆነ እንግሊዛዊ ቤተሰብ፣ “ኖርማን” የሚል ስም ተሰጥቶት በጉዲፈቻ እንዲያድግ የተሰጠው ኢትዮጵያዊ ሕፃን አሳዳጊዎች ክርስትና ካስነሱት በኋላ መጠሪያ ስሙን “ማርክ”፣ የቤተሰቡን መጠሪያ ደግሞ “ግሪንውን” አስብለው ልጁን ተረክበው ማሳደግ ቀጠሉ...**

ለምን ሲሳይ በማንችስተር ዩንቨርስቲና በሌሎች የእንግሊዝ ዩንቨርስቲዎችና ኮሌጆች ለኢትዮጵያውያን ተማሪዎች የትምህርት ዕድል ይሰጡ ዘንድ እየሰራ እንደሆነ፤ በኢትዮጵያ የስነ ፅሁፍና የንባብ ባህል እንዲዳብር ወጣቱ ትውልድ የሀገሩን ታሪክ ያውቅ ዘንድ ከሚጣጣሩ ወገኖች ጋራ በመሆን የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማበርከት እየሰራ ነው።

ትውልደ ኢትዮጵያዊው ለምን ሲሳይ በለንደን የሚገኘው የልዑል አለማየሁ ቴዎድሮስ አፅም ወደ ሀገሩ ኢትዮጵያ ተመልሶ በክብር ማረፍ አለበት የሚል አቋም እንዳለው፤ ለዚህም ሁሉም ኢትዮጵያዊ ሊተባበር ይገባል ይላል፡ ፡ “በማያውቀው ሀገር በማያውቀው ሕዝብ መሐል በብቸኝነት ሞቶ ያረፈው ኢትዮጵያዊ ልዑል፣ በሀገሩ በክብር ሊያርፍ ይገባል የምለው ያለምክንያት አይደለም። እኔ በሰው ሀገር ያየሁት ሊያሳብደኝና ለከባድ አዕምሮ ቀውስ ሊዳርገኝ የነበረውን የሥነልቦና ቀውስን ስለማውቀው ነው” በማለትም የልዑሉ አጽም ወደ ሀገር ቤት እንዲገባ የፈለገበትን ምክንያት ይገልጻል ።

ባለቅኔና ደራሲ፣ የሬዲዮና የቴሌቪዥን አቅራቢ ለምን ሲሳይ ላለፉት ሁለት አስርት አመታት ከእውነተኛ ወላጆቹ ተለይቶ፣ በጉዲፈቻ እንዲያድግ እንዲሁም ማንነቱን እንዳያውቅ አድርገው ለከፍተኛ የስነ ልቦና ቀውስ ዳርገውት የነበሩት የዊጋን ከተማ የማኅበራዊ አገልግሎት ሰጭ ተቋምን ለፈፀሙበት የመብት ጥሰት በሕግ በመክሰስ፣ ተገቢው ቅጣትና ካሳ እንዲከፈለው በመጠየቅ የመሰረተው ክስ ለሁ ለት ዓመታት ሲያየው የነበረው የእንግሊዝ ፍር ድ ቤት በመጨረሻ የፍርድ ውሳኔ ሰጥቷል።

በፍርድ ቤቱ ውሳኔ መሠረትም አንድ ሚሊዮን ፓውንድ የሚደርስ የካሳ ክፍያ ያገኘ ሲሆን፣ ካገኘው ገንዘብ ውስጥ የተወሰነውን ለግሉ የመኖሪያ ቤት በመግዛት ቀሪውን በእንግሊዝ ሀገር በተለያዩ ደረጃ ላይ የሚገኙ የወላጅ አልባ ሕፃናት ማሳደጊያዎች መርጃ እንዲውል አድርጓል።

በ2011 ሰኔ ወር መጨረሻ ላይ ባለቅኔና ደራሲ ለምን ሲሳይ ለአመታት የዘለቀውን የፍርድ ሂደት በተመለከተ ሲናገር “ብዙ ጊዜ በፍርድ ቤት እየታዩ ያሉ ጉዳዮችን በተመለከተ፣ ጉዳያቸው ፍርድ ቤት ያለ ባለጉዳዮች ተስፋ በመቁረጥ ሕይወታቸውን ያጠፋሉ ሲባል ሰምቼ እንዴት ይሆናል እል ነበር። ነገር ግን ራሴ በዚህ ጉዳይ በፍርድ ቤት እየተከታተልኩ ሳለ እንኳ እንደመቅዘፍ ያለ ተስፋ አስቆራጭ ጉዳይ እንደሆነ ተረድቼያለሁ። አሁንም በእኔ ላይ የደረሰው በደልና የመብት ጥሰት በሌላ ላይ እንዳይደርስ መስራቴን እቀጥላለሁ” ብሏል።

በሰኔ ወር መጀመሪያ ሳምንት ለታዋቂው እንግሊዛዊ ደራሲና ጸሐፊ ተውኔት ሀሮልድ ፒንተር መታሰቢያ የተዘጋጀ የ2019 የፔን ኢንተርናሽናል ሽልማትን ትውልደ ኢትዮጵያዊው ባለቅኔ ለምን ሲሳይ አሸናፊ መሆኑን የሽልማት ሰጭው ተቋም ይፋ ያደረገ ሲሆን፤ ለምን ሲሳይ “የጠፋው ልጅ” በሚል የሚታወቀው ኢትዮጵያዊ ለምን ሲሳይ በሚቀጥለው ዓመት ጥቅምት ወር በታላቁ የብሪቲሽ ላይብረሪ በሚካሄድ ደማቅ ፕሮግራም ሽልማቱ ይበረከትለታል ተብሏል።

# ወጣቶች ከልዩነት ጎራ ወጥተው መቀራረብና ትስስር መፍጠር አለባቸው

**ከእሸቱ ደስታ**

ረ/ፕሮፌሰር ሰብስብ ሀዲስ አንድ ሀገር ካሉት ሃብቶች እጅግ የከበረው ወጣቱ መሆኑን ጠቅሰው ወጣቶች በአንድ ሀገር ውስጥ ባላቸው የቀዳሚነት ሚና ለማንኛውም ዓይነት የልማት ፕሮግራም የሚያበረክቱት ግብዓት ለረጅም ጊዜ የሚዘልቅና የትኛውንም ዓላማ ለማሳካት የሚያስችል ነው ብለዋል፡፡

ወጣቶች ለውጤት ከሚያበቃቸው ሚናዎች መካከል ዋናው ራስን ለውጦ መገኘት መቻል መሆኑን የተናገሩት ጽሁፍ አቅራቢው የአመራርነት አቅማቸውን በመረዳትና ራሳቸውን በማስተማር፣ አመለካከታቸውን በመቀየር፣ ትዕግስተኝነታቸውን በማዳበር እና አብሮ የመኖር ጠቀሜታን በመረዳትና ኃላፊነት በመውሰድ እንዲሁም በአካባቢያቸው ላይ ባሉ በልዩ ልዩ አደረጃጀቶች ንቁ ተሳትፎ በማድረግ የሰላምን ድንበር ማስጠበቅ ይኖርባቸዋል ሲሉ አጽንኦት ሰጥተው ገልፀዋል፡፡

ወጣቶች የሰላም መልዕክተኛ በመሆን መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ትስስር በመፍጠርና ከታችኛው የአመራር ክፍል ጋር በጋራብ መስራት እንዲሁም ለዜግነትና ለሥነምግባር ትምህርቶች ልዩ ትኩረት በመስጠት መንፈሳዊ ተሃድሶ ሊያመጡ እንደሚገባቸው ረ/ፕሮፌሰሩ አስገንዝበዋል፡፡



ወጣቶች አስፈላጊውን የማብቂያ እድልና መድረክ ሊፈጥሩና ሊሰጧቸው እንደሚገባ አመልክተው በዚህ ሁሉ ሂደት ውስጥ ሁሉም ወጣቶች በልባቸው ሊይዙትና በሄዱበት ሁሉ ሊያስታውሱት የሚገባ ነገር ሰላም በእጃቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ወጣቶች የመሪነት ሚናቸውን ብሎም ግጭትን የመፍታት ኃላፊነታቸውን ሲወጡ የተፈለገው ውጤት ይገኛል ያሉት ጽሁፍ አቅራቢው ወጣቶችን በሁለንተናዊ መልኩ ተሳታፊ ማድረግ ከተቻለ 21ኛውን ክፍለ ዘመን “የመቻቻል፣ የሰላምና ከግጭት ነፃ የሆነ” ክፍለ ዘመን ይሆናል ብለዋል፡፡

ይገባቸዋል፡፡”

በደሴ ትሮፒካል ኮሌጅ የ2ኛ ዓመት የህክምና ተማሪ የሆነው መሀመድ አስፋው “መሪነት ጥበብ ነው፡፡ መሪ ማለት ራዕይ፣ አላማ ህብረተሰቡን ከጎኑ አሰልፎ እንደ ሀገር ያለውን አሟልቶ የተናገረውን ወደ ተግባር የሚለውጥ በአጠቃላይ ለቃሉ ታማኝ የሆነ ሰው ነው፡፡ ወጣቱ ደግሞ ተስፋና ተራራ ላይ ያለ ስለሆነ ይህንኑ ለማብቃት ዩኒቨርስቲዎች በተከታታይ የስልጠና መድረክ በማመቻቸት መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህ ከተደረገ ወጣቱ ባገኘው የመሪነት ክህሎት ሀገሪቱ ወደተሻለ ደረጃ ያሸጋግራታል፡፡

ኤደን ሰይፉ ትባላለች፡፡ በወሎ ዩኒቨርስቲ የ2ኛ ዓመት ባዮ ቴክኖሎጅ ተማሪና የሰላም ፎረም ፕሬዝደንት ናት፡፡ “ወጣቱ ከስሜታዊነት ነፃ ሆኖ ጥበበኛና አስተዋይ መሆን ይገባዋል፡፡ በሃሳብ አለመስማማት ቢኖር እንኳ ግጭቶችን በቸልታ ማለፍ አይገባም፡፡ ለግጭት መንስኤ የሚሆኑ ጉዳዮች ትንሽ ናቸው ብሎ መናቅ የለብንም ይህን በጊዜው መፍታት ወደ ሰላም ያሸጋግራል፡፡”

በወሎ ዩኒቨርስቲ በቲያትር የ4ኛ ዓመት ተማሪ የሆነችው ሀና ተረፈ በበኩሏ “ሃሳብን በነጻነት ከማንሸራሸር ውጪ ድንጋይ በመወርወር ለውጥ አይመጣም፡፡ አሳፋሪ ተግባርም ነው፡፡ በግጭት አፈታት ላይ ያገኘነው እውቀት ባለመኖሩ ይመስለኛል ችግሩን ለመፍታት ያልተቻለው፡፡ ስለሆነም ለዚህ መፍትሄው የግብረ ገብ ትምህርት ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት እስከ ዩኒቨርስቲ ድረስ መሰጠት አለበት፡፡”

ሰመረ ግርማ ይባላል፡፡ በወሎ ዩኒቨርስቲ በአማርኛ ቋንቋ የ2ኛ ዲግሪ ተማሪ ነው፡፡ “ተማሪውን በአመራር ዙሪያ ከማስተማር በፊት መምህራኖቻችን ማብቃት ያስፈልጋል፡፡ እነሱ ጥሩ መሪ ሲሆኑ እኛም የእነሱን አርዓያ እንከተላለን፡፡ የግጭት ባህላችን ደግሞ በሽምግልና ሽማግሌዎችን ብቻ ባሳተፈ መልኩ ነው የሚከናወነው፡፡ ይሄ በቂ አይደለም፡፡ ወጣቱንም ማሳተፍ ይገባል፡፡”

“በአመራርነትና በግጭት አፈታት ሂደት የወጣቶች ሚና” በሚል ርዕስ ከዩኒቨርስቲውና ከግል ኮሌጆች ለተውጣጡ ተማሪዎች የፓናል ውይይት በወ/ሮ ስህን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ሰኔ 28 ቀን 2011 ዓ.ም ተካሂዷል፡፡ በፓናል ውይይቱ የመነሻ ጽሁፍ ያቀረቡት በወሎ ዩኒቨርስቲ የሶሻል ሳይንስ ኮሌጅ ምክትል ዲን የሆኑት ረ/ፕሮፌሰር ሰብስብ ሀዲስ ናቸው፡፡

**...በወሎ ዩኒቨርስቲ በቲያትር የ4ኛ ዓመት ተማሪ የሆነችው ሀና ተረፈ በበኩሏ “ሃሳብን በነጻነት ከማንሸራሸር ውጪ ድንጋይ በመወርወር ለውጥ አይመጣም... አሳፋሪ ተግባርም ነው... በግጭት አፈታት ላይ ያገኘነው እውቀት ባለመኖሩ ይመስለኛል ችግሩን ለመፍታት ያልተቻለው....**

በሀገራችን የልዩነት ፖለቲካ በተካረረበት በዚህ ወቅት ወጣቶች ከልዩነት ጎራ ወጥተው በመቀራረብና ትስስር በመፍጠር የጋራ እሴቶችን በማጉላት ከትውልድ ትውልድ እንዲተላለፉና የመላ ህዝቡን ትብብር እንዲጠናከር ሚናቸውን መወጣት አለባቸው ሲሉ ጽሁፍ አቅራቢው ተናግረዋል፡፡

ረ/ፕሮፌሰሩ በማጠቃለያቸው የዛሬዎቹ መሪዎች ለነገዎቹ የህዝብ መሪዎች/

የፓናል ውይይቱ ተሳታፊ ከነበሩት የኮሌጅና ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች መካከል የተወሰኑትን አነጋግረን የሚከተለውን ብለውናል፡፡ በወሎ ዩኒቨርስቲ በሥነ ምድር ተመራቂና የክበባት መስራችና ሰብሳቢ የሆነው ተማሪ አህመድ መሀመድ “ወጣቱ በግጭት አፈታት ዙሪያ ያለው ግንዛቤ ዝቅተኛ ነው፡፡ ግጭት በሃሳብና በውይይት ይፈታል፡፡ በዚህ መነሻ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተከታታይነት ባለው መልኩ ለተማሪው ማስተማርና ማሳወቅ


***ኢኒሽየቲቭ አፍሪካ ከላይት ኢትዮጵያ***

***እና ከወሎ ዩኒቨርስቲ ጋር***

***በመተባበር ያቀረቡት***

ታሪክ

# የመጨረሻው ንጉሰ ነገስት አጼ ኃይለ ስላሴ



ብሩክ መኮንን

በዓለም ስማቸው ገናና ከሆኑ የሃገር መሪዎች ውስጥ አንዱ ናቸው። በአህጉራችን አፍሪካ የነፃነትና የትብብር መንፈስ እንዲሰፍን በፊፀሙት ተግባር፣ በመዲናችን አዲስ አበባ በሚገኘው የአፍሪካ ሕብረት ቅጥር ግቢ የመታሰቢያ ሐውልት ቆሞላቸው በታሪክ ተገቢውን ስፍራም ማግኘት ችለዋል።

ከ127 ዓመት በፊት በምስራቅ ኢትዮጵያ “ኢጀርሳ ጎሮ” በተባለች መንደር የተወለዱት፣ የኢትዮጵያ የመጨረሻው ንጉስ ነገስት ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ባላለፍነው ማክሰኞ ሐምሌ 16 ቀን 2011 ዓ.ም በዋሽንግተን በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ የዋሽንግተን ከንቲባ፣ እንዲሁም ጥሪ የተደረገላቸው የኢትዮጵያ ወዳጆች የሆኑ አሜሪካውያን በተገኙበት፣ እኚህ የታላቅ ስብዕና ባለቤት የሆኑትን ኢትዮጵያዊ ንጉስ ሥራዎች ተዘክረዋል።

እኛም በዚህ እትም የመጨረሻውምየኢትዮጵያ ንጉስ ነገስትን ሕይወትና ስራን ወደኋላ መለስ ብለን በመጠኑ ለመቃኘት ሞክርን።

ሐምሌ 16 ቀን 1884 ዓ.ም ከራስ መኮንን ወልደሚካኤልና ከእናታቸው የሺእመቤት አሊ በኤጀርሳ ጎሮ የተወለዱት ተፈሪ መኮንን በልጅነታቸው በወቅቱ በነበረው የቤተ መንግስት ወግና ስርዓት በልዩ ሁኔታ፣ ሞግዚትና የካቶሊክ ቀሳውስት ተቀጥሮላቸው ፈረንሳይኛ ቋንቋ መፃፍ እና ማንበብ፣ የቤተ ክህነትን ትምህርት በጥልቀት እየተማሩ ነው ያደጉት።

ልጅ ተፈሪ መኮንን ገና በጨቅላነታቸው ነበር እናታቸውን በሞት ያጡት። ታዳጊ ሆነው የሚወዱዋቸውን አባታቸውን ራስ መኮንንም በሞት አጥተዋል። በወጣትነታቸው እጅግ ቁጥብ፣ ዝምተኛ የነበሩት ተፈሪ መኮንን ፈረስ ግልቢያ፣ ጉግስ፣ ውሃ ዋና፣ ገበጣ ቸዋታዎችን በእጅጉ ይወዱ እንደነበር ይነገራል። የእግር ጉዞ መሔድ ያዘወትሩም ነበር፣ በአመጋገብ ስርዓታቸው ብዙ ጊዜ የፆም ምግብ ምርጫቸው እንደነበር፣ ከስጋ ይልቅ መረቅ እንደሚመርጡም ከዚህ ቀደም ተናግረዋል።

በምንሊክ ቤተ መንግስት በልዩ እንክብካቤ ከሌሎች የመሳፍንቱና የመኳንንቱ ልጆች ጋራ ያደጉት ተፈሪ መኮንን፣ አባታቸው በሕይወት እያሉ በሐረርጌ ጠቅላይ ግዛት የምትገኝ የአንድ አውራጃ አስተዳዳሪ ሆነው በደጃዝማችነት ተሹመው የነበረ ሲሆን፣ በመቀጠልም በምንሊክ ሿሚነት በደብረ ብርሃን “ባሶ” የተባለ ወረዳን፣ በሌላ ጊዜ የሲዳሞ ጠቅላይ ግዛትን እንዲያስተዳሩ ተሹመው ነበር።

አፄ ምንሊክ ከሞቱ በኋላ በነበረው ለአመታት የዘለቀ የሥልጣን ሽኩቻ ወቅት፣ የአባታቸው ግዛት የነበረው የሐረርጌ ጠቅላይ ግዛት ገገር ሆነው የአዲስ አበባውን የሥልጣን ሽኩቻ በቅርብ ርቀት ሲታዘቡና በኋላ ላይም ንቁ ተሳታፊ በመሆን፣ አዲሱ ስልጣናቸው በመኳንንቱና በቤተ ክህነት ግፊት ዘውዲቱ ንግስተ ነገስት ተብለው በአባታቸው ዙፋን እንዲቀመጡ ሲደረግ፣ የአልጋወራሽነት ስልጣን በመቀዳጀት በሂደት




በኢትዮጵያ ቁልፉን የፖለቲካ ስልጣን ተቀዳጁ።

አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኮንን የንግስቲቱ ባለሙሉ ስልጣን እንደራሴ አልጋወራሽነት ስልጣናቸውን እንደተቆናጡ ነበር እሳቸውና ሌሎች የመሳፍንት ልጆች ዘመናዊ ትምህርት የተማሩበት የዳግማዊ ምንሊክ ትምህርት ቤትን፣ ተፈሪ መኮንን የተሰኘውን ትምህርት ቤትን ያቋቋሙት።

በመላው ሃገሪቱ የተሾሙ መኳንንት ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት እንዲልኩ፣ ማንም ኢትዮጵያዊ ለትምህርት ዕድሜው የደረሰ ልጆቹን ወደ ትምህርት ቤት እንዲልክ ያደረጉት ጥሪ ተቀባይነት አላገኘም ነበር በመጀመሪያ። በዚህም የተነሳ ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት ሲልኩ፣ ለልጆቹ ወርሃዊ የኪስ ገንዘብ የመክፈልን ዘዴ በመጠቀም የተማሪዎችን ቁጥር ከፍ እንዲል አድርገዋል።

ንግስት ዘውዲቱ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ “ሞአ አንበሳ፣ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ንጉሰ ነገስት ዘኢትዮጵያ” በሚል የንግስ ስያሜ የኢትዮጵያ ንጉስ ነገስት በመሆን ጥቅምት 23 ቀን 1928 ዘውድ የደፉት አፄ ኃይለ ስላሴ፣ በአልጋወራሽነት ዘመናቸው በኢትዮጵያ ታሪክ ከፍተኛ የሃገሪቱን መሳፍንት፣ መኳንንትን በማስከተል በአውሮፓ ሀገራት ያደረጉትን ጉብኝት ተከትሎ፣ ሃገራቸው የዘመናዊ መንግስት አስተዳደር ተቋዳሽ ሆና እንድትታይ በርካታ መሰረታዊ ተግባራትን አከናውነዋል።

ንጉስ ነገስት ሆነው በነገሱ በአምስተኛው ዓመት የኢጣልያን ጦር ሃገራችንን በመውረሩ፣ በወቅቱ አባል ለየነበሩበት የሊግ ኦፍ ኔሽን ለተሰኘ የዓለም መንግስታት ማኅበር አቤቱታቸውን ከማሰማት ባሻገር መደበኛ ተዋጊ ጦር እየመሩ ከተዋጉ በኋላ፣ በዓለም የተከለከለ የመርዝ ጋዝ ጭምር በመጠቀም በአውሮፕላን እየታገዘ የሚዋጋውን፣ የኢጣልያን ጦር ለማሸነፍ ስላልተቻለ፣ አቤቱታቸውን ለዓለም ማኅበረሰብ ለማቅረብ ወደ እንግሊዝ ተሰደዱ።

በወቅቱ የደረሰባቸው ስቃይና መከራን ተቋቁመው፣ ይህ በኢትዮጵያ ላይ የደረሰው እልቂትና ሽንፈት ነገ ተራውን ጠብቆ በእያንዳንዱ የአውሮፓ መንግስት ላይ እንደሚደርስ በማሳሰብ፣ በዓለም ታሪክ ውስጥ የሚጠቀስ ተግባርን የፈፀሙት ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ፣ ከአምስት አመት በኋላ በእንግሊዝ መንግስት እርዳታ በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ ነፃ አውጭ ሠራዊት እየመሩ በድል አድራጊነት ወደ አገራቸው ተመለሱ።

ሃገራቸውን ከወራሪው ኢጣልያ ጦር ነጻ ካወጡ በኋላም ሃገሪቱን፣ ህዝብዋን በብልፅግና እና በአንድነት ጎዳና በመምራት ከስልጣን እስከተወገዱበት 1967 ድረስ የኢትዮጵያ ንጉስ ነገስት በመሆን ያስተዳደሩት አፄ ኃይለ ስላሴ ምን ዓይነት ስብዕና ነበራቸው የሚለውን ጋዜጠኛ ኤማኑኤል ካቫላር “ረቂቁ የግርማዊነታቸው መልክ፣ በማንኛውም ንጉስ ዘንድ የሚታየው ክብር ያልተለየውን ሞገስ  የተሞላ ነው” ሲል ገልጾታል ።

የዎል ስትሪት ጆርናሉ ጋዜጠኛ ክሬይ ቪክር እ.ኤ.አ በ1966 ስለግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ስብዕና ሲፅፍ “ንጉሰ ነገስቱ ስድስት ሰዓት ይተኙና ፀሎት አድርገው የሚነሱት በ12 ሰዓት ነው። ከዚያም  በፓሪስ የሚታተሙት ኒዮርክ ታይምስና ኒዮርክ ሔራልድ፣ ትሪቢዩን እንደዚሁም የኢጣልያ፣ የእንግሊዝና የፈረንሳይ ጋዜጦችን ያነባሉ። ጠዋት ሁለት ሰዓት ላይ ቁርስ ተመግበው ከአንድ ሰዓት በኋላ በሮልስ ሮይስ መኪናቸው በቤተ መንግስቱ ወደሚገኘው ጽሕፈት ቤታቸው ይጓዛሉ። በስድስት ሰዓት ተኩል ምሳቸውን በልተው ለአንድ ሰዓት ይተኙና እንደገና ተነስተው ወደ ሥራ ይሄዳሉ። ንጉሰ ነገስቱ ሁልጊዜ ከሚያሳስባቸው ሥራዎች አንዱ የትምህርት ጉዳይ ነው፣ ስለዚህም ለአመታት የሃገሪቱ የትምህርት ሚኒስትርነቱ ስልጣን በግርማዊነታቸው ተይዞ ቆይቷል። ንጉሱ መሐይም መሆን የሚያሳዝን ዕድል ነው፣ ነገር ግን ከዛ ይበልጥ የሚያሳዝነው በመሐይምነት መታበይ፣ ከሁሉ የባሰ መጥፎ ነገር ነው” ብለው መናገራቸውን ጠቅሷል ።

አንዳንድ ጊዜ አዘውትረው ለትምህርት ቤት ግንባታ መሰረት ለማኖር ከሚያደርጉት ጉዞ በተለየ ያለ ፕሮግራማቸው በድንገት ወደ አንዱ ትምህርት ቤት በመሔድ ከትምህርት ቤቱ ተማሪዎች ጋር በገበታ ላይ በመገኘት አብረው ምግብ እየበሉ፣ ምግቡ እንዴት ነው? ትምህርቱስ? ብለው ይጠይቃሉ። ከዚም የሚያስፈልገውን አድርገው በቀጥሮ ወደሚጠብቁበት ፅህፈት ቤታቸው ያመራሉ።

በኢዮቤልዩ ቤተ መንግስት ተመልሰው፣ በሰፊው ጽሕፈት ቤታቸው ሥራቸውን እየሰሩ እስከ ምሽቱ አንድ ሰዓት ድረስ በሥራ ላይ ይቆያሉ፡ ፡ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ለ51 ዓመታት አብረዋቸው የኖሩት ባለቤታቸው ግርማዊት እቴጌ መነን አስፋው ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩዋቸውና ከወለዱዋቸው ስድስት ልጆች አራቱን በሞት ስላጡ ብቸኛ ናቸው። ነገር ግን ብዙ የልጅ ልጆች፣ ጥቂትም የልጅ ልጅ

ልጆችም ስላላቸው በተቻላቸው መጠን አብዛኛዎቹ በግርማዊነታቸው አካባቢ ለመኖር ይሞክሩ ነበር፡፡

ሁልጊዜ በኢዩቤልዩ ቤተ መንግስታቸው በእራት ሰዓት ሁሉም ንጉሳዊ ቤተሰቦች ይገኛሉ፡፡ ከገበታ በኋላ የዓለም ዜናና ፊልም መወያያ ርዕሶች ናቸው፡፡ ከዚያም ትንሽ ጊዜ እረፍት አድርገው፣ ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት ላይ ከመተኛታቸው በፊት የሚፃፉ ወይንም የሚነበብ ሥራቸውን እንደሚያከናውኑ ጋዜጠኛ ክሬይ የቀን ውሏቸውን በከተበበት መጣጥፍ በዝርዝር አስቀምጧል፡፡

ኒዮርክ ታይምስ በበኩሉ፤ ንጉሰ ነገስቱ በ74ኛ ዓመታቸው ላይ "ሐዘን የተሞሉ አይኖቻቸው ቢታይባቸውም እጅግ ከፍተኛ ክብርና ሞገስ የተዋሃዳቸው ናቸው፡፡ በዓለም ፖለቲካ አመራራቸውም አስተዋይና በጣም አዋቂ ናቸው፡፡ ዓለም ምስራቅና ምዕራብ በሚል ለሁለት ጎራ ተከፍሎ ባለበት ወቅት ከማንም ሳይወግኑ ገለልተኛ ሆነው ለዓለም ሰላም መከበርና መረጋገጥ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ያለውን ስልጣንና ሓላፊነት እንዲወጣ፣ አባል ሃገራት ግዴታቸውን እንዲወጡ አድርገዋል፡፤ ሃገራቸውን በኮሬክቲቭ ሴኩሪቲ ረገድ በኮሪያ ልሳነ ምድር በኮንጎ በተቀሰቀሱ ጦርነቶች ሠላም ለማስከበር ሠራዊት ልከው በማዝመት ሓላፊነትዋን እንድትወጣ ሠርተዋል፤ በአጠቃላይ ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ በዓለም ዲፕሎማሲ ረገድ ከአፍሪካ ሃገር መሪዎች ሁሉ የላቁ ናቸው" ብሏል፡፡

የአፍሪካ ሃገራት ነፃ ወጥተው በፓን አፍሪካ መርህ ስር ተሰባስበው፣ አንድ ጠንካራ አህጉራዊ ድርጅት እንዲመሰረቱ ታላቁን ሚና የተጫወቱት ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ በስልጣን ዘመናቸው በ1953 ታህሳስ ወር ላይ ተደርጎባቸው የነበረው መፈንቅለ መንግስት ሙከራ መክሸፉን ተከትሎ የሚቀርብባቸውን ትችት በተመለከተ ሲናገሩ "ሕዝባችንን መልካም ኑሮን እስከሚያገኝ ድረስ በእጃችን እንመራዋለን፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ትምህርት እንዲያገኝ የምናደርገው ጥረት ከማንኛውም የኢኮኖሚ ልማት በላይ መፈፀም ያለበት ቀዳሚ ተግባር ነው፡ ፡ ሕዝባችንን ስናስተምር ወደፊት ሊራመድ የሚችልበትን መንገድ ልንከፍትለት እንደምንችል እርግጠኛ ሆነን ነው" ብለውም ነበር፡፡

ብዙዎች ቀዳማዊ ኃይለስላሴን ሲያስታውሱ የማኬቬሊያዊ የፖለቲካ ስልት መከተልና ከፋፍሎ መግዛትን ይወዱ ነበር፤ ያ የፖለቲካ አመራር ስልታቸው እስከታችኛው የሕብረተሰቡ ክፍል ዘንድ ዘልቆ መግባት ነበረበት ይላሉ፡፡ ያም አለ ይህ ፤ከዛሬ 127 ዓመት በፊት የተወለዱትና ባለፈው ማክሰኞ 127ኛ አመት ልደታቸው ታስቦ የዋለው ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ከዓለማችን ታላላቅ የፖለቲካ መሪዎች ተርታ የሚመደቡ ታላቅ መሪ ነበሩ፡፡

# የቴዲ አፍሮ "ህያው የክብር ሽልማቶች!"

የኢትዮጵያ ሙዚቃ "አልጋ ወራሹ" ብላቴናው ድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ) አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሁለት ታላላቅ ሽልማቶችን በክብር ተቀብሏል፡፡ በሰሜን አሜሪካ አትላንታ ከተማ የሚገኙ የሚዲያና የኪነጥበብ ባለሙያዎች ከደጋፊዎቻቸው ጋር በመሆን ባሰናዱት የሽልማት ሥነ ሥርዓት በሙዚቃ ዘርፍ የላቀ አስተዋፅኦ በማበርከቱ ድምፃዊው የክብር ሽልማቱ የተበረከተለት ሲሆን፣ በዋሽንግተን ዲሲ የአፍሪካ ህብረት ጽ/ቤት፣ የዋሽንግተን ከተማ ከንቲባ ጽ/ቤትና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ጽ/ቤት በጋራ ሆነው ባዘጋጁት የአፍሪካ ወጣት ተፅዕኖ ፈጣሪዎች ሽልማት ፕሮግራምም ቴዲ አፍሮ የክብር ተሸላሚ ለመሆን በቅቷል፡፡



በሙዚቃ ስራዎቹ ፍቅርን፣ አንድነትን፣ ሠላምን፣ መቻቻልና መተጋገዝን አብዝቶ በመስበኩ ከከያኒነቱ ባለፈ እንደሰብዓዊ መብት ታጋይ እና የሠላም መልዕክተኛ የሚታሰበው ድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሳሁን ከዚህ ቀደምም በሀገር ውስጥና በውጪ ሀገራት በርከት ያሉ ሽልማቶች የተበረከቱለት ሲሆን፣ በበርካታ ኢትዮጵያውያን ዘንድም መሸለሙ የሚያንሰው እንጂ የሚበዛበት እንዳልሆነ በአደባባይ ምስክርነት ሲሰጥለት ቆይቷል፡፡

በኢትዮጵያና ኤርትራ መካከል ግጭት ተከስቶ ሁለቱ ወንድማማች ህዝቦች ተለያይተው በነበሩበት፤ ይህም በሁለቱ ህዝቦች የዘር ትብብር ላይ ገደብ አበጅቶ ብዙ ችግሮችን ሲያስከትል በቆየበት ጊዜ "ዳህላክ" በሚለው ዜማው ዘመን ተሻጋሪ መልዕክት ያስተላለፈውና ሀገራችን የሃይማኖት ልዩነት ግጭት ስጋት አንዣቦበት በነበረ ወቅት "ሼ፣መንደፈር" በተሰኘ ስራው አንድነትን፣ ፍቅርንና መቻቻልን ያስተጋባው ቴዲ አፍሮ ከዚህ በፊትም ሆነ በኋላ ባበረከታቸው የሙዚቃ ስራዎቹ ከድምፃዊነት ባሻገር ስለሀገሩ እና ስለህዝቡ አልፎም ስለ አፍሪካና የተቀረው ዓለም ሠላም፣ ፍቅርና አንድነት ያለውን ጥልቅ ስሜት የገለጠባቸውን የሙዚቃ ፈጠራዎች ለማስደመጥ ችሏል፡፡

"ግርማዊነትዎ" በተሰኘ ሙዚቃው ከኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት አፄ ሀይለ ስላሴ የሐገር ውለታ ጋር አጣምሮ የፓን አፍሪካን አስተሳሰብን በአድማጮቹ ልቦና ለማንገስ የቻለው ድምፃዊው ጥቁር ሰው በሚለው ዘፈኑም የአድዋውን ጀግና የአፄ ምኒልክ ገድልና የጥቁር ህዝቦችን የነፃነት ትግል መልክ እጅግ አስደናቂ በሆነ መልኩ አሳይቷል፡፡

"ከአንተ አይጉደል!" በሚል በፍቅር፣ በመቻቻል፣ በአንድነትና በሠላም ሀሳቦች በተቃኘ የህይወት ፍልስፍናው ብዙሃንን ለመማረክ የቻለውና ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ "ፍቅር ያሸንፋል" የሚል ልባዊ እምነቱን ከማንፀባረቅ ወደ ኋላ ሣይል የቆየው ድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሣሁን ሁሌም አስደማሚ፣ እጅግ የረቀቀ ፈጠራና ሩቅ አሻግረው ማየት የሚችሉ የሙዚቃ ፈጠራዎቹን የሚያስደጥ መሆኑ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን በአድናቆትና ተከታይነት ጎራ እንዲሰለፉለት አድርጓል፡፡

አሁን በምንገኝበት ወቅት እውን ሆኖ ያለው አዲሱ የለውጥ መንግሥት "በይቅርታና እርቅ" መንገድ ተጉዞ ከኤርትራ ጋር ሠላም እንዲወርድና የህዝብ ለህዝብ ግንኙነቱ እንዲቀጥል ሲያደርግ ከአመታት በኋላ የሙዚቃ ስራው እንደ አዲስ የተደመጠለት ቴዲ አፍሮ "ዳህላክ" በሚለው ዘፈኑ ውስጥ የቋጠራቸው ስንኞች "የትንቢት ቃል ነበሩ ወይ?" ብለን እንድናሰላስል የሚያስገድድ አጋጣሚ መፈጠሩ በስፋት ሲነሳ ይደመጣል፡፡ በተለይም በዚሁ ዘፈን ውስጥ "ካስተማርሽው ፍቅርን በጊዜ አይሻለሁ ወይ በሱ ጊዜ" የሚለው ስንኝ በዘመናችን እየሆነ ካለው እውነት ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያለው ሆኖ መገኘቱ ድምፃዊው "የነብይነት ባህሪ" እንዳለው ተደርጎ እንዲታሰብ ስለማስገደዱ በብዙዎች ዘንድ ሲወሳ ይሰማል፡፡

ጠ/ሚ/ር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ ኢትዮጵያን ለማቆየትና አንድነቷን ለማፅናት በሀይማኖቶች መካከል መቻቻል፣ መከባበርና የአንድነት ስሜት መፈጠር እንደሚኖርበት አምነው በዚህ ዙሪያ ሰፊ ስራ መስራት ከመጀመራቸው ብዙ ዓመታት በፊት "ሼ መንደፈር" በሚለው ዜማው "ተዋዶ ያለበት እስላም ክርስቲያኑ ተዘነጋሽ እንዴ ኢትዮጵያ መሆኑ፣ እኔም ልማል በአላህ አንቺም በቁልቢ … መኖር እንችላለን አይጠበንም ቤቱ…." እያለ አንድነትን፣ መቻቻልንና ፍቅርን የዘመረው የቴዲ አፍሮ በብዙሃን ኢትዮጵያውያን ዘንድ መጪውን ጊዜ አሻግሮ ማየት የሚያስችል ፀጋ እንዲታደስ ተደርጎ ይታሰባል፡፡ ሙዚቃዎቹ አማርኛ ቋንቋን በማይናገሩ የውጭ ሀገራት ህዝቦች ዘንድም ተወዳጅና ተመራጭ መሆን መቻላቸው በራሱ ብዙዎችን የሚያስደምም ሲሆን፣ እነዚህና ሌሎች ሁኔታዎች አሁን ለሚሰጡት የክብር ሽልማቶች እንዳበቁት ይታመናል፡፡

ስለሰው ልጆች እኩልነት፣ ሠላም፣ ነፃነትና ታላቅነት በሙዚቃዎቹ ሲያስተጋባ የኖረውን ጃማይካዊውን ድምፃዊ ቦብ ማርሌይን እጅግ ልዩ በሆነ ምልከታ በዜማው ያወደሰው ቴዲ አፍሮ በቦብ ማርሌይ ዘፈኑ ውስጥ የቦብን የዘመናት ጥረት አስቀጥሏል፡፡ "አፍሪካዬ" በሚለው ስራውም የአህጉሪቱን ሁለተንተናዊ ችግሮች ከመፍትሔ ሀሳቦች ጋር አንፀባርቋል፡፡ ስለቴዲ ሌላም ተጨማሪ ምስክርነት መስጠት ይቻላል፡፡ ከዚህ ፅሁፍ በላይ ግን ያገኛቸው ህያው ሽልማቶች ማን መሆኑን አብዝተው ይናገሩለታል፡፡

ሰሞኑን በዋሽንግተን ዲሲ የአፍሪካ አንድነት ጽ/ቤት ተገኝቶ የእውቅና እና የምስጋና ሽልማቱን ሲቀበል የጽ/ቤቱ ሀላፊ እንደተናገሩት ቴዲ አፍሮ በሙዚቃዎቹ የአፍሪካ ጥቁር ህዝቦችን ክብር በሚገባ ከመግለፁም በላይ ስራዎቹ ለአህጉሪቱ ተወላጆች ያላቸው አርአያነት በምንም የማይተካ ነው፡፡ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ተወካዩ እንዳሉትም ቴዲ ለአፍሪካ ወጣቶችና ከያኒያን ታላቅነትን ማለም በቂ ማሳያ መሆን የሚችል ነው፡፡

ቴዲ አፍሮ ለአፍሪካ ተፅዕኖ ፈጣሪዎች የሚሰጠውን ታላቅ የክብር ሽልማት ከእነዚህ ተቋማት ከተበረከተለት በኋላ እጅግ ትህትና እና ጨዋነት በተሞላበት ስሜት ሆኖ ይህን ነበር ያለው "ዋሽንግተን ዲሲ በሚገኘው የአፍሪካ ኅብረት ጽ/ቤት የአፍሪካ ተፅዕኖ ፈጣሪዎች ሽልማት እንዲሁም የዲሲ ከንቲባ ጽ/ቤት እና የሜሪላንድ ከተማ የሞንቶጎመሪ ካውንቲ ጽ/ቤት ተሸላሚ በመሆኔ ለአፍሪካ ህብረት ለከተማዋ ከንቲባ እና ለከተማዋ ኗሪ በሙሉ ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡"

ድምፃዊው አሁን በተለያዩ የአሜሪካ ግዛቶች እየተዘዋወረ የሙዚቃ ስራዎቹን በማቅረብ ላይ ሲሆን፣ በቀጣይም ወደ አውሮፓ ታላላቅ ከተሞች በመጓዝ ተወዳጅና ተደናቂ ሙዚቃዎቹን እንደሚያቀርብ ይጠበቃል፡፡

በዚህ አጋጣሚ የግዮን መጽሔት አዘጋጆች በሙሉ "ለእናት አገሩ ኢትዮጵያ የላቀ ፍቅርና ክብር ላለው፣ በኢትዮጵያዊነቱም ድርድር ለማያውቀው፤ ብርቅዬ የአገር ኩራት ለሆነው ቴዲ አፍሮ" የእንኳን ደስ ያለህ መልካም ምኞታችንን እናስተላልፋለን፡፡

# የስፖርት ችግሮቻችንን መቅረፍ !

**ፋንታሁን ኃይሌ**

አንዳንድ የጋራ የሆኑ ጉዳዮች “ምከረው ምከረው፤ እምቢ ካለ መከራ ይምከረው” ተብሎ ሊተው የሚችሉ ሳይሆኑ ይቀርና አማራጭ ሲጠፋ፤ ለሁሉም ጭንቅ ሆነው ይቆያሉ። በልጅነታችን አንድ ችግረኛ ሰው ሐረር ከተማ ውስጥ እንዲህ እያለ ይለምን ስለነበር እስከዛ ይገርመኛል፣“ተቸግሬ የማስቸግራችሁ” በማለት። በበኩሌ የሀገራችን ስፖርት በደንብና በስርዓት መካሄድ የጀመረው ኢጣሊያ ሀገራችንን ከወረረች ወዲህ ሲሆን የእግር ኳስ ፌዴሬሽን በ1940 ዓ.ም እንደተተቋቋመ ድርሳናት ያወሱናል።

በስፖርት ጋዜጠኝነት ደረጃ እነ ሰለሞን ተሰማ የመጀመሪያዎቹ እኛ ደግሞ ተከታዮቹ፣ አሁን ያሉት ደግሞ ሶስተኛው ትውልድ ለመሆን የተቃረቡ ይመስለኛል። አንድ እናት (አባት) የወጣትነት ዘመኗን/ኑን አጣጥማ/ሞ ሳትጨርስ/ሳይጨርስ ልጇ/ጁ በጉርስምና ከደረሰበት አንድ ዘመን ስለሚኖሩ በሁለቱ መካከል ያለው መጣጣም ብዙ ጊዜ መስመሩን መልቀቁ አይቀሬ ነው።

ዛሬ ላይ ሆኜ እንደገባኝና እንደተረዳሁት ከሆነ ቀደም ብለን የነበርነው የስፖርት ጋዜጠኞች ወይንም (በራሳችን ፈቃድ) ሆነ ተገደን በአንድ ጊዜ ሁላችንም ሙያውን ለቀን በመሄድ እንዳልደከምንበት፣ መስዋዕትነት እንዳልከፈልንበት፣ ባለቤትና ወገን እንዳንሆን ሁሉ የዳር ተመልካች መሆን አልነበረብንም።

ለምሳሌ ከሬድዮ ይንበርበሩ ምትኬ፣ ከቴሌቪዥን ፀጋ ቁምላቸው፣ ከጋዜጣ ግርማ ሠይፉና እኔ በአንድ ጊዜ በመልቀቃችን ከልምድና ሙያ ሽግግር አንፃር ሳስተውለው በጣም ሰፊ ክፍተት እንደተፈጠረ መገንዘብ ይቻላል። ክፍተቱን በመጠቀም በቦታው ያልነበሩና በሙያው ያላለፉ ሁሉ “ተጨዋች” ነበርኩ በሚሉበት ጊዜ ሣይቀር ታሪክ ተናጋሪዎችና ዘጋቢዎች ሲሆኑና ተጨባጭ ያልሆኑ (የተሳሳቱ) ነገሮችን ሲያቀርቡ እያስተዋልንና እያደመጥን ነው። ብዙ መዘርዘር ይቻላል። ተሳስታችኋልና አርሙ ሲባሉ እንኳን “ካፈርኩ አይመልሰኝ” በሚል ይመስላል መሰሳታቸውን በመግለፅ ዕወነታውን ለህዝቡ አይገልፁም። እኛ በልምድ ሳይሆን ተምረን ነው የስፖርት ጋዜጠኞች የሆንነው።። ቀልድ የለም! ነባር የስፖርት ጋዜጠኞች ለቀው በመሄዳቸው የተነሳ በተፈጠረው ክፍተት ቡድኖች አሰልጠኞች፣ ስፖርተኞች፣ አርቢትሮች፣ የውድድር አዘጋጆች፣ ተመልካቾችና ደጋፊዎች እንዲሁም የተለያዩ ፌዴሬሽኖች በብዙ አቅጣጫ ተጎጂ ሆነዋል። በእርግጥ የዛሬዎቹ ጋዜጠኞች በአካል ብቻ ሳይሆን በኢኮኖሚም ዳብረዋል።

የስፖርት ቤተሰቡ አማራጭ ስለሌለው ዕውቀቱ ሳይኖራቸው እርስ በርሳቸው የሚሸላለሙትንና የሚንቆለጳጰሱትን፣ ማለትም አጠገቡ ያገኛቸውን ቢያደንቅ አይፈረድበትም። በተለይ ለወጣቱ ትውልድ የስፖርት ጋዜጠኝነት ምን እንደሚመስልና ምን መምሰል (መሆን) እንዳለበት በጭላንጭል እንኳን ስላላሳየነው ወደ ተሳሳተ አቅጣጫ ቢያዘነብል አይፈረድበትም።

ለስፖርት ጋዜጠኞቻችንም ምሳሌ ሞዴል ሆነን ቀርበን አላሳየናቸውም። አንዳንዶች የሚችሉትን ለመሥራት ሞክረዋል። አቅማቸውንና ችሎታቸውን አውቀው፣ የተለያዩ ዘርፎች ውስጥ ሳይዘባርቁ፤ እንደ ሌላው ዓለም የስፖርት ጋዜጠኞች በአንድ ስፖርት ላይ ስፔሻላይዝድ አድርገው ለመስራት የሚሞክሩ እንደ መንሱር አብዱልቀኒ የመሳሰሉት እግር ኳስ ጋዜጠኞችን ማድነቅ ተገቢ ነው። ይህን አለማድረግ እውነታውን መካድ ነው የሚሆነው።

የማደንቀውና የማከብረው ይኸ የስፖርት ጋዜጠኛ ከአንድ መጽሔት ጋር ባደረገው ቃለ ምልልስ በሀገራችን የስፖርት ጋዜጠኛ እንደሌለ በአንድ ወቅት ገልፆልን ነበር። ዛሬስ? በሀገራችን ሀቀኛ የስፖርት ጋዜጠኛ አለ? ከነመረጃው አሁንም ብዙ ማለት ይቻላል። ለሀገራችን ስፖርት ድክመት ውድቀት መጠየቅና ኃላፊነት መውሰድ ካለባቸው መሀል የስፖርት ጋዜጠኞች አይገኙበትም? መድረኩን ክፍት እናድርገውና በሕዝባዊ መጽሔታችን ላይ በግልፅ እንወያይበት እስኪ!

አንዱን በምሳሌነት እንውሰድ። የአንድ ተጨዋችን ችሎታ የተረዳ አንድ ቡድን (መቼም በሀገራችን ክለብ የለም) ተጨዋቹ ለምርጫ በቀረበበት ጊዜ ብቻ ሳይሆን የኋላ ታሪኩን በመመርመር አልቀጥርህም በማለት አባረረው። በሦስተኛው ቀን አንድ ሌላ ጋዜጠኛ ይኼው ተጨዋች በሶስት ቡድኖች በእጅጉ እየተፈለገ መሆኑን ይሉኝታውን ሽጦ ፃፈ። ሳይውል ሳያድር ያባረረው ክለብ ጠርቶ ቀጠረው። አሰልጣኞችንና የውጪ ተጨዋቾችን በተመለከተ በመሞዳመድ የሚሰሩ ነገሮች ሞልተው ተርፈዋል። ዕውነት ለመናገር ከሀገራችን ታዋቂ አሰልጣኞች ዕውነት ስለያዙ ብቻ ያለስራ የተቀመጡ የሉም? ይህ ያመጣልን ነገር ቢኖር ውድቀታችንን ማፋጠን ብቻ ነው።

በገንዘብ ብቻ ሳይሆን አብሮ በመብላትና በመጠጣት፣ በዓይነት በማበርከትና በተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች በመደለል የሚሰሩ ነገሮች የሉም? መድረክ ስላጡ ነው እንጂ አያሌ የስፖርት ቤተሰቦች ለሕዝብ ግልፅ ሊያደርጓቸው የሚፈልጓቸው በጣም ብዙ ነገሮች አሉ።

በበኩሌ ከዳር ሆኜ ማየቱን እርግፍ አድርጌ በመተው ወደ ስፖርት ጋዜጠኝነቱ እየመጣሁ ነው። እንደቀድሞ በሀቅ፣ ስለሀቅ ለመስራት ትጥቄን እያጠበቅኹኝ ነው። ከሁሉም ጋር ልንተያይ ነው። አካፋን አካፋ! ዶማን ዶማ! ትምህርትን ትምህርት! ስልጠናን ስልጠና! ማለቴን እቀጥላለሁ።

በቀጣይ ወደ ተለያዩ ስፖርት ፌዴሬሽኖችና የክልሉ ስፖርት ተጠሪዎች ዘንድ ጎራ ልበል። እኛ በየክፍለ ሀገሩ ተጠሪ (ኮሚሽነር) በነበርንበት ጊዜ እንደኛው ሁሉ በየፌዴሬሽኖች ጠንካራ ጠንካራ ፀሐፊዎች ተመድበው ያገለግሉ ነበር። ሁላችንም የምንመራው ብቻ ሳይሆን “እንገራና እንቀረፅ” የነበረው በይድነቃቸው ተሰማ ነበርና የታደልን ነበርን። ዛሬ ላይ ሆኜ ሳየው ታድለን የነበርነው እኛ ብቻ ሳንሆን ጋሽ ይድነቃቸውም ጭምር ነበሩ። ይህን ያልኹት በኃላፊነት የተመደብነው ተማሪዎች ስፖርቶችን ተምረንና አስተምረን የመጣን፣ ለስፖርቱ ስንል ሁሉንም እንጋፈጥ የነበርን፣ ከመካከላችን የታሰርንና ብዙ ስቃይ የደረሰብን ስለሆንን ነበር። ባለሙያ መሪና ተመሪ ተገናኘ ይሏል፤ የዚያን ጊዜ ነበርና የሀገራችን ስፖርት ዕድገቱን ቀጥሎ ነበር።

ዛሬ ይህንን በተግባር ለመተርጎም ጊዜና ሁኔታን ጨምሮ አያሌ ተግዳሮቶችን መጥቀስ ይቻላል። ታዲያ መጥቀስ ብቻ ይቻል እንደሁ እንጂ ለውድቀት ምክንያትነት በቂ ነው ተብሎ ሊወሰድ ቢሞከር ይተናነቃል።

ለምሳሌ በአሁኑ ጊዜ ያለ የአንድ ፌዴሬሽን ጸሐፊ የተመደበበትን ስፖርት እንዴት ነው ለማስፋፋት ጥረት የሚያደርገው? የክልል ተጠሪስ (ኮሚሽነርስ)? ዘርዘር አድርገን እንመልከተው።

የመረብ ኳስ ፌዴሬሽን ሓላፊን አልያም የሁሉንም የፌዴሬሽን አባላትን እንውሰድ። ስፖርቱን ለማስፋፋት በቅድሚያ መጀመር ያለባቸው ከአካባቢያቸው ነው። ከአዲስ አበባ አካል ማሰልጠኛና ስፖርት ፅሕፈት ቤት ጋር ይነጋገሩ ። በመቀጠል ዕቅዳቸውን በመንደፍ ፕሮግራማቸውን ያውጡ። በየክፍለ ከተማው የሚገኙ የስፖርት ቅርንጫፍ ፅሕፈት ቤት ባለሙያዎች ጋር በመመካከር ትምህርት ይስጡ። ከዚያም ቡድኖችን በመመስረት ውድድሮች ያድርጉ።

ይህ በየቀበሌዎቹ ሲከናወን፣ ትምህርት ቤት በመሄድ ስልጠና በመስጠትና ቅስ ቀሳ በማካሄድ፣ የውድድር ፕሮግራም በማውጣትና ማካሄድ፣ በየመስሪያ ቤቱም እንደዚሁ በማድረግ ግዴታቸውንና ኃላፊነታ ቸውን ይወጡ። ይህን ከከወንን ብዛት ያላቸው ስፖርተ ኞችን ብቻ ሳይሆን ምርጥ ስፖርተኞችንም ለማፍራት የሚያግድ ነገር አይኖርም። ቢሮ በሠዓት ገብቶ መውጣት ብቻ የሚፈይደው አንዳች ነገር የለም።

በዚህ ረገድ ለስፖርት ኮሚሽን መስሪያ ቤት የምለው ነገር ቢኖር ትምህርትና ስልጠና በተግባር ካልተተረጎመ ዋጋ የለውምና አሁን ካሉት የፌዴሬሽን ኃላፊዎችና አባላት በተጨማሪ ቀድሞ የፌዴሬሽን ጸሐፊዎችና የቴክኒክ ሓላፊዎችን በመጠነኛ ክፍያ ወደየፌዴሬሽኖቻቸው ተመልሰው በአማካሪነት እንዲሰሩና ስፖርቱን ወደነበረበት ለመመለስ ልምድና ዕውቀታቸውን እንዲያካፍሉ ያድርግ የሚል ነው። ይህ በየሀገሩ የሚሰራበትና ውጤታማ የተሆነበት ነውና እንሞክረው እስኪ! ሊተካከሉ የሚገባቸው አወቃቀሮችና አደረጃጀቶች እንዳሉ ሆነው።

***ቸር እንሰብት!***

# “ኢትዮጵያ በአንድነትና በሰላም ብትኖር ደስታዬ ነው”

## ሳምራዊት ደረጀ  የሚስ ኢትዮጵያ በአሜሪካ አሸናፊ

ወ/ት ሳምራዊት ደረጀ፣ የሚስ ኢትዮጵያ ዩ.ኤስ.ኤ 2018/19 ተሸላሚ ነች፡፡ ከአሜሪካ ዋሽንግተን ዲሲ በቅርቡ ወደ ኢትዮጵያ መጥታለች፡፡ ሳምራዊት አሜሪካ ተወልዳ ብታድግም አገርዋን ኢትዮጵያን አልሰራችም፡፡ ከወላጆቿ የአገሯን  ታሪክና ባህልም ተምራለች፡፡ ባህላዊ ምግብና መጠጦቻችንን አዘገጃጀቶችም ጠንቅቃ ታውቃለች፡፡ ወጣቷ በአሜሪካ “የኢትዮጵያና ኤርትራ ሶሳይቲ” የተሰኘ ድርጅት ውስጥ ሰፊ ድርሻ ያላት ሲሆን ፤ በት/ቤት Hayfield Secondary School ካሉት ተማሪዎች ከፍተኛ ነጥብ አምጥታ ከአሜሪካ የቀድሞው ፕሬዚዳንት ኦባማ እጅ ተሸላሚ ለመሆን በቅታለች፡፡

በበጎ አድራጎት ድርጅቶች ውስጥ ሰፊ የሆነ ድርሻ ያላት ሳምራዊት በ”ሮሆቦት ፊዲንግና የትምህርት ሴንተር ኦርጋናይዜሽን” እንዲሁም በሙዳይ የበጎ አድጎት ማህበር ውስጥ እያገለገለች ሲሆን፤ በሜሪጆይ ፋውንዴሽን በአሜሪካ የበጎ ፍቃድ አምባሳደር ከመሆኗም በተጨማሪ ስኮላርሺፕ ከግሎባል ሜሪላንድ ዩኒቨርስቲ አግኝታለች፡፡ የግዮን ጋዜጠኛ ሙሉጌታ አክሊሉ ወደ አሜሪካ ከመመለሷ አንድ ቀን በፊት በኤሊያና ሆቴል አግኝቷት ያደ ረጉትን ቆይታ እንደሚከተለው አቅርቦታል፡፡

**ግዮን፡- ስለ ኢትዮጵያዊ ባህልሽ ምን ያህል ታውቂያለሽ?**

ሳምራዊት፡- አሜሪካ ተወልጄ ባድግም አገሬን ኢትዮጵያዊ ማንነቴን መርሣት አልችልም፡፡ በወላጆቼና በአያቴ በጣም እኮራለሁ፤ ስለ ባህላዊ የቡና አፈላል፣ የባልትና አዘገጃጀት፣ የባህላዊ ምግቦች አሰራርና ጨምሮ የድፎ ዳቦ አዘገጃጀት፣ ቋንቋችንን፣ ታሪካችንን፣ ቅርሶቻችንን ጭምር በጣም እንዳውቅ አድርገውኛል፡፡

**ግዮን፡- በአሜሪካ የትምህርት ሁኔታሽ ምን ይመስላል?**

ሳምራዊት፡- አሁን አሜሪካ ስመለስ “ሃይፊልድ ሰከንደሪ ስኩል” የተሰኘ ት/ቤት 12ኛ ክፍል ነው የምገባው፡፡ በዚህ ት/ቤት ውስጥ እኔና አንዲት ኢትዮጵያዊት ጓደኛዬ “የኢትዮጵያና ኤርትራ ሶሳይቲ” የሚባል  ድርጅት አቋቁመን የበጎ አድራጎት ሥራ መስራት  ጀምረናል፡፡

ኢትዮጵያውያንና ኤርትራዊያኖችን በት/ቤታችን አሰባስበን “በአንድነትና በፍቅር ተጠናክረን፣ እንዴት ሃገራችንን መርዳት እንችላለን?” የሚል ሀሳብ በማቅረብ ነው የበጎ ሥራውን ጀመርነው፡፡ በዋሽንግተን ዲሲ ብዙ ኢትዮጵያዊያኖችና ኤርትራውያኖችም አሉ፡፡ ፊት ለፊት ባይናገሩትም ትንሽ የእርስ በርስ ክፍፍል ስላለ ያንን ለማጥፋት ሁላችንም በአንድነት ሆነን ለመስራት፣ባህልና ታሪካችን በአብዛኛው ተቀራራቢነትና ተመሳሳይነት ስላለው ፤ በአንድ ወቅትም አንድ ላይ ስለነበርን “ ከመለያየት አንድ ብንሆን ይሻለናል፡፡ ብዙ መሥራትም እንችላለን፡፡ መለያየት ማንንም አይጠቅምም” በሚል ነው መንቀሳቀስ የጀመርነው፡፡

የምማርበት ት/ቤት ከዓለም ዙሪያ በርካታዎች የሚሰባሰቡበት በመሆኑ የሌላውንም አገር ባህል በመማር ዕውቀትን በስፋት የምንገበያይበት ነው፡፡ በትምህርቴ በጣም ጎበዝ ነኝ ማለት እችላለሁ፡፡ ከ1ኛ ደረጃ ትምህርቴ ጀምሮ የ ቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ኦባማ ልዩ ተሸላሚ ነበርኩ፡፡

**ግዮን፡- ኢትዮጵያን እንዴት አገኘሻት?**

ሳምራዊት፡- በጣም ፍቅር ያላት ሀገር ናት፡፡ ከዚህ ቀደም ኢትዮጵያ መጥቼ አንድ ዓመት ኖሬያለሁ፡፡ የተለያዩ በዓላትን ከቤተዘመድ ጋር አንድ ላይ ማክበር ደስ ይላል፡፡ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ፍቅርን በመግለጽ፣ የበርካታ አኩሪ ታሪክ፣ ቋንቋና ባህል ስላለን ሃገሬን በጣም እወዳለሁ፡፡ ኢትዮጵያዊነት ማለት ፍቅር ነው፡፡ ከራሳችን በላይ ለሌሎች የምናስብ ነን፡፡ ከፍቅር ሁሉ ነገር ከጀመረ፣ ምንም ነገር



መስራት ይቻላል፡፡

በአሜሪካን ብወለድም ስለ አክሱም፣ ላሊበላ፣ አብያተ ክርስቲያናት መሰል ታሪኮች በደንብ አውቃለሁ፡፡ ቤተሰቦቼም ባላቸው አቅም መሰረት ቆፍቱ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያንን አሰርተዋል፡፡

**ግዮን፡- በበጎ ፍቃድ አምባሰደርነት  ሜሪጆይን በመወከልሽ ምን ይሰማሻል?**

ሳምራዊት፡- ይህንን ዕድል አግኝቼ ድምፄን ለማሰማት በመታደሌ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን፡፡ ሌሎችንም እንዳነሳሳ መታደሌ ትልቅ ዋጋ አለው፡፡ ክራውኑ ሌሎች እንዲነሳሱ አድርጎ በበጎ ፈቃድ ከሌሎች ጋር ተገናኝተን እንድንሰራ የሚያደርግ እንጂ፣ ዘውድ መጫን ካለሥራ ትርጉም የለውም፡፡ የምሠራው ሥራ ነው የኔን ማንነት መግለጽ ያለበት፡፡ ሁላችንም ለሃገራችን ማሰብ ይገባናል፤ መርዳትም ይገባናል፡፡ ሁላችንም በምንችለው አቅም ሌሎችን እናግዝ፡፡

የ”ሜሪጆይ ፋውንዴሽን” እና የ”ሚስ ኢትዮጵያ ዩ.ኤስ.ኤ ኤጀንትን” በጣም አመሰግናለሁ፡፡ ለኢትዮጵያ በአምባሳደርነቴ የምሰራው በሶሻል ሚዲያ ላይ የሜሪ ጆይ ፋውንዴሽንን በማስተዋወቅ፤ በእኔ ዕድሜ ያሉት ማህበራዊ ድህረ ገጽ የሚጠቀሙ ወጣቶችም ሆኑ ሌሎች ኢትዮጵያውያን መልዕክቱን በመመልከት ግንዛቤውን እንዲያዳብሩ፣ ለዓላማው መሳካትም በበጎ አድራጎት ላይ እንዲሣተፉ  ለቅስቀሳና ግንዛቤ መፍጠር ነው ዋነኛ ስራዬ ፡፡

**ግዮን፡- ከትምህርትሽ ውጪ ምን ትሰሪያለሽ?**

ሳምራዊት፡- በአሜሪካ ከኢትዮጵያዊያን የበጎ አድጎት ድርጅቶች ጋር  እሰራለሁ፡፡ በአሜሪካ በቤተክርስቲያን ውስጥ ዘማሪ ነኝ፡፡ ለበጎ አድራጎቶች የሚሆን የትምህርት ቁሳቁሶችን አሰባስበን ለድርጅቶቹ ለመስጠት ሙሉ ዝግጅታችንን አጠናቀናል፡፡ በኮንቴይነር በመላክ በቅርቡ ኢትዮጵያ ይደርሣል ብለን ተስፋ እናደርጋለን፡፡

**ግዮን፡- የበጎ ፍቃድ አምባሳደርነትሽ ምን ያህል ሰዎችን ተጠቃሚ አድርጓል?**

ሳምራዊት፡- እኔ የማምነው በአንድ ሰው ተጠቃሚነት ትንሽም ሆኖ ትልቅ ነገር በመስራት በዛ ሰው ህይወት ላይ ልዩነት ማምጣት ከቻልን፤ ለወንድሜ ወይንም ለእህቴ ብዬ ማሰብ ከቻልኩ በራሱ ትልቅ ነገር ነው፡፡ ከትንሽ ነገር በጎ ነገርን ካሰብን ማደግ እንችላለን፡፡

**ግዮን፡- ሜሪጆይ ፋውንዴሽንን ከመርዳት አኳያ ምን ምን ነገሮችን አድርገሻል?** ▶

ሳምራዊት፡- አንድ ዶላር ሲመነዘር በኢትዮጵያ ብዙ ነው፣ ግን ዶላሩ ሳይሆን መታየት ያለበት ቀና ሃሳቡ ነው፡፡ ውስጣችን ያለው ነገር መለካት ያለበት፡፡ ውስጣችን ስላለ ነው ብር አውጥተን የምንሰጠው፣ በገንዘብም ይሁን በጉልበት ወይንም በዕውቀት በጸሎትም ቢሆን መርዳት በምንችለውና አቅማችን በፈቀደው ለሀገራችን ልናስብ ይገባናል፡፡ እኔም ከዛ አኳያ ነው እየተንቀሳቀስኩ ያለሁት፡፡

**ግዮን፡- ለበጎ አድራጎት ማህበራት የሚሰጡ ዕርዳታዎች በትክክል ለተረጂዎች መድረስና ያለመድረሱን በተመለከተ ጥርጣሬ ላላቸው ሰዎች ምላሽሽ ምንድን ነው?**

ሳምራዊት፡- አንዳንዴ ይህን መሰል ሀሳብ ይስተዋላል፡፡ ግን በማህበራዊ ድህረ ገጽ፣ በዌብ ሳይት ፖስት አድርጎ ለማሳየትና “ለዚህ ድርጅት ነው የምንሰጠው” ብለን ስለምንፅፍ እሱን ሲመለከትና ሲሰማ ያምናል፡፡ ከቤተሰብና ከጓደኛም በንግግር ቢሰማም፤ በዓይኑ ያየውን ያምናልና፡፡ በሶሻል ሚዲያ ዝርዝር ጉዳዩን ቀድመን በማሳየት እንዲያምኑን ለማድረግ የአቅማችንን እንሞክራለን፡፡

**ግዮን፡- ከውጭ ወደ ኢትዮጵያ ልገሳዎች ሲመጡ የሚቆጣጠር አካል አለ?**

ሳምራዊት፡- በመጀመሪያ ለበጎ አላማ የተቋቋመውን ፋውንዴሽን (ድርጅት) እናምናለን፡፡ ለምሣሌ ሜሪጆይን ብንጠቅስ ሲስተር ዘቢደርን ስናስብ የእርሷን ፔጅ እንጠቀማለን፡፡ ብዙ ያደረግናቸውን ድጋፎች ራስዋ ለማህበረሰቡ ታሳያለች፡፡ ያንን በመከታተል ያደረግናቸውን ድጋፎች መድረሱን ማወቅ እንችላለን፡፡

**ግዮን፡- በአሜሪካ እናንተ የበጎ አድራጎ ሥራ ስትሰሩ በበላይነት የሚያስተዳራችሁ ማነው?**

ሳምራዊት፡- ከሚስ ኢትዮጵያ ዩ.ኤስ.ኤ ኤጀንት አቶ ተስፋሁን ጋር አብረን እየሰራን እንገኛለን፡፡ ብዙ የሚረዱን እናቶች ቤተሰቦች ጓደኞች አሉ፡፡

**ግዮን፡- የበጎ ፍቃድ ዓላማውን አስመልክቶ በስንት ጊዜ ትገናኛላችሁ?**

ሳምራዊት፡- በአካል በየቀኑ ባንገናኝም በስልክና በአጭር የፅሁፍ መልዕክትም ሁሌም በየቀኑ እንገናኛለን፡፡ የደረስንበትን ሁኔታም በነፃነት እንወያያለን፡፡ የበጎ አድራጎቱ፣ የፈቃደኝነቱ ሥራ በሁላችንም ውስጥ ስላለ ሁሌም እንነጋገራለን፡፡ ወደ አገር ቤት እንዲደርስም ጥረት እናደርጋለን፡፡

**ግዮን፡- በበጎ አድራጎት ላይ ስትሰማሩ የሚከፈላችሁ ነገር አለ?**

ሳምራዊት፡- ማንም ገንዘብ ተከፍሎት አይደለም የሚሰራው፤ ውስጣችን ያለና አገራችንን መርዳት ስለምንፈልግ ሁላችንም በራሳችን በጎ ፍቃድ ተገናኝተን ነው የምንሰራው፡፡ የሚስ ኢትዮጵያ ኤጀንት ፕሬዚዳንት ተስፋሁን ጌቱ ነው ያሰባሰበን፡፡ አብረን ሰርተንና ዕቃዎችን አሰባስነብ ነው አሁን ወደ ኢትዮጵያ የመጣነው፡፡

**ግዮን፡- አሜሪካ ተወልደሽ ብታድጊም የቋንቋ አጠቃቀምሽ በሚያስደንቅ ሁኔታ ጥርት ያለነው፤ ይህ እንዴት ሊሆን እንደቻለ ትነግሪናለሽ?**

ሳምራዊት፡- ከኢትዮጵያዊያን ጋር ሳወራ እንግሊዘኛ ቋንቋን አልቀላቅልም፡፡ ቋንቋውን ይበልጥ ላጠና የቻልኩት በቤተሰቦቼ ድጋፍና እገዛ ሲሆን፤ አያቶቼና ወላጆቼ ከልጅነቴ ጀምሮ አማርኛን በደንብ ያስጠኑኝ በመሆኑ ነው፡፡ ቤት ውስጥ ሁሌም እንዳጠና የሚፈቀድልኝ አማርኛን ብቻ ስለነበረ እሱ ቋንቋውን በደንብ እንድናገር ጠቅሞኛል፡፡ አንዳንድ እንግሊዝኛ የማይችሉ ቤተሰቦች ስላሉኝ አማርኛ በማወቄ ቅርበቴን አጠንክሬበታለሁ፡፡ ይህንን ላደረጉልኝ ቤተሰቦቼም ከፍተኛ አክብሮትና ምስጋና አለኝ፡፡ አገሬንና ባህሌን እንዳልረሳ ያደረጉኝ፣ ዛሬ ላይ ደስተኛ እንድሆን ውለታ የዋሉልኝ እነሱ ናቸው፡፡

**ግዮን፡- ኢትዮጵያዊነትን የሚያጎሉ ፊልሞችንስ ትከታተያለሽ?**

ሳምራዊት፡- ሁሌም ከወላጆቼ ጋር ዩ-ቲዩብ ላይ የአማርኛ ፊልም ሲያዩ ከጎናቸው ተቀምጬ አይ ነበር፡፡ አማርኛው አንዳንዴ ያስቀኛል፡፡ አማርኛውን በደንብ ስትገባበት የሚያደናግሩ ቃላት (የማይገባ) ሊገጥምህ ቢችልም ማዳመጥና መረዳት ከፈለክ ወዲያው ታውቀዋለህ፡፡ ሁሌም ቋንቋዎችን መማር እፈልጋለሁ፡፡ አማርኛን ማጠንከር ስለምፈልግ የኢትዮጵያ ፊልም ማየት ደስ ይለኛል፡፡

**ግዮን፡- ስለ ቁንጅና ያለሽ ግምት ምን ይመስላል?**

ሳምራዊት፡- ቁንጅና በውጭ ያለው አካል ብቻ ሳይሆን በውስጥህ ያለውም ነው፡፡ በውጭ ቆንጆ ብንሆን ምንም ብቻውን ትርጉም የለውም፡፡ ውስጣችን ያለው ፍቅር ለሰው አሣቢነታችን፣ የምንወስድ ሳይሆን ካለን ነገር ላይ የምንሰጥ ከሆነ፣ እሱ ነው በአንደኛነት የሚቆጠረው፡፡

**ግዮን፡- በታሪክ ደረጃ ለመረዳት ምን አውቀሻል?**

ሳምራዊት፡- ከልጅነቴ ጀምሮ ብዙ ነገሮችን እሰማለሁ፡፡ የነገሥታትና የንግስት ታሪኮችን ጨምሮ እጅግ ብዙዎችን ከወላጆቼ ተረድቻለሁ፡፡ አንድን ልጅ ለማሳደግ ወላጅ ብቻ ሣይሆን በዙሪያው ያለ ዘመድ አዝማድ አንድ-አንድ ነገር አስተምረውኛል፡፡

**ግዮን፡- የዶክተር ዐቢይ አሕመድን ወደ ሥልጣን መምጣት እንዴት አገኘሽው?**

ሳምራዊት፡- (ሣቅ) እንደሰማሁት እና እንዳየሁት ከሆነ ሁሌም ስለ ሰላም፣ አንድነትና ፍቅር ስለሚያወራ በሁሉም በኢትዮጵያዊ ልብ ውስጥ ያለ ስለሆነ በእርሱ ደስተኛ ነኝ፡፡ መልካምነትን፣ ጥንካሬና በጎነትን መሥራት ከአስተዳደግና ከቤተሰብ ይጀምራል፡፡ አንድን መጥፎ ድርጊት የሚያደርግን ሰው ከቤተሰብ ውጭ ቢሆንም ብናግዘውና ብንረዳ ሁላችንም ጥሩ ደረጃ ላይ መድረስ እንችላለንና እንተሳሰብ፣ እንረዳዳ፣ ወንድሜና እህቶቼ እያላችሁ ወደ በጎ ተግባር ሣብ አድርጓቸው፡፡

**ግዮን፡- ኢትዮጵያና ኤርትራን አስመልክቶ ‹‹ኢትዮ ኤርትራ አሶሴሽን›› ላይ የተሰባሰባችሁ ግሩፕ ምን ሰርቷል?**

ሳምራዊት፡- የኢትዮጵያና ኤርትራ ባህልን፣ አለባበሳችንን ምግባችንን በማስተዋወቅ፣ ባህላዊ የጭፈራ ትርኢት በማካሄድ በርካቶች ተሳትፈውበታል፡፡ በበጎ ፈቃደኝነትም ብዙ አርቲስቶች እስክስታን በማለማመድ አስተም ረዋል፡፡ በዚያ ላይ ወጣቶችን በማሰባሰብ የልምምድ ልውውጥ አካሂደናል፡፡ ከዚያ ውጭ በልብስ አሰባሰብ ዙሪያ በቤተክርስቲያን፣ በተለያዩ ማተሚያ ቤቶች በመዞር የተለያዩ ድርጅቶች እንደ ማርክ ኮምፒውተር አይነት ለበጎ ፍቃድ ድርጅት የሚረዳ፣ በኢትዮጵያዊነት የሚያምንና ጥሩ አቋም ኖሮት በውጭ ያሉ ኢትዮጵያውኖች ባህላቸውን እንዲጠብቁ የሚያበረታታ በመሆኑ የእርሱ ድርጅትና ሌሎች በርካታ ሱቆች የአረጋውያን ዳይፐር፣ በአልጋ ላይ ለተቀመጡ ከየሆስፒታሉና ከተለያዩ ሰዎች አሰባስበናል፡፡

የአረጋውያውንና የህፃናት ልብሶችን እንዲሁም የት/ቤት መሣሪያ (እርሳስ፣ ስክሪፕቶ፣ ደብተር፣ መቅረጫ፣ መጽሐፍ.....) ቤት ተከራይተን ኢትዮጵያዊነትን በማንፀባረቅ ጊዜያችንን እየወሰድን ከአርቲስት ኩሪባቸው፣ ከተወዛዋዥ እናቴ ጥሩ ዓለም ከበደ ጋር ልብሶችን እያሰባሰብን፤ ከትምህርትና ከሥራ ቀርተን ጥሩውን በመምረጥና በማጠብ፣ የህፃናትንና የአዋቂን በመለየት በተስፋሁን ጌታቸው አማካኝነት የበጎ አድራጎቱ አዘጋጅ ጋር ካለ ምንም ክፍያ ከኢትዮጵያ ኤምባሲ ጋር በመተባበር ሰርተናል፡፡

በአሁኑ ሰዓት ለሮሆቦት ፊሊንግ ሴንተር ለምግብ የሚሆን ገንዘብ ከቤተሰባችን ረድተናል፡፡ ለሜሪጆይ ደግሞ ልጆችን ለማሳደግ ስፖንሰር አድርገናል፡፡ በቤተሰባችን እናቴ አንድ ልጅ እኔና እናቴ በጥምረት መንትያ ልጆችን ስፖንሰር በማድረግ በየወሩ የሚከፈል ገንዘብ ከሜሪጆይ ደረሰኝ እየተቀበልን እንከፍላለን፡፡ በአሜሪካ ደረጃ 360 ብር ከ15 ዶላር አይበልጥም፡፡ ልጆቹን በቀጥታ ስፖንሰር አድርገን ጥሩ ደረጃ እስከሚደርሱ እናግዛለን፡፡ (እንሣተፋለን) እኛ በቀን 3 ጊዜ የሚበላበት ቦታ ነው ያለነው፡፡ ከምንበላው ላይ አንዱ ተቀንሶ በሃገራችን መንገድ ላይ ላሉ አባትና እናት ጧሪ ለሌላቸው በማካፈል ኢትዮጵያዊነታችንን እየገለፅን ነው፡፡

**ግዮን፡- የኢትዮጵያን ፖለቲካ እንዴት አገኘሽው?**

ሳምራዊት፡- ኢትዮጵያና ዓለም በአንድነት፣ በሰላምና በፍቅር ብትኖር ደስታዬ ነው፡፡ እኛ ኢትዮጵያዊያን በጣም የምንዋደድ ብዙ ባህል ያለን ከራሳችን አልፈን ለሰው የምንተርፍ በመሆናችን በኢትዮጵያዊነታችን በውጭው ዓለም ኩራት አለን፡፡ የዶክተር ዐቢይ አሕመድን ራዕይ እንከተላለን፤ እንኳን በኢትዮጵያ በአፍሪካና በዓለም ላይ የምንኖር አንድ መሆን አለብን ፍቀር ሁልጊዜም ያሸንፋል፡፡

**ግዮን፡- እናመሰግናለን፡፡**

# በአዲስ አበባ የሌኒን ሀውልት ውዝግብ !

በአዲስ አበባ የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን(ኢሲኤ) ፊት ለፊት እስከ1983 ዓ.ም ድረስ የቭላድሚር ሌሊን ሀውልት ቆሞ እንደነበር ይታወሳል፡፡ 20 ቶን የሚመዝነውና ከነሀስ የተሰራው ይህ ግዙፍ ሀውልት የተሰራው በኢትዮጵያዊያንና ኩባዊያን አርቲስቶች ሲሆን የፈጀውም 40 ሺ ብር ነበር፡፡ ወጪውን የሸፈነው የሰሜን ኮሪያ መንግስት እንደነበር ሰነዶች ያመለክታሉ፡፡ ይህ ሀውልት የተሰራውም ሩሲያዊውን አብዮተኛ፣ ፖለቲከኛ፣ የፖለቲካ ሀሳብ አመንጪ፣ የሩሲያ ኮሙኒስት ፓርቲ መስራችና የሩሲያ የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር የሆኑትን ቭላድሚር ሌኒንን ለማስታወስ ነበር፡፡ ህወሀት/ኢህአዴግ አዲስ አበባን ሊቆጣጠር ጥቂት ቀናት ሲቀሩት ይህ ግዙፍ ሀውልት ተገርስሶ ወድቋል፡፡ ሀውልቱ ከወደቀ በኋላ ከእስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን ጀርባ ባለ ቦታ ተቀምጦ የነበረ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት በአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን የተሽከርካሪዎች ጥገና ጋራዥ ውስጥ ይገኛል፡፡ በመስቀል ፍላወር መንገድ የሚገኘው ጋራዥ ግን አሁን ተለዋጭ ቦታ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለከተማ ስለተሰጠው ከቦታው ሊነሳ ነው፡፡ ጋራዡ ያለበት ቦታ በለገሀር ይሰራል ለተባለው ኤግል ሂልስ ፕሮጀክት ፅህፈት ቤት ሊሆን ነው፡፡ የአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን ኮሙኒኬሽን ሀላፊ አቶ ጥኡማይ ወልደገብርኤል ለፎርቹን እንግሊዘኛ ጋዜጣ እንደተናገሩት ባለስልጣኑ በሚቀጥሉት ሶስት ወራት ውስጥ ጋራዡን ሙሉ በሙሉ ለቆ ለመውጣት በዝግጅት ላይ ይገኛል፡፡ በዚህ ሂደት የሌኒን ሀውልት እጣ ፈንታ ምን እንደሚሆን አቶ ጥኡማይ ተጠይቀው ሀውልቱን የማስተዳደር ሀላፊነት ባለስልጣኑ ስለሌለው እዛው ያለበት ቦታ ጥለውት እንደሚሄዱ ተናግረዋል፡፡ የአዲስ አበባ ባህልና ቱሪዝም ቢሮም ሀውልቱን ለመቀበል ፈቃደኛ እንዳልሆነ ተናግሯል፡፡ የቢሮው ምክትል ሃላፊ አቶ ስዩም ተመስገን ለጋዜጣው ሲናገሩ ‹‹እኛ ተጠያቂነት ያለብን ከ1990 ወዲህ ለተመዘገቡ ቅርሶች ብቻ ነው፡፡ ይህ ሀውልት በቅርስነት በእኛ ቢሮ አልተመዘገበም›› ብለዋል፡፡ በመሆኑም የሃውልቱ መጨረሻ እስካሁን አልታወቀም፡፡
(ምንጭ - የዘሀበሻ እለታዊ ዜና)

# ግማሽ ሚሊዮን ዶላር ያወጣው ጫማ



የናይኪ ጫማ አምራች ድርጅት በ1970ዎቹ ለስፖርተኞች ያመርታቸው ከነበሩ ጫማዎች መካከል አንዱ ዲዛይን የተደረገው የናይክ መሥራች ከነበሩት ግለሰቦች አንዱ በነበሩት ቢል ቦወርማን ሲሆን «የጨረቃ ጫማ» የሚል ቅጽል ስም ነበረው ያኔ፡፡
ለማንኛውም ይህ ስኒከር የዓለማችን ውዱ ስኒከር ተብሏል፡፡ የተሸጠውም ግማሽ ሚሊዮን ዶላር በሚሆን ነው፤ ወደኛ ሲመነዘር ይህ ጫማ በ20 ሚሊዮን ብር አካባቢ ነው የተሸጠው፡፡
ጫማውን የገዛው ማይልስ ናዳል የተባለ ካናዳዊ ቅርስ ሰብሳቢ ባለሐብት ነው፡፡ እንደዚህ ተመሳሳይ 99 ታሪካዊ ጫማዎችን ገዝቷል ሰውየው፡፡ በድምሩ ወደ 400 ሚሊዮን ብር ከፍሏል ለአሮጌዎቹ ጫማዎች፡፡
ምንጭ፡- BBC News Amharic

## የኢጀቶ ጨካኝ. . . ከገጽ 4 የዞረ

አባቱ የስብከተወንጌል አገልግሎት በሚሰጡበት የፕሮቴስታንት ቤተ እምነት ተደብቆ መያዙን የደረሰን መረጃ ያመለክታል፡፡

ከጥቃቱ ጋር በተያያዘ ቁጥራቸው ወደ 500 (አምስት መቶ) የሚጠጉ ንፁሃን ዜጎች በገዛ አገራቸው ለስደት ተዳርገዋል፡፡ ከተለያዩ የሲዳማ ዞን አካባቢዎች የተፈናቀሉት እነዚሁ የሌላ ብሔር ተወላጆች በኦሮሚያ ክልል ጉጂ ዞን ቦሬ ወረዳ ተጠልለው የሚገኙ ሲሆን ግብረሰናይ ድርጅቶችና ግለሰቦችም ከዕለት ጉርስ ጀምሮ ብርድልብስና አልባሳትን የመሣሠሉ ቁሶችን እየለገሷቸው እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡

## የደኢህዴን፣ የሲአንና የኢዜማ መግለጫ!

የደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ደኢህዴን) የሀዋሳ ከተማ አስተዳደርን ጨምሮ የሲዳማ እና የሀድያ ዞን ከፍተኛ ባለስልጣናትን ከኃላፊነት ማገዱን ሐሙስ እለት ከሰአት በኋላ አስታውቅዋል፡፡ ደኢህዴን በዚሁ መግለጫው እንዳስታወቀው የሀዋሳ ከተማ አስተዳደር እና የሲዳማ ዞን አመራሮች የታገዱት ሰሞኑን በሀዋሳ ከተማና እና በሲዳማ ዞን የገጠር አካባቢዎች በተከሰተው ግጭት የራሳቸው ሚና ነበራቸው በሚል ነው፡፡ የሃድያ ዞን አመራሮች ላይ በዞኑ የህዝቡን ሰላም እና ደህንነት አደጋ ላይ ከሚጥሉ እንቅስቃሴዎች ጋር በተያያዘ ተመሳሳይ የማገድ እርምጃ መወሰዱን አመልክቷል፡፡

ንቅናቄው ከስልጣን አግጃቸዋለሁ ያላቸውን የሲዳማና የሀድያ ዞን ባለስልጣናት "የፊት አመራሮች " ከማለት ውጪ ቁጥራቸውንም ሆነ ማንነታቸውን አልጠቀሰም፡፡ በደቡብ ክልል በከፋ እና በወላይታ ዞኖች የተስተዋሉት ተመሳሳይ ድርጊቶችም የህግ ተጠያቂነትን የሚያስከትሉ ናቸው ሲል ድርጅቱ በመግለጫው ጠቁሟል፡፡

በዚህ የደኢህዴን መግለጫ “የፊት አመራሮች” ተብለው የተገለፁት “እነማን ናቸው?” በሚል ለማጣራት ባደረግነው ሙከራ የግጭቱ መነሻና ማጠንጠኛ የነበረችው የሐዋሳ ከተማ ከንቲባ አቶ ስኳሬ ሹንዳ እና የሲዳማ ዞን አስተዳዳሪ የሆኑት አቶ ቃሬ ጫዊሳን ጨምሮ ሌሎች የአስተዳደርና የፀጥታ ሀላፊዎችም ሲሆኑ እንደሚችሉ ከቅርብ ምንጮች ተጠቁሞናል፡፡

ሐምሌ 18 ቀን 2011 ተጀምሮ ለተከታታይ አምስት ቀናት እንደሚዘልቅ በሚጠበቀው የደኢህዴን ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ ለጊዜው ከስልጣን ተገልለው እንዲቆዩ የተወሰነባቸው አመራሮች በውሣኔው መሰረት ከየትኛውም የፖለቲካ ተሳትፎና የአስተዳደር ስራ ታግደው የሚቆዩ ሲሆን፣ ምናልባትም የክልሉ ም/ቤት በሚያደርገው አስቸኳይ ስብሰባ ያለመከሰስ መብታቸው ተነስቶ በህግ ተጠያቂ የሚሆኑበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችልም የቅርብ ምንጮች ያላቸውን ግምት ሰንዝረዋል፡፡

በሌላ በኩል በደቡብ ኢትዮጵያ ሲዳማ ዞን ካለፈዉ ሳምንት ጀምሮ በተከሰተው ግጭትና ግድያ ለጠፋዉ ሕይወት፣ አካልና ንብረት የአካባቢው ፖለቲከኞች ወቀሳ ጀምረዋል፡፡ሲዳማ ዞን የክልል አስተዳደርነት ሥልጣን እንዲኖው በቀረበዉ ጥያቄ መዘዝ የተገደለው ሰው ቁጥርና የጠፋውን ንብረት ብዛት በተመለከተ ከክልሉም ሆነ ከዞኑ ባለስልጣናት እስካሁን በይፋ ያስታወቁት ነገር የለም፡፡ የዓይን ምስክሮችና ተቃዋሚ ፖለቲከኞች ግን በግጭቱ በትንሹ 60 ሰዎች ተገድለዋል፤ ብዙ ሚሊዮን ብር የሚያወጣ ንብረት ወድሟል ይላሉ፡፡ተቃዋሚው የሲዳማ አርነት ንቅናቄ (ሲአን) ሐሙስ ባወጣዉ መግለጫ ለግድያና ግጭቱ “ለተነሳው ጥያቄ በሕገ-መንግስቱ መሠረት” መልስ ያልሰጡ ያላቸውን ወገኖች ተጠያቂ አድርጓል፡፡ ንቅናቄው ተጠያቂ ያላቸውን ወገኖች ግን በስም አልጠቀሰም፡፡

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትሕ ፓርቲ (ኢዜማ) በሲዳማ ዞን የተፈጠረውን ግጭትና በዜጎች ላይ የደረሰውን ጉዳት በቀዳሚነት ካወገዙ የአገር ውስጥ ፖለቲካ ፓርቲዎች ቀዳሚው ሆኗል፡፡

“በዜጎች ላይ ኢ መደበኛ በሆኑ ቡድኖች ጉዳት እንዲደርስ ግፊት ያደረጉ ሀይሎች ለደረሰው መጠነ ሰፊ ጉዳት ሀላፊነት ሊወስዱ ይገባል” ያለው ኢዜማ መንግሥት በአጥፊዎች ላይ ጠንካራ እርምጃ እንዲወስድና ሠላማዊ ዜጎችን ከጥቃት እንዲከላከል ጠይቋል፡፡

# ክፍት የስራ ቦታ ማስታወቂያ በሳውዲ አረቢያ

**የኤጀንሲው ስም:-** አንሊሚትድ በውጭ ሀገር ስራና ሰራተና አገናኝ ኤጀንሲ

**የኤጀንሲው የፍቃድ ቁጥር** PEA /491/2019

**ኤጀንሲው ፍቃድ ያገኘበት ሀገር** ሳውዲ አረቢያ

| የተገኘው ክፍት የስራ መደብ | ፆታ | የሚፈለገው ብዛት | መነሻ ደሞዝ | ተፈላጊ ችሎታ |
|---|---|---|---|---|
| የቤት አያያዝ | ሴት | 50 | በስምምነት | 8ኛ ክፍል ያጠናቀቀች፣ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ያላት |
| የቤተሰብ ሹፌር | ወንድ | 50 | በስምምነት | 8ኛ ክፍል ያጠናቀቀች፣ አለም አቀፍ መንጃፍቃድያለው |
| የቤት ውስጥ ስራ | ሴት | 50 | በስምምነት | 8ኛ ክፍል ያጠናቀቀች፣ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ያላት |

**በሁሉም የስራ መደቦች ላይ ለሚመዘገቡ ሰራተኞች ማሳሰቢያ**

- እድሜ ከ 18- 40
- የቅጥር ቆይታ 2 (ሁለት) አመት
- ስራው የተገኘበት ሀገር ሳውዲ አረቢያ
- የስልክ አቅርቦት ይመቻቻል
- ደሞዝ በየወሩ ይከፈላል
- አመልካቾች ወቅቱ ያላለፈበት የቀበሌ መታወቂያ ያለው/ያላት መሆን አለባቸው::
- ኤጀንሲው ለሚሰጠው ማንኛውም አገልግሎት ሰራተኛውን ምንም አይነት የአገልግሎት ክፍያ አያስከፍልም
- አመልካቾች ማስታወቂያው ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ጊዜያት በኤጀንሲው ቢሮ የት/ት ማስረጃና የስራ ልምዳቸውን ዋናውና ፎቶ ኮፒው በመያዝ በግንባር ቀርበው መመዝገብ ይችላሉ::

**አድራሻ:-** እንቁላል ፋብሪካ ሀዊ ህንፃ 2ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 207-208

**ስልክ ቁጥር:-**+251912476004 +251983797111